# M

**macabre** አሰቃቂ
The battlefield was a macabre sight. የጦርነቱ ፡ ሜዳ ፡ አሰቃቂ ፡ ትዕይንት ፡ ነበር

**macerate** (vt.) እንዲለሰልስ ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ዘፈዘፈ
She macerated the meat for two days. ሥጋው ፡ እንዲለሰልስ ፡ ለሁለት ፡ ቀን ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ዘፈዘፈችው

**macerate** (vi.) መነመነ
The ascetic's body slowly macerated. የመናኙ ፡ ሰውነት ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ መነመነ

**machine** መኪና
The machine is working again. መኪናው ፡ እንደገና ፡ ይሠራ ፡ ጀመር

**machine gun** መትረየስ
He sprayed the advancing troops with a machine gun. የሚገፋውን ፡ ጦር ፡ በመትረየስ ፡ ረፈረፈው

**machinery** ፋብሪካ
New machinery has just been installed. አዲስ ፡ ፋብሪካ ፡ ገና ፡ አሁን ፡ ተተከለ

**mad**
1. እብድ. He drove like mad. እንደ ፡ እብድ ፡ ነዳ
He was bitten by a mad dog. በእብድ ፡ ውሻ ፡ ተነከሰ
2. ከንቱ. The dog made a mad effort to catch up with the train. ውሻው ፡ በባቡሩ ፡ ላይ ፡ ለመድረስ ፡ ከንቱ ፡ ሙከራ ፡ አደረገ
3. ኀይለኛ. A mad gale swept across the channel. ኀይለኛ ፡ ነፋስ ፡ በባሕር ፡ ሰላጤ ፡ ላይ ፡ አለፈ

**be mad** ጦፈ
He was so mad that his face was red. በጣም ፡ ጦፎ ፡ ስለነበረ ፡ ፊቱ ፡ ደም ፡ ለበሰ

**be mad about**
1. አበደ(ለት). She is mad about him because he is so pleasant. በጣም ፡ አስደሳች ፡ ስለሆነ ፡ አብዳለታለች
2. ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ወደደ. She is mad about hats. ባርኔጣ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ትወዳለች

**be mad at** ተናደደ
She is mad at me because I insulted her friend. ጓደኛዋን ፡ ስለሰደብኩባት ፡ ተናዳብኛለች

**be mad for**
*The dog was mad for water. ውሻውን ፡ በጣም ፡ ጠምቶት ፡ ነበር

**get mad** ተናደደ
He got mad and called me names. ተናዶ ፡ ሰደበኝ

**go mad** አበደ
He went mad during the bombardment. በቦምብ ፡ ድብደባው ፡ ጊዜ ፡ አበደ

**stark raving mad**
He was stark raving mad. ጨርቁን ፡ ጥሏል

**madam** ወይዘሮ
Madam Mammite came yesterday. ወይዘሮ ፡ ማሚቴ ፡ ትናንትና ፡ መጡ

**madame!** እሜቴ
Madame, your purse is open. እሜቴ ፣ ቦርሳዎ ፡ ክፍት ፡ ነው

**madden**
1. አሳበደ. The drug maddened him. መድኃኒቱ ፡ አሳበደው
2. አናደደ. His ignorance maddens me. የሱ ፡ ድንቁርና ፡ ያናድደኛል

**made**, see **make**

**mademoiselle** እቱ ፣ ወይዘሪት
Mademoiselle, please come here! እቱ ፣ ነይ ፡ እስቲ
Mademoiselle, how are you? ወይዘሪት ፣ እንደምን ፡ አለሽ ?

**made-up** የፈጠራ
This is a made-up tale. ይህ ፡ የፈጠራ ፡ ተረት ፡ ነው

**madhouse** የትርምስ ፡ ቦታ
The stores are madhouses during the Christmas rush. በገና ፡ በዓል ፡ ጊዜ ፡ መደብሮች ፡ የትርምስ ፡ ቦታዎች ፡ ናቸው

**madly** ሳይቈጠብ
They worked madly to fix the bridge. ድልድዩን ፡ ለመጠገን ፡ ሳይቈጠቡ ፡ ሠሩ

*He was madly in love with her. በፍቅሯ ፡ አብ ዷል

**run madly** እየከነፈ ፡ ሮጠ
He ran madly down the street. በመንገዱ ፡ ላይ ፡ እየከነፈ ፡ ሮጠ

**madman** ያበደ ፡ ሰው
Madmen have to live in a sequestered place. ያበዱ ፡ ሰዎች ፡ በተከለለ ፡ ቦታ ፡ መኖር ፡ አለባቸው

**madness** እብደት
It would be madness to climb the mountain during a storm. በኀይለኛ ፡ ዝናብ ፡ ጊዜ ፡ ተራራውን ፡ መውጣት ፡ እብደት ፡ ነው

**magazine**
1. መጋዘን. The ammunition is stored in an underground magazine. ጥይቱ ፡ የተከማቸው ፡ ባንድ ፡ ከመሬት ፡ በታች ፡ ባለ ፡ መጋዘን ፡ ውስጥ ፡ ነው
2. መጽሔት. This magazine appears twice monthly. ይህ ፡ መጽሔት ፡ በወር ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ይወጣል

**magic** (n.)
1. አስማት. They used magic to bewitch their enemies. ጠላቶቻቸውን ፡ በአስማት ፡ ያፈዙ ፡ ነበር
2. መተት. It suddenly appeared as if by magic. ልክ ፡ በመተት ፡ እንደሆነ ፡ ነገር ፡ በድንገት ፡ ታየ
3. ውበት. The magic of poetry captivates many people. የቅኔ ፡ ውበት ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ይማርካል

**magic** (adj.) በአስማት ፡ የተሠራ
A magic palace stood in place of their hut. በጎጆዋቸው ፡ ፈንታ ፡ በአስማት ፡ የተሠራ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ታየ

**black magic** አስማት
The witch doctor used black magic to injure his enemies. አስማተኛው ፡ ጠላቶቹን ፡ ለመጕዳት ፡ በአስማት ፡ ተጠቀመ

**magical, ~ spell** አስማት
A magical spell was cast on her. በአስማት ፡ ተይዛለች

**have a magical effect on** ነፍስ ፡ ዘራ(በት)
The sight of money had a magical effect on the tired man. ገንዘብ ፡ ማየቱ ፡ የደከመውን ፡ ሰው ፡ ነፍስ ፡ ዘራበት

**magician**
1. አስማተኛ. The magician conjured a rabbit out of a hat. አስማተኛው ፡ በመተቱ ፡ ከባርኔጣው ፡ ውስጥ ፡ ጥንቸል ፡ አወጣ
2. ጠንቋይ. The magician foretold my future. ጠንቋዩ ፡ ስለ ፡ ወደፊት ፡ ዕድሌ ፡ ነገረኝ

**magisterial** ሥልጣኔ ፡ ያለው
The captain spoke with a magisterial voice. ሻምበሉ ፡ ሥልጣኔ ፡ ባለው ፡ ድምፅ ፡ ተናገረ

**magistrate** የሕግ ፡ ባለሥልጣን
The magistrate has the authority to perform marriages. የሕጉ ፡ ባለሥልጣን ፡ ጋብቻን ፡ ለመፈጸም ፡ ሥልጣን ፡ አለው

**magnanimity** ለጋስነት
His magnanimity prompts him to help everyone who is in trouble. ለጋስነቱ ፡ የተቸገረን ፡ ሁሉ ፡ ለመርዳት ፡ ይገፋፋዋል

**magnanimous**
1. ይቅር ፡ ባይ. He is magnanimous toward his enemies. ጠላቶቹን ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ነው
2. ቸር. This magnanimous king is loved by his people. ይህ ፡ ቸር ፡ ንጉሥ ፡ በሕዝቡ ፡ የተወደደ ፡ ነው
*He showed a magnanimous attitude toward the conquered enemy. ድል ፡ የተመታውን ፡ ጠላት ፡ በፍቅር ፡ ዓይን ፡ ተመለከተ

**magnanimous with money** ለጋስ
He was magnanimous with his money and lost all his inheritance. በጣም ፡ ለጋስ ፡ ስለሆነ ፡ የወረሰውን ፡ ሀብት ፡ ሁሉ ፡ አጠፋ

**magnate** ሥልጣንና ፡ ሀብት ፡ ያለው
The magnates control all our industries. እንዱስትሪዎችን ፡ ሁሉ ፡ የያዙት ፡ ሥልጣንና ፡ ሀብት ፡ ያላቸው ፡ ናቸው

**magnet** ማግኔት
The magnet picks up nails. ማግኔት ፡ ምስማር ፡ ከመሬት ፡ ያነሣል

**magnetize**
1. ወደ ፡ ማግኔትነት ፡ ለወጠ. You can magnetize a needle by rubbing it with a magnet. መርፌን ፡ በማግኔት ፡ ላይ ፡ በመፈግፈግ ፡ ወደ ፡ ማግኔትነት ፡ ልትለውጥ ፡ ትችላለህ
2. ማረከ. Her beautiful voice magnetized the audience. የሚያምረው ፡ ድምጿ ፡ አድማጩን ፡ ማረከው

**magnificence** አስደናቂነት
The magnificence of mountain scenery attracts many visitors. የተራራው ፡ አስደናቂነት ፡ ብዙ ፡ ጐብኝዎችን ፡ ይስባል

**magnificent**
1. ዕጹብ ፡ ድንቅ. The Emperor's palace is magnificent. የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ዕጹብ ፡ ድንቅ ፡ ነው

2. በጣም ፡ ድንቅ. This is a magnificent idea. ይህ ፡ በጣም ፡ ድንቅ ፡ ሐሳብ ፡ ነው

**magnify** (magnified)
1. አጕልቶ ፡ አሳየ. This lens magnifies six times. ይህ ፡ መነጽር ፡ በድስት ፡ እጅ ፡ አጕልቶ ፡ ያሳያል
2. አጋነነ. He magnifies the deeds that he has done. የሠራቸውን ፡ ተግባሮች ፡ ያጋንናል

**magnifying glass** የሚያጕላ ፡ መነጽር
You can see it only with a magnifying glass. ልታየው ፡ የምትችለው ፡ በሚያጕላ ፡ መነጽር ፡ ብቻ ፡ ነው

**magnitude**
1. መጠን. The magnitude of the building makes it the largest in the world. የሕንጻው ፡ መጠን ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ ካሉት ፡ ሁሉ ፡ ትልቅ ፡ ያደርገዋል
2. ከፍተኛነት. The magnitude of the loss ruined the business completely. የኪሳራው ፡ ከፍተኛነት ፡ ንግዱን ፡ ፈጽሞ ፡ አበላሸው

**of great magnitude** እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ
War brings problems of great magnitude to many nations. ጦርነት ፡ በብዙ ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ችግሮችን ፡ ያስከትላል

**maid** ገረድ
We hired a maid last month. ባለፈው ፡ ወር ፡ ገረድ ፡ ቀጠርን

**maiden** (n.) ልጃገረድ
A maiden should not trust a young man's praises. ልጃገረድ ፡ የጐረምሳን ፡ ሙገሳ ፡ አምና ፡ መቀበል ፡ የለባትም

**maiden** (adj.)
1. ያልተዳረች. My maiden aunt is coming to see us today. ያልተዳረችው ፡ አክስቴ ፡ ዛሬ ፡ ልትጠይቀን ፡ ትመጣለች
2. የመጀመሪያ. This is the ship's maiden voyage. ይህ ፡ የመርከቧ ፡ የመጀመሪያ ፡ ጉዞ ፡ ነው

**mail** (v.) በፖስታ ፡ ላከ
Please mail the letter for me! ደብዳቤውን ፡ በፖስታ ፡ ላክልኝ

**mail** (n.) ደብዳቤ
In some American cities, the mail is delivered twice a day. ባንዳንድ ፡ የአሜሪካ ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ ደብዳቤ ፡ በቀን ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ይታደላል

**by mail** በፖስታ ፡ ቤት ፡ በኩል
The package will be sent to you by mail. ጥቅሉ ፡ በፖስታ ፡ ቤት ፡ በኩል ፡ ይላክልሃል
[See also 'return']

**mailbox** የፖስታ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ ሣጥን
Where is the nearest mailbox? ቀረብ ፡ ያለው ፡ የፖስታ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ ሣጥን ፡ የት ፡ ነው ?

**mail carrier** ደብዳቤ ፡ አመላላሽ
A postman is sometimes called a mail carrier. ፖስተኛ ፡ አንዳንዴ ፡ ደብዳቤ ፡ አመላላሽ ፡ ይባላል

**mailman** ፖስተኛ
I hope the mailman will bring me a letter. ፖስተኛው ፡ ደብዳቤ ፡ እንደሚያመጣልኝ ፡ ተስፋ ፡ አለኝ

**maim** አካለ ፡ ጐደሎ ፡ አደረገ
A leg wound maimed the soldier for life. የግሩ ፡ ላይ ፡ ቁስል ፡ ወታደሩን ፡ ዕድሜ ፡ ልኩን ፡ አካለ ፡ ጐደሎ ፡ አደረገው

**main** (n.), **water** ~ ቧምቧ
The water main broke and so we had no water. ቧምቧው ፡ ስለተሰበረ ፡ ውኃ ፡ አጣን

**in the main**
1. አብዛኛውን ፡ ጊዜ. The discussion revolved in the main around two questions. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ውይይቱ ፡ ስለ ፡ ሁለቱ ፡ ጥያቄዎች ፡ ነበር
2. በጠቅላላው. I agree with him in the main. በጠቅላላው ፡ ከሱ ፡ ጋር ፡ እስማማለሁ

**main** (adj.) ዋና
You have forgotten the main thing. ዋናውን ፡ ነገር ፡ ዘንግተሃል
Did you inquire at the main office? ዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ጠይቀሃል ?
[See also 'point']

**mainland** የብስ
We crossed from the island to the mainland in a boat. ከደሴቱ ፡ ወደ ፡ የብስ ፡ በጀልባ ፡ አቋረጥን

**mainly** አብዛኛውን ፡ ጊዜ
He comes mainly on Tuesdays. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ማክሰኞ ፡ ይመጣል
*He is mainly interested in making money. ዋናው ፡ ፍላጎቱ ፡ ገንዘብ ፡ ማግኘት ፡ ነው

**mainstay**
1. መሠረት. The mainstay of Ethiopian economy is agriculture. የኢትዮጵያ ፡ የምጣኔ ፡ ሀብት ፡ መሠረት ፡ እርሻ ፡ ነው
2. ዋና ፡ ደጋፊ ፤ ምሰሶ. He is his parents' mainstay; without him, they would starve to death. የወላጆቹ ፡ ዋና ፡ ደጋፊ ፡ እሱ ፡ ነው ፤ እሱ ፡ ባይኖር ፡ በረኃብ ፡ ይሞቱ ፡ ነበር

Through her work she was the mainstay of the family. በሥራዋ ፡ የቤቱ ፡ ምሰሶ ፡ እሷ ፡ ነበረች

**mainstream** ዋና ፡ ግንባር
The mainstream of American politics favors the center. ዋናው ፡ ያሜሪካን ፡ ፖለቲካ ፡ ግንባ ር ፡ የሚከተለው ፡ አማካዩን ፡ መንገድ ፡ ነው

**Main Street** ዋና ፡ ጐዳና
Main Street was full of cars. ዋናው ፡ ጐዳና ፡ በመኪና ፡ ተሞልቶ ፡ ነበር

**maintain**
1. አስተዳደረ. He spends a hundred dollars a week just to maintain his family. ቤተሰቡን ፡ ለ ማስተዳደር ፡ ብቻ ፡ በሳምንት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ያወጣል
2. ያዘ. You must maintain your equipment in good condition. መሣሪያህን ፡ በጥሩ ፡ ሁኔታ ፡ መያዝ ፡ አለብህ
3. ጠበቀ. The church has a vested interest in maintaining its schools. ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትምህ ርት ፡ ቤቶቿን ፡ ለመጠበቅ ፡ እሷን ፡ የሚነካ ፡ ጥ ቅም ፡ አላት
The government is trying to maintain friendly relations with all countries. መንግሥቱ ፡ ከሁሉ ም ፡ ሀገሮች ፡ ጋር ፡ ወዳጅነት ፡ ለመጠበቅ ፡ ይ ሞክራል
4. በሚገባ ፡ ጠበቀ. It costs a lot of money just to maintain the road. መንገዱን ፡ በሚገባ ፡ መ ጠበቁ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ይፈጃል
5. አለ. He maintains that he was there. እዚያ ፡ ነበርኩ ፡ ይላል
6. ተከራከረ. He maintains his innocence. ንጹሕ ፡ ስለ ፡ መሆኑ ፡ ይከራከራል
7. አስከበረ. The police must maintain public security. ፖሊስ ፡ የሕዝብን ፡ ጸጥታ ፡ ማስከበር ፡ አለበት
8. አደረገ (ተደረገ). Contact with the main office is maintained by radio. ከዋናው ፡ መሥሪያ ፡ ቤ ት ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ የሚደረገው ፡ በሬዲዮ ፡ ነው
*Everyone wants to maintain a good reputation. ማንም ፡ ቢሆን ፡ መልካም ፡ ስም ፡ እንዲኖረው ፡ ይፈልጋል
[See also 'hold']

**maintenance**
1. መጠበቂያ. A thousand dollars have been granted for road maintenance. ለመንገድ ፡ መጠ በቂያ ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ተሰጥቷል
2. መተዳደሪያ. Taxes pay for the maintenance of schools. ከግብር ፡ የሚገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ለትም ህርት ፡ ቤቶች ፡ መተዳደሪያ ፡ ይውላል
3. ለኑሮ ፡ ያህል. His small farm provides a maintenance, but not much more. ትንሹ ፡ እርሻ ው ፡ ለኑሮው ፡ ያህል ፡ እንጂ ፡ የበለጠ ፡ አይሰጥም
4. ማክበር. Maintenance of quiet is necessary in a hospital. ሐኪም ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ጸጥታን ፡ ማክበር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው

**maize** በቆሎ
Maize is seeded in May. በቆሎ ፡ የሚዘራው ፡ በ ግንቦት ፡ ነው

**majestic** ባለግርማ
The palace is a majestic building. ቤተ ፡ መንግ ሥቱ ፡ ባለግርማ ፡ ሕንጻ ፡ ነው

**majestic appearance** ግርማ ፡ ሞገስ
He has a majestic appearance. ግርማ ፡ ሞገስ ፡ አለው

**majesty** (majesties)
1. ግርማ. The majesty of the night sky impressed him. የሌሊቱ ፡ ሰማይ ፡ ግርማ ፡ በጣም ፡ አስደነቀው
2. ሞገስ. The majesty of the mountains awed us. የተራራው ፡ ሞገስ ፡ አስደነቀን
3. ኀይል. Policemen and judges maintain the majesty of the law. ፖሊሶችና ፡ ዳኞች ፡ የሕግ ን ፡ ኀይል ፡ ያስከብራሉ

**majesties** ነገሥታት
The wedding was attended by the majesties of Europe. የአውሮፓ ፡ ነገሥታት ፡ በጋብቻው ፡ ላይ ፡ ተገኝተው ፡ ነበር

**His Majesty** ግርማዊነታቸው
His Majesty will see you now. አሁን ፡ ግር ማዊነታቸው ፡ ፊት ፡ ትቀርባለህ

**Your Majesty!** ግርማዊ ፡ ሆይ!
Your Majesty, may I present to you the Swedish ambassador. ግርማዊ ፡ ሆይ! የስዊድንን ፡ አምባሳደር ፡ እንዳቀርብ ፡ ይፈቀድልኝ

**major** (n.)
1. ሻለቃ. The major was promoted. ሻለቃው ፡ የ ማዕረግ ፡ እድገት ፡ አገኘ
2. ዋና ፡ ትምህርት. What was your major in college? ኮሌጅ ፡ ሆነህ ፡ ዋናው ፡ ትምህርትህ ፡ ምን ፡ ነበር ?

**major** (adj.)
1. ዋና. A major cause of accidents is driving while intoxicated. ያደጋዎች ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ በስካር ፡ መንፈስ ፡ መንዳት ፡ ነው
2. ትልቅ. A major war will probably put an end to civilization. ትልቅ ፡ ጦርነት ፡ ቢነሣ ፡ ሥ ልጣኔን ፡ ሳያወድም ፡ አይቀርም

3. ከፍ ፡ ያለ. Garbage disposal is a major problem for large cities. ለታላላቅ ፡ ከተማዎች ፡ ቆሻሻ ፡ ማንሣት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ነው

**major part** ይበልጡ

The major part of my income goes for rent. ከገቢዬ ፡ ይበልጡ ፡ የሚውለው ፡ ለቤት ፡ ኪራይ ፡ ነው

**majority** (majorities)

1. አብዛኞች. The majority was against it. አብዛኞቹ ፡ ተቃውመውት ፡ ነበር

2. በዛ ፡ ያለ ፡ ወገን. Ethiopia aligned herself with the majority on that vote. ኢትዮጵያ ፡ ድምፅ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ በዛ ፡ ካለው ፡ ወገን ፡ ተሰለፈች

3. የድምፅ ፡ ብልጫ. He was elected by a bare majority. የተመረጠው ፡ ባነስተኛ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ነው

4. ዓቅመ ፡ አዳም. When will he attain his majority? ለዓቅመ ፡ አዳም ፡ የሚደርሰው ፡ መቼ ፡ ነው ?

5. አካለ ፡ መጠን ፤ ዓቅመ ፡ ሔዋን. When will she attain her majority? እሷ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ (ለ ዓቅመ ፡ ሔዋን) ፡ የምትደርሰው ፡ መቼ ፡ ነው ?

**(the) majority of** አብዛኞዎቹ

The majority of the students were sick. አብዛኞዎቹ ፡ ተማሪዎች ፡ ታመው ፡ ነበር

**majority vote** የድምፅ ፡ ብልጫ

The farmers have the majority vote in all elections. በማንኛውም ፡ ምርጫ ፡ ገበሬዎቹ ፡ የድምፅ ፡ ብልጫ ፡ አላቸው

**(the) great majority of** እጅግ ፡ የሚበዛው

The great majority of people favor having elections. እጅግ ፡ የሚበዛው ፡ ሕዝብ ፡ ምርጫ ፡ እንዲደረግ ፡ ይደግፋል

[See also 'narrow, preponderate']

**make** (made)

1. አደረገ. They made him chairman. ሊቀ ፡ መንበር ፡ አደረጉት

2. አድርጎ ፡ ሾመ. The President made him his special envoy. ፕሬዚዳንቱ ፡ ልዩ ፡ መልእክተኛ ፡ አድርገው ፡ ሾሙት

3. አዘጋጀ. Since the mother was at work, the daughter made the meal. እናትየዋ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ስለነበረች ፡ ምግቡን ፡ ልጅቷ ፡ አዘጋጀች

4. ሠራ. The man made a bed. ሰውዬው ፡ አልጋ ፡ ሠራ

5. አነጠፈ. The maid makes the bed every evening. ገረዲቱ ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ አልጋ ፡ ታነጥፋለች

6. አገኘ. How much do you make a week? በሳምንት ፡ ስንት ፡ ታገኛለህ ?

7. ተጓዘ. We have made eighty miles since noon. ከእኩለ ፡ ቀን ፡ ወዲህ ፡ ሰማንያ ፡ ማይል ፡ ተጉዘናል

8. ወጣ. Our teacher made the front page of the Amharic newspaper. መምህራችን ፡ ባማርኛው ፡ ጋዜጣ ፡ በመጀመሪያ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ወጣ

9. ወጣ(ው). +If you study hard, you will make a good doctor. በርትተህ ፡ ካጠናህ ፡ ጥሩ ፡ ሐኪም ፡ ይወጣሃል

10. አፈራ. His disdainful attitude made him many enemies. ሰውን ፡ የመናቅ ፡ ጠባዩ ፡ ብዙ ፡ ጠላት ፡ አፈራለት

11. ደረሰ(በት) ፤ ደረሰ. Do you think we will make the train? ባቡሩን ፡ የምንደርስበት ፡ ይመስልሃል ?

You can make home by sundown. ፀሐይ ፡ ዘቅዘቅ ፡ ስትል ፡ እቤት ፡ ልትደርስ ፡ ትችላለህ

12. አስ-stem, or አ-stem. You make me laugh. ታሥቀኛለህ

13. ሆነ. Twelve inches make a foot. ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ኢንች ፡ አንድ ፡ ጫማ ፡ ይሆናል

Bread and milk will make a supper for us. ዳቦና ፡ ወተት ፡ እራት ፡ ይሆነናል

Two and two make four. ሁለትና ፡ ሁለት ፡ አራት ፡ ይሆናል

14. ነው. This makes the fifth time you failed an exam. ፈተና ፡ ስትወድቅ ፡ ይህ ፡ አምስተኛ ፡ ጊዜህ ፡ ነው

*He'll make his way in life all right. ኑሮው ፡ ይቃናለታል

**make after** አሳደደ

The men made after the thief, but could not catch him. ሰዎቹ ፡ ሌባውን ፡ አሳደዱት ፤ ግን ፡ ሊይዙት ፡ አልቻሉም

**make as if**

1. (relative verb) + መሰለ. We will make as if to leave, then come back and bring him a present. የምንሄድ ፡ መስለን ፡ ስጦታ ፡ ይዘንለት ፡ እንመለስ

2. ቃጣ. He made as if to strike me. ሊመታኝ ፡ ቃጣብኝ

**make away with**

1. ይዞ ፡ ጠፋ. The embezzler made away with thousands of dollars. አጭበርባሪው ፡ ብዙ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ይዞ ፡ ጠፋ

2. ጨረሰ. He made away with the whole loaf of bread. ዳቦውን ፡ በሙሉ ፡ ጨረሰው

3. አጠፋ. He made away with his enemies. ጠላቶቹን ፡ አጠፋቸው

**make do (with, without)**

1. በላ. You will have to make do with

roasted beans for dinner. ለእራት ፡ ቆሎ ፡ መብላት ፡ ይኖርብሃል
2. ኖረ. During the war, we had to make do without coffee or butter. በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ ቡናና ፡ ያለ ፡ ቅቤ ፡ መኖር ፡ ነበረብን

**make (for)**
1. አመራ. They made for the hills. ወደ ፡ ኮረብታዎቹ ፡ አመሩ
2. ገሰገሰ. The soldiers made for the enemy camp by night. ወታደሮቹ ፡ ወደ ፡ ጠላት ፡ ሰፈር ፡ በሌሊት ፡ ገሰገሱ
3. ለማግኘት ፡ ረዳ. Respect for the rights of others makes for a happy life. የሌሎችን ፡ መብት ፡ ማክበር ፡ ደስተኛ ፡ ኑሮን ፡ ለማግኘት ፡ ይረዳል

**make (one's) fortune** ሀብታም ፡ ሆነ
He made his fortune in oil. በዘይት ፡ ንግድ ፡ ሀብታም ፡ ሆነ

**make it**
1. ደረሰ(በት). He just made it; the bus was leaving. አውቶቡሱ ፡ ሊነሣ ፡ ለጥቂት ፡ ደረሰበት
2. ሆነ(ለት). You don't have to worry; he will make it. አታስብ ፤ ይሆንለታል

**make of** አለ
What do you make of his strange behavior? ይህንን ፡ እንግዳ ፡ ጠባዩን ፡ ምን ፡ ትለዋለህ?

**make off** ሸሽቶ ፡ ሄደ
The witness to the accident made off before the police arrived. ባደጋው ፡ የነበረ ፡ ምስክር ፡ ፖሊስ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ሸሽቶ ፡ ሄደ

**make off with** ይዞ ፡ ጠፋ ፤ ዘረፈ
The thief made off with all my money. ሌባው ፡ ገንዘቤን ፡ ሁሉ ፡ ይዞ ፡ ጠፋ
Someone broke in and made off with all our money. አንድ ፡ ሰው ፡ ቤታችንን ፡ ሰብሮ ፡ ንብረታችንን ፡ ዘረፈን

**make out** (vt.)
1. ሞላ. Have you made out the application blank? የማመልከቻውን ፡ ፎርም ፡ ሞላህ?
2. ለየ. I can barely make out the ships in the distance. ከሩቅ ፡ መርከቡን ፡ እምብዛም ፡ አልለይም
3. ገባ(ው). +Can you make out what he means? የሚለው ፡ ይገባሃል?
4. ጻፈ. He made out a check for fifteen dollars. የዐሥራ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ቼክ ፡ ጻፈ
He made out his will. ኑዛዜውን ፡ ጻፈ
5. አሰበ(ለት). Please make out our bill! ሒሳባችንን ፡ አስብልን

**make out** (vi.)
1. ሆነ. How did you make out yesterday? ትላንትና ፡ እንዴት ፡ ሆንክ ?
2. ዘለቀ. He will make out all right. በደኅና ፡ ይዘልቃል
3. ያዘ(ው). +How are you making out in your new job? አዲሱ ፡ ሥራህ ፡ እንዴት ፡ ይዞሃል ?

**make (one) out**
*He is a strange person; I can't make him out at all. ጠባዩ ፡ የተለየ ፡ ስለሆነ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አልችልም

**make over**
1. አስተላለፈ. He made over the whole of his property to the national trust. ሀብቱን ፡ በሙሉ ፡ ለብሔራዊ ፡ ድርጅት ፡ አስተላለፈ
2. በሱ ፡ ስም ፡ አዛወረ(ለት). Her father made over the farm to her. አባቷ ፡ መሬቱን ፡ በሷ ፡ ስም ፡ አዛወረላት
3. ለወጠ. She tried to make over her husband after their marriage. ከተጋቡ ፡ በኋላ ፡ ባሏን ፡ ልትለውጠው ፡ ሞከረች

**make up** (vt.)
1. ፈጠረ. He is very ingenious when it comes to making up excuses. ምክንያት ፡ በመፍጠር ፡ አንደኛ ፡ ነው
2. አዘጋጀ. The druggist made up the prescription for me. መድኃኒት ፡ ቀማሚው ፡ መድኃኒቱን ፡ አዘጋጀልኝ
Did he make up the speech himself? ንግግሩን ፡ ያዘጋጀው ፡ ራሱ ፡ ነው ?
3. አሟላ. I still need five dollars to make up the sum you asked for. የጠየቅኸኝን ፡ ገንዘብ ፡ ለማሟላት ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ይቀረኛል
4. ሠራ. Make up a sentence with the word 'no'! «የለም» ፡ በሚለው ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ ሥራ
*Water makes up most of the earth's surface. አብዛኛው ፡ የመሬት ፡ ገጽ ፡ በውኃ ፡ የተሸፈነ ፡ ነው

**(not) be made up**
1. ሊተካ ፡ አይችልም. Losses in war are not soon made up. በጦርነት ፡ ምክንያት ፡ የሚደርስ ፡ ጥፋት ፡ በቶሎ ፡ ሊተካ ፡ አይችልም
2. አልተመለሰም. Lost time can never be made up. የባከነ ፡ ጊዜ ፡ አይመለስም

**make up for**
1. አረመ. You cannot make up for past mistakes. ያለፈውን ፡ ስሕተት ፡ ለማረም ፡ አትችልም
2. ሸፈነ(ለት). His kind act made up for his rough manner. የደግነት ፡ ሥራው ፡ ባለጌ ፡ ጠባዩን ፡ ይሸፍንለታል

**make up with** ታረቀ
He made up with his wife after the quarrel. ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ ከተጣላ ፡ በኋላ ፡ ታረቀ

[See also 'bed, believe, face, fortune, good, mind, nothing, time, way']

**make** (n.) ዓይነት
What make is your radio? ራዲዮንህ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ነው ?

**make-believe** የማስመሰል
A make-believe battle was performed on the stage. በመድረኩ ፡ ላይ ፡ የማስመሰል ፡ ጦርነት ፡ ተሠራ

**makeshift**
1. ምትክ. When the electric lights went out, we used candles as a makeshift. ኮረንቲው ፡ በጠፋ ፡ ጊዜ ፡ በምትኩ ፡ ሻማ ፡ አበራን
2. በምትኩ ፡ ሌላ ፡ ነገር. We couldn't find any pliers, so we had to use a makeshift. መቆንጠጫ ፡ ስላልነበረን ፡ በምትኩ ፡ በሌላ ፡ ነገር ፡ መጠቀም ፡ ነበረብን
3. ቢጤ. He used a makeshift screwdriver to remove the screw. ቡሎኑን ፡ ለመፍታት ፡ በጠመንጃ ፡ መፍቻ ፡ ቢጤ ፡ ተጠቀመ

**makeup**
1. አቀማመጥ. The makeup of the front page is not clear. የመጀመሪያው ፡ ገጽ ፡ አቀማመጥ ፡ ጉልህ ፡ አይደለም
2. ፊቱን ፡ የተቀባባው. Her makeup was washed away by the rain. ፊቷን ፡ የተቀባባችው ፡ በዝናብ ፡ ሙልጭ ፡ ብሎ ፡ ታጠበ
3. የተፈጥሮ ፡ ጠባይ. Shyness is part of his makeup. ዓይነ ፡ አፋርነት ፡ የተፈጥሮ ፡ ጠባዩ ፡ ነው

**wear makeup** ተኳኳለ
She wears makeup all the time. ሁልጊዜ ፡ ትኳኳላለች

**making** መሥራት
The making of a violin requires great skill. ቫዮሊን ፡ መሥራት ፡ ትልቅ ፡ ጥበብ ፡ ይጠይቃል

**makings** ባሕርይ
I see in him the makings of a hero. የጀግና ፡ ባሕርይ ፡ አይቼበታለሁ

**maladjusted** ካካባቢው ፡ ጋር ፡ የማይስማማ
The maladjusted children show a tendency to be sick more often than the happy children. ካካባቢያቸው ፡ ጋር ፡ የማይስማሙ ፡ ልጆች ፡ ከደስተኞች ፡ ልጆች ፡ የበለጠ ፡ የመታመም ፡ ዝንባሌ ፡ ያሳያሉ

**malady** (maladies) በሽታ
Lying and cheating are social maladies. መዋሸትና ፡ ማጭበርበር ፡ የኅብረተ ፡ ሰብ ፡ በሽታዎች ፡ ናቸው

**malaria** ወባ
He got infected with malaria while in the swamp. ረግረጉ ፡ ውስጥ ፡ ሳለ ፡ ወባ ፡ ያዘው

**male** (n.) ወንድ ፤ ተባዕት
Is that dog a male or a female? ያ ፡ ውሻ ፡ ወንድ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ሴት ?
This basketball team consists of three males and two females. ይህ ፡ የቅርጫት ፡ ኳስ ፡ ቡድን ፡ ሦስት ፡ ተባዕቶችና ፡ ሁለት ፡ አንስቶች ፡ አሉበት

**male** (adj.) የወንዶች
Our school has a male choir only. ትምህርት ፡ ቤታችን ፡ ያለው ፡ የመዘመር ፡ ጓድ ፡ የወንዶች ፡ ብቻ ፡ ነው

**male being** ወንድ
Only male beings are allowed in this monastery. እዚህ ፡ ገዳም ፡ ለመግባት ፡ የሚፈቀድላቸው ፡ ወንዶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው

**malediction** እርግማን
A father's malediction has great effect. ያባት ፡ እርግማን ፡ አጥንት ፡ ይሰብራል

**malevolent, ~ character** ተንኰለኛነት
His malevolent character shows in his constant efforts to belittle everyone. ተንኰለኛነቱ ፡ ሁልጊዜ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ለማቃለል ፡ በሚያደርገው ፡ ጥረት ፡ ይታወቃል

**malformation** በትክክል ፡ አለመብቀል
A malformation of his teeth prevented him from chewing well. የጥርሱ ፡ በትክክል ፡ አለመብቀል ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ እንዳያኝክ ፡ አደረገው

**malice** ተንኰል
His malice was responsible for my losing my job. ሥራዬን ፡ ለማጣት ፡ ያደረሰኝ ፡ የሱ ፡ ተንኰል ፡ ነው

**malicious** ተንኰል ፡ ያዘለ
His malicious remarks irritated everybody. ተንኰል ፡ ያዘለ ፡ አስተያየቱ ፡ ሁሉንም ፡ ሰው ፡ አበሳጨ

**malign** (v.) አማ
He maligns me when I am not around. በሌለሁበት ፡ ያማኛል

**malign** (adj.) የጭካኔ
The malign rule of the tyrant caused revolts, massacres, and exile. የጨቋኙ ፡ የጭካኔ ፡ አገዛዝ ፡ ሁከት ፡ ፍጅትንና ፡ ከሀገር ፡ መሰደድን ፡ አስከተለ
*Gambling has a malign influence. ቁማር ፡ ጉዳትን ፡ ያስከትላል

**malignant**
1. አደገኛ. The growth on his shoulder turned out to be malignant, so it was removed. በትከሻው ፡ ላይ ፡ ያደረበት ፡ እብጠት ፡ አደገኛ ፡ ሆኖ ፡ ስለተገኘ ፡ በቀዶ ፡ ጥገና ፡ ወጣለት
2. በጣም ፡ አረመኔ. Hitler was a malignant person. ሂትለር ፡ በጣም ፡ አረመኔ ፡ ሰው ፡ ነበር
3. የተንኰል. The malignant plot to oust the director failed. ዲሬክተሩን ፡ ለመሻር ፡ የተደረገው ፡ የተንኰል ፡ አድማ ፡ ከሸፈ

**malleable** በመቀጥቀጥ ፡ ሊሠራ ፡ የሚችል
Gold is a malleable metal. ወርቅ ፡ በመቀጥቀጥ ፡ ሊሠራ ፡ የሚችል ፡ የብረታ ፡ ብረት ፡ ዓይነት ፡ ነው

**mallet** የዕንጨት ፡ መዶሻ

**malnutrition** የምግብ ፡ ጉድለት
Malnutrition can cripple children. የምግብ ፡ ጉድለት ፡ ሕፃናትን ፡ አካለ ፡ ጐደሎ ፡ ሊያደርጋቸው ፡ ይችላል

**malpractice** ከአግባብ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ሕክምና
The Medical Association hopes to prevent malpractice. የሕክምና ፡ ማኅበር ፡ ከአግባብ ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ ሕክምናን ፡ ለማስወገድ ፡ ያስባል

**malt** ብቅል
We make beer with malt. ከብቅል ፡ ጠላ ፡ ይጠመቃል

**maltreat** አንገላታ
He maltreated his horse. ፈረሱን ፡ አንገላታው

**mamma** እማማ
Mamma came to visit me yesterday. ትላንትና ፡ እማማ ፡ መጥታ ፡ ጠየቀችኝ

**mammal** ወተት ፡ የምትሰጥ ፡ እንስሳ
Mammals suckle their young. ወተት ፡ የሚሰጡ ፡ እንስሳት ፡ ግልገሎቻቸውን ፡ ያጠባሉ

**man** (v.)
*During the war, the women had to man the factories. በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ሴቶች ፡ በወንዶች ፡ ቦታ ፡ ተተክተው ፡ በየፋብሪካዎቹ ፡ መሥራት ፡ ነበረባቸው

**man oneself** ሐሞቱን ፡ ቋጠረ
The captive manned himself to endure torture. ምርኮኛው ፡ ሥቃዩን ፡ ለመቋቋም ፡ ሐሞቱን ፡ ቋጠረ

**man** (men), n.
1. ሰው. God created man in his image. እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ ባምሳሉ ፡ ፈጠረ
He is not the man for it. እሱ ፡ የዚህ ፡ ሰው ፡ አይደለም
2. የሰው ፡ ልጅ. The two men engaged in a long dialogue concerning the rights of man. ሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ መብት ፡ ረጅም ፡ ውይይት ፡ አደረጉ
3. ባል. Man and wife are buried in the same grave. ባልና ፡ ሚስቱ ፡ ባንድ ፡ መቃብር ፡ ተቀበሩ
4. ወንድ. The army will make a man of you. ውትድርና ፡ ወንድ ፡ ያደርግሃል
5. ወታደር. One officer and four men volunteered to capture the rebel. አንድ ፡ መኰንንና ፡ አራት ፡ ወታደሮች ፡ ሽፍታውን ፡ ለመያዝ ፡ ፈቃደኞች ፡ ሆኑ
*They were killed to the last man. አንድም ፡ ሰው ፡ ሳይቀር ፡ አለቁ

**any man** ማንም
Any man can do it. ማንም ፡ ሊሠራው ፡ ይችላል

**as one man** ባንድነት
They arose as one man to protest the verdict. ፍርዱን ፡ ለመቃወም ፡ ባንድነት ፡ ተነሡ

**to a man**
*To a man, the members of the team did their best. እያንዳንዱ ፡ የቡድኑ ፡ አባል ፡ የሚቻለውን ፡ ያህል ፡ ሠርቷል
[See also 'aged, estate, leading, mark, mean, note, old, room, white, young']

**manage** (vt.)
1. አካሄደ. He managed the store for six years. መደብሩን ፡ ለስድስት ፡ ዓመታት ፡ አካሄደ
The house is so big that I wouldn't be able to manage without help. ቤቱ ፡ በጣም ፡ ትልቅ ፡ ስለሆነ ፡ ያለረዳት ፡ ላካሂደው ፡ አልችልም
2. አስተዳደረ. Who manages the estate? ርስቱን ፡ ማን ፡ ያስተዳድራል ?
3. ተቈጣጠረ. I cannot manage the children. ልጆቹን ፡ ልቈጣጠራቸው ፡ አልችልም
4. ፈጸመ. He managed this difficult affair with admirable address. ይህን ፡ አስቸጋሪ ፡ ጉዳይ ፡ በሚያስደንቅ ፡ ችሎታ ፡ ፈጸመው
5. ቻለ. How did you manage to get the tickets? ቲኬቶቹን ፡ እንዴት ፡ ለማግኘት ፡ ቻልህ ?
He managed to see the governor. አገረ ፡ ገዢውን ፡ ለማነጋገር ፡ ቻለ
6. ተሳካ(ለት). He barely managed it. ለጥቂት ፡ ተሳካለት

**manage** (vi.)
1. ተዳደረ. We have to manage very carefully on our small salary. ባነስተኛ ፡ ደሞዛችን ፡ በጥንቃቄ ፡ መተዳደር ፡ አለብን

2. ሊኖር ፡ ቻለ. How can you manage on that salary? በዚያ ፡ ደሞዝ ፡ እንዴት ፡ ልትኖር ፡ ትችላለህ ?
3. ኖረ. How will she manage with her husband gone? ባሏ ፡ ሄዶ ፡ እንዴት ፡ ትኖራለች ?

**manageable**
*We must begin while the task is still manageable. ሥራው ፡ ሊሠራ ፡ በሚችልበት ፡ ጊዜ ፡ አሁን ፡ መጀመር ፡ አለብን

**management**
1. አመራር. The management of the store is not very good. የመደብሩ ፡ አመራር ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ አይደለም
2. አስተዳዳሪዎች. Complain to the management! ላስተዳዳሪዎቹ ፡ አመልክት

**manager**
1. ሥራ ፡ አስኪያጅ. The manager left town. ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ ሄደ
2. አስተዳዳሪ. His wife is a good manager. ሚስቱ ፡ ጥሩ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ናት

**mandate**
1. የተጣለበት ፡ አደራ. Our mandate allows us to do all we can to develop the country. የተጣለብን ፡ አደራ ፡ ሀገሪቷን ፡ ለማበልጸግ ፡ የተቻለንን ፡ ሁሉ ፡ እንድናደርግ ፡ ይፈቅድልናል
2. በሞግዚትንት ፡ የማስተዳደር ፡ ኀላፊነት. The mandate over Syria was given to France. ሶሪያን ፡ በሞግዚትነት ፡ የማስተዳደር ፡ ኀላፊነት ፡ የተሰጠው ፡ ለፈረንሳይ ፡ ነበር

**mandated** በሞግዚት ፡ አስተዳደር ፡ ሥር ፡ የምትገኝ ፤ በሞግዚትነት ፡ የምትተዳደር
Southwest Africa was a mandated territory. ደቡብ ፡ ምዕራብ ፡ አፍሪካ ፡ በሞግዚት ፡ አስተዳደር ፡ ሥር ፡ የምትገኝ ፡ ግዛት ፡ ነበረች

**mandatory** ግዴታ
Taxes have been mandatory. ግብር ፡ መክፈል ፡ ግዴታ ፡ ነው

**mandatory power** የሞግዚትነት ፡ አስተዳደር ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው
A mandatory power is in charge of the mandated territory. የሞግዚትነት ፡ አስተዳደር ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ በሞግዚትነት ፡ ለሚተዳደረው ፡ ግዛት ፡ ኀላፊ ፡ ነው

**mane** ጋማ
Comb out the horse's mane! የፈረሱን ፡ ጋማ ፡ አበጥረው

**maneuver** (v.)
1. በዘዴ ፡ ሊያስገባ ፡ ቻለ. He maneuvered his car into a small space. መኪናውን ፡ በዘዴ ፡ ካንዲት ፡ ጠባብ ፡ ቦታ ፡ ሊያስገባ ፡ ቻለ
2. አንቀሳቀሰ. The admiral maneuvered his fleet into an attack position. አድሚራሉ ፡ ለማጥቃት ፡ እንደሚመች ፡ አድርጎ ፡ መርከቦቹን ፡ አንቀሳቀሰ
3. በዘዴ ፡ መራ. The chairman maneuvered the discussion to his own advantage. ሊቀመንበሩ ፡ ውይይቱን ፡ ለሱ ፡ እንደሚመቸው ፡ አድርጎ ፡ በዘዴ ፡ መራው
4. ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ. Their maneuvering at the conference was a play for time. በስብሰባው ፡ ጊዜ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ማለታቸው ፡ ጊዜ ፡ ለማግኘት ፡ ነው

**maneuver oneself** እንደምንም ፡ ተሹሎክልኮ ፡ ደረሰ
He is trying to maneuver himself into a higher position. እንደምንም ፡ ተሽሎክልኮ ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ ይሞክራል

**maneuver** (n.)
1. ልምምድ. The troops are on maneuvers now. አሁን ፡ ወታደሮቹ ፡ በልምምድ ፡ ላይ ፡ ናቸው
2. የብልጠት ፡ ዘዴ. When we refused to use his idea, he tried to force it on us by a series of maneuvers. የሱን ፡ ሐሳብ ፡ ሥራ ፡ ለማዋል ፡ እምቢ ፡ ብንል ፡ እንድንቀበለው ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የብልጠት ፡ ዘዴዎች ፡ ሊገፋፋን ፡ ሞከረ

**manger** ግርግም
They put oats in the manger. ግርግም ፡ ውስጥ ፡ አጃ ፡ አኖሩ

**mangle** ቀረጠፈ
A trap has mangled the rabbit's paw. ወጥመድ ፡ የጥንቸሏን ፡ መዳፍ ፡ ቀረጠፈው

**mango** ማንጎ

**manhandle** አንገላታ
The police manhandled the suspected murderer. በነፍስ ፡ ግዳይ ፡ የተጠረጠረውን ፡ ሰው ፡ ፖሊሶች ፡ አንገላቱት

**manhole** [ቆሻሻ ፡ መውረጃ ፡ ቦይ ፡ ውስጥ ፡ ለመግቢያ ፡ የሚያገለግል ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ባለ ፡ ክዳን ፡ ጉድጓድ]

**manhood**
1. አካለ ፡ መጠን. He has reached manhood. ላካለ ፡ መጠን ፡ ደርሷል
2. ወንድነት. Manhood is not acquired by

avoiding difficulty and hardship. ችግርና ፡ መከራን ፡ በመሸሽ ፡ ወንድነት ፡ አይገኝም

3. ወንዶች ፡ ሁሉ. The manhood of the nation answered the call to defend the country. አገሪቱን ፡ ከወራሪ ፡ ለመከላከል ፡ የተደረገውን ፡ ዐዋጅ ፡ ወንዶች ፡ ሁሉ ፡ ተቀበሉት

**mania, have a ~** ሻቀለ

She has a mania for new clothes. ላዲስ ፡ ልብስ ፡ ትሻቅላለች

**manifest** (v.)

1. ገለጸ. He manifested his joy by whistling. ደስታውን ፡ በፉጨት ፡ ገለጸ

2. ታየ(በት). +She does not manifest much of a desire to marry him. እሱን ፡ ለማግባት ፡ ብዙ ፡ ፍላጎት ፡ አይታይባትም

**manifest itself** ታወቀ

When did your illness manifest itself? በሽታህ ፡ የታወቀህ ፡ መቼ ፡ ነው ?

**manifest** (adj.) ግልጽ

This is something that should be manifest to all of you. ይህ ፡ ለሁላችሁም ፡ ግልጽ ፡ መሆን ፡ ያለበት ፡ ነገር ፡ ነው

**manifestation** መግለጫ

His whistling is a manifestation of joy. የሱ ፡ ፉጨት ፡ የደስታ ፡ መግለጫ ፡ ነው

**manifesto** መግለጫ

The students' manifesto demanded far-reaching reforms. የተማሪዎቹ ፡ መግለጫ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ መሻሻል ፡ እንዲደረግ ፡ ጠየቀ

**manifold**

1. ብዙ ፡ ዘርፍ ፡ ያለው. This manifold subject requires years of study to master. ብዙ ፡ ዘርፍ ፡ ያለውን ፡ ትምህርት ፡ አጠናቆ ፡ ለማወቅ ፡ የብዙ ፡ ዓመታት ፡ ጥናት ፡ ያስፈልጋል

2. ልዩ ፡ ልዩ. His manifold duties included editing a newspaper. ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ተግባሮቹ ፡ አንዱ ፡ ጋዜጣ ፡ ማዘጋጀት ፡ ነበር

**manipulate**

1. በእጅ ፡ አንቀሳቀሰ. He manipulated the controls of the car, but could not drive it. የመኪናውን ፡ መቈጣጠሪያዎች ፡ በእጅ ፡ ማንቀሳቀስ ፡ ችሏል ፡ ግን ፡ መንዳት ፡ አይችልም

2. አንቀሳቀሰ. Even though he is young, he manipulates the tractor well. ገና ፡ ወጣት ፡ ቢሆንም ፡ የእርሻ ፡ መኪናውን ፡ ጥሩ ፡ አድርጎ ፡ ያንቀሳቅሰዋል

3. እንደፈለገው ፡ አግባባ. A clever politician manipulates people to get his own way. ብልህ ፡ የፖለቲካ ፡ ሰው ፡ የሚፈልገውን ፡ ለማግኘት ፡ ሰዎችን ፡ እንደፈለገው ፡ ያግባባቸዋል

4. አማታ. The bookkeeper manipulated the company's accounts to conceal his theft. ሒሳብ ፡ ያዢው ፡ ስርቆቱን ፡ ለመደበቅ ፡ የኩባንያውን ፡ ሒሳብ ፡ አማታ

5. እንደልቡ ፡ አደረገ. He manipulated the pliant twig. ተለማጩን ፡ ቅርንጫፍ ፡ እንደልቡ ፡ ያደርገው ፡ ነበር

**mankind**

1. ሰው. Mankind was created by God in his image. ሰውን ፡ እግዚአብሔር ፡ በአምሳሉ ፡ ፈጠረው

2. የሰው ፡ ልጅ. Mankind has committed crimes against nature. የሰው ፡ ልጅ ፡ ተፈጥሮን ፡ በድሏል

3. ሰብአዊ ፡ ፍጡር. The desire for praise is a strong drive in mankind. ምስጋና ፡ መፈለግ ፡ በሰብአዊ ፡ ፍጡር ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ የሚገፋፋ ፡ ብርቱ ፡ ኀይል ፡ ነው

**manlike** ሰው ፡ የሚመስል

A manlike ape once lived in what is now Kenya. ሰው ፡ የሚመስል ፡ ዝንጀሮ ፡ አሁን ፡ ኬንያ ፡ በሚባለው ፡ አገር ፡ ይኖር ፡ ነበር

**manly**

1. ወንዳ ፡ ወንድ. He is a very manly boy for one so young. እንደሱ ፡ ያለ ፡ ወጣት ፡ ልጅ ፡ በጣም ፡ ወንዳ ፡ ወንድ ፡ ነው

2. የወንድ. Boxing is a manly sport. ቦክስ ፡ የወንድ ፡ ጨዋታ ፡ ነው

3. ጐበዝ. If you coddle your child, he won't grow up to be manly. ልጅህን ፡ ካሞላቀቅኸው ፡ ጐበዝ ፡ ሆኖ ፡ አያድግም

**man-made** ሰው ፡ ሠራሽ

Man-made objects were found in a cave. በዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ሰው ፡ ሠራሽ ፡ እቃዎች ፡ ተገኙ

**manner**

1. ጠባይ. I do not like his manner. ጠባዩን ፡ አልወደውም

2. ዓይነት. What manner of man is he? ምን ፡ ዓይነት ፡ ሰው ፡ ነው ?

3. ሁኔታ. He sang in an amusing manner. በሚያሥቅ ፡ ሁኔታ ፡ ዘመረ

4. ዘዴ. What is the best manner of peeling onions? ሽንኩርትን ፡ ለመላጥ ፡ ጥሩው ፡ ዘዴ ፡ ምንድነው ?

5. (noun of manner). His manner of dressing shows much care. አለባበሱ ፡ ብዙ ፡ ጥንቃቄ ፡ ማድረጉን ፡ ያሳያል

*These houses are built in the Mexican manner. እነዚህ ፡ ቤቶች ፡ የተሠሩት ፡ እንደ ፡ ሜክሲኮ ፡ ቤቶች ፡ ነው

**manners**
1. ልማድ. The manners of the ancient Romans are described in this book. የጥንት ፡ ሮማውያን ፡ ልማዶች ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ተገልጸዋል
2. ባህል. The literature of a nation reflects its manners. ያንድ ፡ አገር ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ያገሩን ፡ ባህል ፡ ይገልጻል
3. ጠባይ. He has good manners. ጥሩ ፡ ጠባይ ፡ አለው
4. ሥርዓት. After the guests left, the boy got a sermon on table manners from his father. እንግዶቹ ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ አባትየው ፡ ለልጁ ፡ ስለ ፡ ገበታ ፡ ሥርዓት ፡ ምክር ፡ ሰጠው
*She has no manners. ስድ ፡ ናት

**bad manners** ብልግና ፤ መጥፎ ፡ ምግባር
It is bad manners to stare at people. ሰውን ፡ አፍጥጦ ፡ ማየት ፡ ብልግና ፡ ነው
You shouldn't correct your children for their bad manners in public. ስለ ፡ መጥፎ ፡ ምግባራቸው ፡ ልጆችህን ፡ በአደባባይ ፡ መቅጣት ፡ አይገባህም
[See also 'decisive, ease, ill, proper, smooth']

**mannered**, see **ill-mannered, well-mannered**

**mannerism** ጠባይ
Each of us has his own mannerisms. እያንዳንዳችን ፡ የየግል ፡ ጠባይ ፡ አለን

**mannerly** ጨዋ
A mannerly child is a source of pride to his parents. ጨዋ ፡ ልጅ ፡ ለወላጆቹ ፡ መኩሪያ ፡ ነው

**mannerly way** ጨዋነት
He spoke in a mannerly way. በጨዋነት ፡ ተናገረ

**mannish** የወንድ
She has a mannish voice. ድምጿ ፡ የወንድ ፡ ድምፅ ፡ ነው

**man-of-war** (pl. men-of-war) የጦር ፡ መርከብ
Portuguese men-of-war appeared in the Red Sea in 1520. በ፲፭፻፳ ዓ. ም. የፖርቱጋል ፡ የጦር ፡ መርከቦች ፡ ቀይ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ታዩ

**manpower** ሰው
They need a lot of manpower to build new roads. አዲስ ፡ መንገድ ፡ ለመሥራት ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ያስፈልጋቸዋል
The army is short of manpower. ሰራዊቱ ፡ ሰው ፡ ያንሰዋል

**mansion** ትልቅ ፡ ቤት
He lives in a handsome mansion. በሚያምር ፡ ትልቅ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል

**manslaughter**
1. ሳያውቅ ፡ ሰው ፡ መግደል. He was convicted of manslaughter. ሳያውቅ ፡ ሰው ፡ በመግደል ፡ ተፈርዶበታል
2. ነፍስ ፡ ገዳይነት. The driver was proven innocent of manslaughter. ነጂው ፡ ከነፍስ ፡ ገዳይነት ፡ ንጹሕ ፡ መሆኑ ፡ ተረጋገጠ

**mantel** [ከእሳት ፡ ማንደጃ ፡ በላይ ፡ የሚገኝ ፡ መደርደሪያ]

**mantle** ካባ
The nobles wore silk mantles. መኳንንቱ ፡ የሐር ፡ ካባ ፡ ለብሰው ፡ ነበር

**manual** (n.) መምሪያ
I am writing a teacher's manual. የመምህራን ፡ መምሪያ ፡ እጽፋለሁ

**manual** (adj.)
1. የጉልበት ፤ የሞያተኛነት. He looks down on manual labor. የጉልበት ፡ (የሞያተኛነት) ፡ ሥራን ፡ ይንቃል
2. የእጅ. Using a loom requires manual skill. የሸማኔ ፡ እቃ ፡ የእጅ ፡ ሙያን ፡ የሚጠይቅ ፡ ነው

**manufacture** (v.)
1. ሠራ. They manufacture rifles and ammunition in this factory. በዚህ ፡ ፋብሪካ ፡ ውስጥ ፡ ጥይትና ፡ ጠመንጃ ፡ ይሠራሉ
2. ፈጠረ. The lazy boy manufactured excuses. ሰነፉ ፡ ልጅ ፡ ምክንያቶች ፡ ፈጠረ

**manufacture** (n.)
*The code on the label shows the date of manufacture. በንግድ ፡ እቃው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ልዩ ፡ ማስታወሻ ፡ እቃው ፡ የተሠራበትን ፡ ጊዜ ፡ ያመለክታል

**manufacturer** ባለፋብሪካ
Don't deal with middlemen; write directly to the manufacturer! ከትራፊ ፡ ጋር ፡ አትዋዋል ፤ ቀጥታ ፡ ለባለፋብሪካው ፡ ጻፍ

**manumission** አርነት ፡ ማውጣት
Manumission of slaves is an act of piety. ባሮችን ፡ አርነት ፡ ማውጣት ፡ የተቀደሰ ፡ ተግባር ፡ ነው

**manure** ፍግ
Manure is used by farmers to fertilize their fields. ገበሬዎች ፡ መሬታቸውን ፡ ለማዳበር ፡ በፍግ ፡ ይጠቀማሉ

**manuscript**
1. የብራና ፡ መጽሐፍ. I want to buy an Ethiopian manuscript. የኢትዮጵያ ፡ የብራና ፡ መጽሐፍ ፡ ለመግዛት ፡ እፈልጋለሁ
2. የእጅ ፡ ጽሑፍ. This is the earliest extant manuscript. ይህ ፡ የእጅ ፡ ጽሑፍ ፡ ከጥንቶቹ ፡ ሁሉ ፡ የሚቀድም ፡ ነው

**many** ብዙ
I have many books. ብዙ ፡ መጽሐፍ ፡ አለኝ

**many a** ብዙ
Many a man owes his success to his wife. ብዙ ፡ ሰው ፡ በሚስቱ ፡ ምክንያት ፡ ሥራው ፡ ይቃናለታል
I have passed here many a time. በዚህ ፡ በኩል ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አልፌያለሁ

**many of-** ብዙዎች + suffix pronouns
Many of us left early. ብዙዎቻችን ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ ሄድን

**a great many** ብዙ
A great many books have been written on that subject. በዚህ ፡ አርእስት ፡ ብዙ ፡ መጽሐፎች ፡ ተጽፈዋል

**in as many** የዚያኑ ፡ ያህል
You made ten spelling errors in as many lines. ዐሥር ፡ መሥመር ፡ ጽፈህ ፡ የዚያኑ ፡ ያህል ፡ የፊደል ፡ ስሕተት ፡ አድርገሃል

**one too many**
*I feel that I am one too many in this company. በዚህ ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ መገኘቴ ፡ የተፈለገ ፡ አይመስለኝም

**so many**
1. በጣም ፡ ብዙ. So many people have failed to pay attention to the warning! በጣም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ማስጠንቀቂያውን ፡ ከምንም ፡ ሳይቈጥሩት ፡ ቀሩ
2. ይህን ፡ ያህል. Do you need so many? ይህን ፡ ያህል ፡ ያስፈልግሃል ?

**too many**
1. አብልጦ. You gave me three too many. ሦስት ፡ አብልጠህ ፡ ሰጠኸኝ
2. ብዙ. A student who has too many activities does not have time to study. ብዙ ፡ ተግባሮች ፡ የሚያከናውን ፡ ተማሪ ፡ ለጥናት ፡ ጊዜ ፡ የለውም

**map** (mapped), v. ካርታ ፡ አነሣ
This scholar mapped Western America. ይህ ፡ ምሁር ፡ ምዕራብ ፡ አሜሪካን ፡ ካርታ ፡ አነሣ

**map out**
1. በንድፍ ፡ አወጣ. The general mapped out the campaign. ጀኔራሉ ፡ የዘመቻውን ፡ ስልት ፡ በንድፍ ፡ አወጣ
2. ወሰነ. Have you mapped out your route yet? የጉዞህን ፡ አቅጣጫ ፡ ወስነሃል ?
3. ደረጃ ፡ በደረጃ ፡ አወጣ. The students mapped out the week's tasks. ተማሪዎቹ ፡ የሳምንቱን ፡ ሥራ ፡ ደረጃ ፡ በደረጃ ፡ አወጡት

**map** (n.) ካርታ
He is making a map of Sidamo province. የሲዳሞን ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ካርታ ፡ እየሠራ ፡ ነው

**put on the map** የታወቀ ፡ አደረገ
The discovery of gold put our town on the map. በከተማችን ፡ ውስጥ ፡ ወርቅ ፡ መገኘቱ ፡ የታወቀች ፡ አደረጋት

**mar** (marred) አወከ
Nothing marred the happiness of our outing. በሽርሽራችን ፡ ጊዜ ፡ የነበረንን ፡ ደስታ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አላወከውም

**be marred**
1. ተበላሸ. The painting was marred by cracks. ሥዕሉ ፡ በመቀዳደዱ ፡ ተበላሽቶ ፡ ነበር
2. ተሟጨረ I ተቧጨረ. This table has been marred by knife marks. ይህ ፡ ጠረጴዛ ፡ በስንጢ ፡ ተሟጭሯል ፡ (ተቧጭሯል)

**maraud** ወረረ
The gang marauded over the countryside. ወንበዴዎቹ ፡ ገጠሩን ፡ ወረሩት
*A fox marauded the chicken coop. ቀበሮ ፡ ከዶሮው ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ዶሮዎች ፡ በላ

**marauder** ወንበዴ
The marauders pillaged the house and then set it on fire. ወንበዴዎቹ ፡ ቤቱን ፡ ከዘረፉ ፡ በኋላ ፡ እሳት ፡ለኰሱበት

**marble** እብነ ፡ በረድ
The statue is made of marble. ሐውልቱ ፡ የተሠራው ፡ ከእብነ ፡ በረድ ፡ ነው

**marbles** ብይ
Boys like to play marbles. ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ብይ ፡ መጫወት ፡ ይወዳሉ

**march** (v.)
1. ተሰለፈ ፡ ተጓዘ. He drums when the soldiers march. ወታደሮቹ ፡ ተሰልፈው ፡ ሲጓዙ ፡ ታምቡር ፡ ይመታል
2. በሰልፍ ፡ ሄደ. Did you see the soldiers marching? ወታደሮቹ ፡ በሰልፍ ፡ ሲሄዱ ፡ አየህ ?

**march (someone) off** ወሰደ
The policeman marched the thief off to jail. ፖሊሱ ፡ ሌባውን ፡ ወደ ፡ እስር ፡ ቤት ፡ ወሰደው

**march on**
Time marches on. ጊዜው ፡ ይነጕዳል

**march through** አቋርጦ ፡ ሄደ
The soldiers marched through the desert to the front. ወታደሮቹ ፡ በረሃውን ፡ አቋርጠው ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ሄዱ

**march up and down** ላይና ፡ ታች ፡ አለ
He marched impatiently up and down outside the doctor's office. ከሐኪሙ ፡ ቢሮ ፡ ውጭ ፡ ያለ ፡ ትዕግሥት ፡ ላይና ፡ ታች ፡ ይል ፡ ነበር
[See also 'doom, head, step']

## march (n.)
1. ጕዞ. We still have a long march ahead of us. ገና ፡ ረጅም ፡ ጕዞ ፡ ይቀረናል
2. ማርሽ. The band began with a march. የሙዚቀኞቹ ፡ ጓድ ፡ በማርሽ ፡ ጀመረ

**march of events** ከጊዜ ፡ ወደጊዜ ፡ የሚደረጉ ፡ ነገሮች
The march of events shows us that life is getting more complicated. ከጊዜ ፡ ወደጊዜ ፡ የሚደረጉት ፡ ነገሮች ፡ ኑሮ ፡ እየተወሳሰበ ፡ መሄዱን ፡ ያሳዩናል

**forward march** ግስጋሴ
Their forward march was blocked by a river. የነርሱ ፡ ግስጋሴ ፡ ባንድ ፡ ወንዝ ፡ ታግዶ ፡ ነበር

## March መጋቢት
It rains in March. በመጋቢት ፡ ይዘንባል

## mare ባዝራ
He kept two mares in the stall. ጋጣው ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ባዝራ ፡ አሰረ

## margin
1. ኅዳግ. Leave a wider margin on the left side! በግራ ፡ በኩል ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ኅዳግ ፡ አስቀር
2. ዳርቻ. The margin of the lake is overgrown with reeds. የባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ በቄጠማ ፡ ተውጧል

**by a narrow margin** ለጥቂት
He escaped defeat by a narrow margin. ለጥቂት ፡ ከመሸነፍ ፡ ዳነ

## marginal
1. በኅዳጉ ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈ. A marginal note explains that the book was printed in 1910. በኅዳጉ ፡ ውስጥ ፡ የተጻፈው ፡ ማስታወሻ ፡ መጽሐፉ ፡ በ፲፱፻፪ ዓ. ም. መታተሙን ፡ ይገልጻል
2. (= adv.) እንደምንም ፡ ብሎ. The crops in that region are adequate for marginal subsistence. በዚያ ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ ያለው ፡ እህል ፡ እንደምንም ፡ ብሎ ፡ ለመኖሪያ ፡ ያህል ፡ ይበቃል

**be marginal** አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ አይደለም
This is marginal; we need not consider it in our plans. ይህ ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ አይደለም ፤ በእቅዳችን ፡ ውስጥ ፡ ልናስገባው ፡ አያስፈልግም

## marinate በቅመም ፡ ዘፈዘፈ
Marinate the meat to make it more tender! ሥጋውን ፡ ይበልጥ ፡ ለማለስለስ ፡ በቅመም ፡ ዘፍዝፈው

## marine (n.) መርከቦች
Ethiopia has a small merchant marine. ኢትዮጵያ ፡ ጥቂት ፡ የንግድ ፡ መርከቦች ፡ አሏት

## marine (adj.)
1. የባሕር. Whales are marine animals. ዓሣ ፡ ነባሪዎች ፡ የባሕር ፡ እንስሶች ፡ ናቸው
Marine insurance protects cargo ships. የባሕር ፡ ዋስትና ፡ ለጭነት ፡ መርከቦች ፡ ዋስትና ፡ ይሰጣል
2. ከባሕር ፡ የሚገኝ. Marine products are sold in Massawa. ምፅዋ ፡ ከባሕር ፡ የሚገኙ ፡ ሸቀጦች ፡ ይሸጣሉ

## marital
1. የባል. Providing for one's wife is a marital obligation. ሚስት ፡ የሚያስፈልጋትን ፡ ሁሉ ፡ እንድታገኝ ፡ ማድረግ ፡ የባል ፡ ኀላፊነት ፡ ነው
2. የጋብቻ. A man and a woman take marital vows when they marry. ወንድና ፡ ሴት ፡ ሲጋቡ ፡ የጋብቻ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይፈጽማሉ

## maritime
1. የባሕር ፡ ላይ. Maritime commerce was harmed when the Suez canal was closed. የሱዌዝ ፡ ቦይ ፡ በመዘጋቱ ፡ የባሕር ፡ ላይ ፡ ንግድ ፡ ተጐዳ
2. የባሕር ፡ አዋሳኝ. Eritrea is Ethiopia's maritime province. ኤርትራ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የባሕር ፡ አዋሳኝ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ናት
3. የባሕር. He studies maritime law. የባሕር ፡ ሕግ ፡ ያጠናል

## mark (vt.)
1. ምልክት ፡ አደረገ(በት). I have marked the important parts of the article. የጽሑፉን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ምልክት ፡ አድርጌበታለሁ
Have you marked your laundry? የሚታጠበውን ፡ ልብስህን ፡ ምልክት ፡ አድርገህበታል ?
2. አረመ. When will you mark our examination papers? የፈተና ፡ ወረቀታችንን ፡ መቼ ፡ ታርማለህ ?

3. አመለከተ. His answers mark him as a good student. የሚሰጣቸው ፡ መልሶች ፡ ጥሩ ፡ ተማሪ ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታሉ
He marked the enemy position on a chart. ጠላት ፡ ያለበትን ፡ ሰፍራ ፡ በካርታ ፡ ላይ ፡ አ
መለከተ
4. ገለጸ. He marked his satisfaction with a smile. ደስታውን ፡ በፈገግታ ፡ ገለጸ
5. የተለየ ፡ አደረገ. Many important inventions mark the last hundred years. ብዙ ፡ ታላላቅ ፡ ፍ
ልሰፋዎች ፡ ያለፉትን ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ የተለ
ዩ ፡ ያደርጓቸዋል
6. ልብ ፡ አለ. You had better mark my warning! ማስጠንቀቂያዬን ፡ ልብ ፡ ብትል ፡ ይሻላል
7. ሞጫጨረ. Be careful not to mark the table! ጠረጴዛውን ፡ እንዳትሞጫጭር ፡ ተጠንቀቅ
8. (= pass.) ታወቀ. +A frown marked her displeasure. አለመደሰቷ ፡ ፊቷን ፡ ከመቋጠሯ ፡ ታወቀ

**mark** (vi.) አስተዋለ
Mark how carefully he moves! እንዴት ፡ በጥን
ቃቄ ፡ እንደሚራመድ ፡ አስተውል

**be marked**
1. ታወቀ. His face was marked by years of hard work. ጊዜውን ፡ በከባድ ፡ ሥራ ፡ ያሳለፈ ፡ መሆኑ ፡ በፊቱ ፡ ይታወቃል
2. ጠቀጠቀ. +His face is marked by smallpox. ፊቱን ፡ ፈንጣጣ ፡ ጠቅጥቆታል
3. ተመለከተ. The borderline is not marked on the map. ድንበሩ ፡ በካርታው ፡ ላይ ፡ አልተመ
ለከተም

**mark down**
1. ጻፈ. I have marked down the things I want. የምፈልጋቸውን ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ ጽፌያቸዋለሁ
Mark down the address! አድራሻውን ፡ ጻፍ
2. ዋጋ ፡ ዝቅ ፡ አደረገ. The store marked down the coats from seventy to fifty dollars. መደብ
ሩ ፡ የኮቱን ፡ ዋጋ ፡ ከሰባ ፡ ወደ ፡ አምሳ ፡ ብር ፡ ዝቅ ፡ አደረገ

**(be) marked for** ተደገሰ(ለት)
+The informer is marked for death. ጆሮ ፡ ጠቢ
ው ፡ ሞት ፡ ተደግሶለታል

**mark off** በምልክት ፡ ለየ
He marked off the distance on the map. ርቀቱን ፡ በካርታው ፡ ላይ ፡ በምልክት ፡ ለየ

**mark out** አሠመረ
We marked out a tennis court. የቴኒሱን ፡ ሜ
ዳ ፡ አሠመርን

**mark up**
1. ጨመረ. The store marked up the prices ten per cent. መደብሩ ፡ ዋጋዎቹን ፡ በሥር ፡ በመቶ ፡ ጨመረ
2. ሞጫጨረ. Don't mark up the desk! ጠረጴዛ
ውን ፡ አትሞጫጭር
[See also ' time, word']

**mark** (n.)
1. ምልክት. Make a mark after the names of those present! ባሉት ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ አንጻር ፡ ም
ልክት ፡ አድርግ
His face shows the marks of old age. ፊቱ ፡ ላ
ይ ፡ የእርጅና ፡ ምልክት ፡ ይታይበታል
The wet glass left a mark on the table. እርጥ
ቡ ፡ ብርጭቆ ፡ ጠረጴዛው ፡ ላይ ፡ ምልክት ፡ ተወ
2. ውጤት. He always got good marks in mathematics. እርሱ ፡ ሁልጊዜ ፡ በሒሳብ ፡ ጥ
ሩ ፡ ውጤት ፡ ያገኝ ፡ ነበር
3. ዒላማ. He hit the mark with his first arrow. በመጀመሪያው ፡ ቀስት ፡ ዒላማውን ፡ መታ
4. ዘላቂ ፡ የሆነ ፡ መታሰቢያነት. Theodore left his mark on Ethiopia. ቴዎድሮስ ፡ በኢትዮጵ
ያ ፡ ውስጥ ፡ ዘላቂ ፡ የሆነ ፡ መታሰቢያነትን ፡ ትተዋል
5. የተወሰነ ፡ ደረጃ. His dissertation was below the mark. ጽሑፉ ፡ ከተወሰነው ፡ ደረጃ ፡ ዝቅ ፡ ያለ ፡ ነበር
6. መግለጫ. Remove the price mark from your new suit! ካዲሱ ፡ ልብስህ ፡ ላይ ፡ የዋጋውን ፡ መ
ግለጫ ፡ ገንጥል
*Standing there, the lion was an easy mark. እዚያ ፡ እንደቆመ ፡ አንበሳው ፡ በቀላሉ ፡ ሊመታ ፡ ይችል ፡ ነበር

**as a mark of** የሚገልጽ
Accept this gift as a mark of my esteem! ይህን ፡ አክብሮቴን ፡ የሚገልጽ ፡ ስጦታ ፡ ተቀበለኝ

**(be) beside the mark** ከጉዳዩ ፡ ውጭ ፡ ነበር
The answers given by the witness were beside the mark. ምስክሩ ፡ የሰጣቸው ፡ መልሶች ፡ ከ
ጉዳዩ ፡ ውጭ ፡ ነበሩ

**get black-and-blue marks**
Where did you get those black-and-blue marks? ሰውነትህን ፡ ምን ፡ አበለዘው ?

**make (one's) mark** ዝናን ፡ አተረፈ
He made his mark in the world. በዓለም ፡ ላይ ፡ ዝናን ፡ አተረፈ

**make dirty marks on** አቆሸሸ
Who made these dirty marks on my new book? አዲሱን ፡ መጽሐፌን ፡ ማን ፡ አቆሸሸው ?

**man of mark** ዝነኛ
His uncle is a man of mark. አጎቱ ፡ ዝነኛ ፡ ናቸው

**not feel up to the mark** እንደ ፡ ወትሮው ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም
A tired person does not feel up to the mark. የደከመው ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ወትሮው ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም

**(be) off the mark** ልክ ፡ አይደለም
His opinion is off the mark. አስተያየቱ ፡ ልክ ፡ አይደለም
[See also 'identification, passing, punctuation']

## marked

1. ጉልህ. There is a marked difference between the two brothers. በሁለቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ መካከል ፡ ጉልህ ፡ የሆነ ፡ ልዩነት ፡ አለ
2. ምልክት ፡ የተደረገበት. Did you read the marked passage? ምልክት ፡ የተደረገበትን ፡ ምን ባብ ፡ አንብበሃል ?
3. ተጠርጣሪ. He was a marked man once his revolutionary past became known. ቀድሞ ፡ ደመ ፡ ነውጥ ፡ እንደነበረ ፡ ከታወቀ ፡ በኋላ ፡ ተጠርጣሪ ፡ ሰው ፡ ሆነ

## markedly በጣም

He has markedly improved. በጣም ፡ ተሻሽሏል

## marker ምልክት

The marker for the exact spot where Theodore died was made of bronze. ቴዎድሮስ ፡ የሞቱበትን ፡ ትክክለኛ ፡ ስፍራ ፡ የሚያሳየው ፡ ምልክት ፡ ከነሐስ ፡ የተሠራ ፡ ነው

## market (vt.)

1. ሸጠ. The farmers market their grain through cooperatives. ገበሬዎቹ ፡ እህላቸውን ፡ በኅብረት ፡ ድርጅት ፡ በኩል ፡ ይሸጣሉ
2. (= intr.) ለገበያ ፡ ቀረበ. My invention needs a few refinements before we market it. የፈለሰፍኩት ፡ ለገበያ ፡ ከመቅረቡ ፡ በፊት ፡ አንዳንድ ፡ መሻሻል ፡ ያስፈልገዋል

## market (n.) ገበያ

Everything is cheaper at the market. እገበያ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ረከስ ፡ ይላል
How is the coffee market today? ዛሬ ፡ የቡና ፡ ገበያ ፡ እንዴት ፡ ነው ?
The market is under way. ገበያው ፡ ቆመ
The market is in full swing in the afternoon. ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ገበያው ፡ ይደራል
The market is over. ገበያው ፡ ተበተነ

**be in the market for** ለመግዛት ፡ ፈለገ
Are you in the market for a good car? ጥሩ ፡ መኪና ፡ ለመግዛት ፡ ትፈልጋለህ ?

**be off the market** ከገበያ ፡ ጠፋ
That item has been off the market for a year. ያ ፡ እቃ ፡ ላንድ ፡ ዓመት ፡ ከገበያ ፡ ጠፍቷል

**be on the market** ገበያ ፡ ዋለ
Fresh vegetables will be on the market this week. ያልዋለ ፡ ያላደረ ፡ አትክልት ፡ በዚህ ፡ ሳምንት ፡ ውስጥ ፡ ገበያ ፡ ይውላል

**be put on the market** ገበያ ፡ ወጣ
This toothpaste has been put on the market only recently. ይህ ፡ የጥርስ ፡ ሳሙና ፡ ገበያ ፡ የወጣው ፡ ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ነው

**there is a market for**
*There is a big market for warm clothing during the winter. ገበያ ፡ ውስጥ ፡ በክረምት ፡ ሞቃት ፡ የሆኑ ፡ ልብሶች ፡ ይነግሉ

**there is no market for** ፈላጊ ፡ የለውም
There is no market here for these typewriters. እዚህ ፡ ለነዚህ ፡ የጽሕፈት ፡ መኪናዎች ፡ ፈላጊ ፡ የላቸውም

## (be) marketable ገዢ ፡ አገኘ

His invention is marketable. እሱ ፡ የፈለሰፈው ፡ ነገር ፡ ገዢ ፡ ያገኛል

## marketing, do ~ ገበየ

She does her marketing in the morning. ጧት ፡ ጧት ፡ ትገበያለች

## marketplace ገበያ

He went to the marketplace to see how the goods were selling. እቃዎቹ ፡ እንዴት ፡ እንደሚሸጡ ፡ ለማየት ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ ሄደ

## marksman አነጣጣሪ

Since the hunter was a good marksman, the bullet did not hit the ground. አዳኙ ፡ ጥሩ ፡ አነጣጣሪ ፡ ስለሆነ ፡ ጥይቱ ፡ መሬት ፡ አልወደቀም

## marmalade ማርመላታ

## maroon (v.) ያለ ፡ መመለሻ ፡ አስቀረ ፤ ያለ ፡ መመለሻ ፡ ለቀቀ

The loss of our boat marooned us. የጀልባችን ፡ መጥፋት ፡ ያለ ፡ መመለሻ ፡ አስቀረን
Pirates used to maroon people on desert islands. የባሕር ፡ ሽፍቶች ፡ ሰዎችን ፡ በረሃማ ፡ በሆኑ ፡ ደሴቶች ፡ ላይ ፡ እየወሰዱ ፡ ያለ ፡ መመለሻ ፡ ይለቋቸው ፡ ነበር

## maroon (n.) [ሸክላ ፡ ዓይነት ፡ ቀለም]

## marriage

1. ጋብቻ. His marriage was considered a disgrace for the family. የሱ ፡ ጋብቻ ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ እንደ ፡ ኀፍረት ፡ ተቈጠረ

We wished the bride and groom a happy marriage. ለሙሽሪቷና ፡ ለሙሽራው ፡ የደስታ ፡ ጋብቻ ፡ እንዲሆንላቸው ፡ ተመኘንላቸው

2. ትዳር. Her career is more important to her than her marriage. ለርሷ ፡ ከትዳሯ ፡ ይልቅ ፡ ሥራዋ ፡ ይበልጥባታል

3. ማግባት. Before her marriage, she worked in an office. ከማግባቷ ፡ በፊት ፡ ቢሮ ፡ ውስጥ ፡ ትሠራ ፡ ነበር

**arrange marriages**

*Arranging marriages for one's children is outmoded. የወላጆች ፡ ለልጆች ፡ የኑሮ ፡ ጓደኛ ፡ መምረጥ ፡ ድሮ ፡ ቀርቷል

**civil marriage** የብሔራዊ ፡ ጋብቻ ፡ ሥርዓት

They had a civil marriage. የተጋቡት ፡ በብሔራዊ ፡ ጋብቻ ፡ ሥርዓት ፡ ነው

**(from her) first marriage** ከመጀመሪያ ፡ ባሏ

She has a daughter from her first marriage. ከመጀመሪያ ፡ ባሏ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ወልዳለች

**give in marriage** ዳረ

He gave his daughter in marriage to a minister's son. ልጇን ፡ ለሚኒስትር ፡ ልጅ ፡ ዳረ

[See also 'propose, service']

## marriageable ለትዳር ፡ የደረሰ

He has two marriageable daughters. ሁለት ፡ ለትዳር ፡ የደረሱ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ አሉት

## married (adj.) ያገባ ፤ የተዳረች

He is a married man. እሱ ፡ ያገባ ፡ ሰው ፡ ነው

She is a married woman. እሷ ፡ ያገባች ፡ ሴት ፡ ናት

The adventurer looked for an unmarried girl whose father was rich. ሙሌው ፡ ያልተዳረች ፡ የባለጸጋ ፡ ልጅ ፡ ፈለገ

**married couple** ባለትዳር

This house is only for married couples. ይህ ፡ ቤት ፡ ለባለትዳር ፡ ብቻ ፡ ነው

**married life** ትዳር

Married life changed many of his previous habits. ትዳር ፡ ብዙውን ፡ የድሮ ፡ ልማዱን ፡ ለወጠው

## marrow ቅልጥም

The marrow is taken from the bones and eaten. ቅልጥም ፡ ካጥንት ፡ ውስጥ ፡ ወጥቶ ፡ ይበላል

## marry (married), vt.

1. አገባ. Is she going to marry him? ልታገባው ፡ ነው ?

Is he going to marry her? ሊያገባት ፡ ነው ?

2. ዳረ. He married his youngest daughter to a writer. ትንሿን ፡ ልጁን ፡ ለደራሲ ፡ ዳራት

3. አጋባ. The patriarch is going to marry them. ፓትሪያርኩ ፡ ሊያጋባቸው ፡ ነው

**marry** (vi.)

1. አገባ. He married late in life. በዕድሜው ፡ ከጠና ፡ በኋላ ፡ አገባ

2. ባል ፡ አገባች. She married late in life. ባል ፡ ያገባችው ፡ በዕድሜ ፡ ከጠናች ፡ በኋላ ፡ ነው

**marry off** ዳረ

He has married off all his daughters. ሴት ፡ ልጆቹን ፡ ሁሉ ፡ ድሯል

**be married**

1. አገባ. Were you married in church? ያገባኸው ፡ በተክሊል ፡ ነው ?

2. ተጋቡ. They've been married over a year. ከተጋቡ ፡ ዓመት ፡ አልፏቸዋል

**get married** አገባ

When is he getting married? መቼ ፡ ነው ፡ የሚያገባው ?

When is she getting married? እሷ ፡ የምታገባው ፡ መቼ ፡ ነው ?

## marsh ረግረግ

They are draining the marsh to build houses on. ቤት ፡ ለመሥራት ፡ ረግረጉን ፡ እያደረቁ ፡ ናቸው

## marshal (v.)

1. አዘጋጀ. He took great care in marshaling his facts for the court. ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚቀርበውን ፡ በትልቅ ፡ ጥንቃቄ ፡ አዘጋጀ

2. መራ. The host marshaled them into the room. ባለቤቱ ፡ ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ መራቸው

**be marshaled** በክብር ፡ ተወሰደ

The foreign visitor was marshaled into the presence of the Emperor. የውጭ ፡ አገሩ ፡ እንግዳ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ወዳሉበት ፡ በክብር ፡ ተወሰደ

## marshal (n.) [በጦር ፡ ሰራዊት ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ባለሥልጣን]

## marshland ረግረግ ፡ ስፍራ

This marshland is a breeding ground for mosquitoes. ይህ ፡ ረግረግ ፡ ስፍራ ፡ የወባ ፡ ትንኝ ፡ መርቢያ ፡ ነው

## marshy ረግረግ

Marshy land shelters many small animals. ረግረግ ፡ መሬት ፡ ብዙ ፡ ትንንሽ ፡ እንስሳትን ፡ ያኖራል

## martial

1. የጀግንነት. The Ethiopian patriots showed

their martial spirit in battle. የኢትዮጵያ ፡ አርበኞች ፡ የጀግንነት ፡ ስሜታቸውን ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ አሳዩ
2. ማርሽ. He likes martial music. ማርሽ ፡ ሙዚቃ ፡ ይወዳል

**martial law** ወታደራዊ ፡ ሕግ
The governor declared martial law. ገዢው ፡ ወታደራዊ ፡ ሕግ ፡ ዐወጀ

**martyr** ሰማዕት (pl. ሰማዕታት)
The church honors all martyrs. ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰማዕታትን ፡ ሁሉ ፡ ታከብራለች

**martyrdom** ሰማዕትነት
The martyrdom of St. John the Baptist is the subject of a new play. የመጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፡ ሰማዕትነት ፡ ያዲስ ፡ ቲያትር ፡ አርእስት ፡ ነው

**martyrize** አሠቃየ
The ancient Romans martyrized many Christians. የጥንት ፡ ሮማውያን ፡ ብዙ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ አሠቃዩ

**martyrize oneself**
He sought to martyrize himself. ሰማዕት ፡ ለመሆን ፡ ሞከረ

**marvel** (v.) ተደነቀ
I marvel that you were able to succeed under these difficult conditions. በዚህ ፡ ከባድ ፡ ሁኔታ ፡ መካከል ፡ ስለተሳካልህ ፡ እደነቃለሁ

**marvel at** አደነቀ
He marveled at her skill in typing. የመኪና ፡ ጽሕፈት ፡ ቅልጥፍናዋን ፡ አደነቀ

**marvel** (n.)
1. ታምር. The marvels of modern science are amazing. የዘመናዊ ፡ ሳይንስ ፡ ታምር ፡ ያስገርማል
These pills work marvels. እነዚህ ፡ ኪኒኖች ፡ ታምር ፡ ይሠራሉ
2. ምሳሌ. Your room is a marvel of neatness and order. ክፍልህ ፡ የንጽሕናና ፡ የሥርዓት ፡ ምሳሌ ፡ ነው

**marvelous** ግሩም
This is a marvelous cake. ይህ ፡ ግሩም ፡ ኬክ ፡ ነው

**masculine** (n.) ተባዕታይ ፡ ጾታ
The masculine does not have a special marker in Amharic. ባማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተባዕታይ ፡ ጾታ ፡ ልዩ ፡ ምልክት ፡ የለውም

**masculine** (adj.)
1. የወንድ. Football is a masculine sport. የእግር ፡ ኳስ ፡ የወንድ ፡ ጨዋታ ፡ ነው
2. ተባዕታይ. "He" is a masculine pronoun. « እሱ » ፡ ተባዕታይ ፡ ተውላጠ ፡ ስም ፡ ነው

**masculine gender,** see **gender**

**mash** (v.)
1. አደቀቀ. A rock fell on his foot and mashed it. ድንጋይ ፡ እግሩ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ አደቀቀው
The elephant's heavy feet mashed the grass. ዝሆኑ ፡ በከባድ ፡ እግሮቹ ፡ ሣሩን ፡ አደቀቀው
2. ፈጨ. I just have to mash the potatoes. ገና ፡ ድንቹን ፡ መፍጨት ፡ አለብኝ
3. ለነቀጠ. They mashed the chickpeas to make stew. ወጥ ፡ ለመሥራት ፡ ሽንብራውን ፡ ለነቀጡት

**mash** (n.) ቅልቅል
The baby ate a mash of bananas and water. ሕፃኑ ፡ የሙዝና ፡ የውኃ ፡ ቅልቅል ፡ በላ

**mask** (v.)
1. ደበቀ. He masked his anger behind a smile. ብስጭቱን ፡ በፈገግታ ፡ ደበቀው
2. እንዳይታወቅ ፡ ሸፈነ. The robber masked his face. ቀማኛው ፡ እንዳይታወቅ ፡ ፊቱን ፡ ሸፈነ

**mask** (n.) መደበቂያ
The robber wore a mask over his face. ቀማኛው ፡ ፊቱን ፡ በመደበቂያ ፡ ሸፍኖ ፡ ነበር
*His smile was a mask to hide his disappointment. ፈገግታው ፡ ቅሬታውን ፡ ለመደበቅ ፡ የተደረገ ፡ ነበር

**mason** ግንበኛ
The mason will build the wall. ግንበኛው ፡ ግድግዳውን ፡ ይገነባል

**masonry** የግንበኛነት ፡ ሥራ
He is an apprentice in masonry. እሱ ፡ በግንበኛነት ፡ ሥራ ፡ ተለማማጅ ፡ ነው

**mass** (vt.) አንድነት ፡ ሰበሰበ
The general massed his troops for an attack. ጄኔራሉ ፡ ወታደሮቹን ፡ ለውጊያ ፡ አንድነት ፡ ሰበሰበ

**mass** (vi.) ተሰበሰበ ፤ በብዛት ፡ ተሰበሰበ
Crowds were massing in the square. ባደባባዩ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ተሰብስቦ ፡ ነበር
The troops massed for an attack. ወታደሮቹ ፡ ለማጥቃት ፡ በብዛት ፡ ተሰበሰቡ

**mass** (n.)
1. ክምር. A large mass of feathers will be light

in weight. ትልቅ ፡ የላባ ፡ ክምር ፡ ክብደቱ ፡
ቀላል ፡ ነው
2. ግዙፍነት. He couldn't move the piano
because of its mass. ከግዙፍነቱ ፡ የተነሣ ፡ ፒያ
ኖውን ፡ ሊያንቀሳቅሰው ፡ አልቻለም
3. (= adv.) በብዛት. Mass meetings are forbidden unless a permit is obtained from the
police. ከፖሊስ ፡ ፈቃድ ፡ ካልተሰጠ ፡ በስተቀ
ር ፡ በብዛት ፡ መሰብሰብ ፡ ክልክል ፡ ነው
Mass production results in lower costs.
እቃን ፡ በብዛት ፡ መሥራት ፡ የመሥሪያ ፡ ዋጋውን ፡
ይቀንሳል
*The mass of opinion is against the plan.
የአብዛኛው ፡ ሰው ፡ አስተሳሰብ ፡ እቅዱን ፡ የሚ
ቃወም ፡ ነው
*The car is buried under a mass of mud.
መኪናዋ ፡ ማጥ ፡ ውስጥ ፡ ተቀበረች

**masses** ተራ ፡ ሕዝብ
The masses are illiterate. ተራው ፡ ሕዝብ ፡ መ
ሀይም ፡ ነው

**in the mass** በጠቅላላው
The valley, in the mass, is extremely fertile.
ሸለቆው ፡ በጠቅላላው ፡ በጣም ፡ ለም ፡ ነው

## Mass ቅዳሴ
Mass begins at 7 o'clock. ቅዳሴ ፡ የሚገባው ፡
ከጧት ፡ ባንድ ፡ ሰዓት ፡ ነው

**celebrate Mass** ቅዳሴ ፡ ገባ
The priests are celebrating Mass now. ቄሶቹ ፡
ቅዳሴ ፡ ገብተዋል

**go to Mass**
She went to Mass. ልታስቀድስ ፡ ሄደች
[See also 'sing']

## massacre (v.)
1. ገደለ. The soldiers looted and massacred
for three weeks. ወታደሮቹ ፡ ለሦስት ፡ ሳምን
ታት ፡ ሲዘርፉና ፡ ሲገድሉ ፡ ቆዩ
2. ፈጀ. The enemy massacred the wounded.
ጠላት ፡ ቁስለኞቹን ፡ ፈጃቸው

## massacre (n.)
1. እልቂት. At Siddist Kilo there is a memorial to the Yekatit massacre. ስድስት ፡ ኪሎ ፡
ላይ ፡ ለየካቲት ፡ እልቂት ፡ የቆመ ፡ መታሰቢያ ፡ ሐ
ውልት ፡ አለ
2. ፍጅት. The malign rule of the tyrant caused
revolts and massacres. የጨቋኙ ፡ የጭካኔ ፡ አገዛ
ዝ ፡ ሁከትና ፡ ፍጅት ፡ አስከተለ

## massage (v.) አሸ
He massaged his cold fingers. ብርድ ፡ የመታ
ቸውን ፡ ጣቶቹን ፡ አሸ

## massage (n.) መታሸት
How much does a massage cost? ለመታሸት ፡
ምን ፡ ያህል ፡ ይከፈላል ?

**get a massage** ታሸ
I'm going to get a massage to help my aching
back. የሚያመኝን ፡ ጀርባዬን ፡ እንዲሻለኝ ፡ እታ
ሻለሁ

## massive
1. ግዙፍ. He was locked in by a massive door.
ግዙፍ ፡ መዝጊያ ፡ ተዘጋበት
2. ብዙ. Massive evidence showed that the
president was the embezzler. ፕሬዚዳንቱ ፡ የሕ
ዝብ ፡ ገንዘብ ፡ የሚያጭበረብር ፡ መሆኑ ፡ በ
ብዙ ፡ መረጃ ፡ ታወቀ
3. ከፍ ፡ ያለ. His massive erudition impressed
the audience. ከፍ ፡ ያለ ፡ ዕውቀቱ ፡ አዳማጮቹ
ን ፡ ገረማቸው
4. መዓት. A massive swarm of locusts invaded
the country. መዓት ፡ የአንበጣ ፡ መንጋ ፡ ሀገሪቷ
ን ፡ ወረረ

## mast የመርከብ ፡ ምሰሶ
The sailor was leaning against the mast.
መርከበኛው ፡ የመርከቡን ፡ ምሰሶ ፡ ተደግፎ ፡
ቆሞ ፡ ነበር

## master (v.)
1. ጠንቅቆ ፡ ዐወቀ ፤ በደንብ ፡ አጣርቶ ፡ ዐወቀ. It
will take you five years to master Amharic.
አማርኛን ፡ ጠንቅቆ ፡ ለማወቅ ፡ አምስት ፡ ዓመ
ት ፡ ይፈጅብሃል
He was bent on mastering Amharic. አማርኛ ፡
በደንብ ፡ አጣርቶ ፡ ለማወቅ ፡ ጣረ
2. አጠናቆ ፡ ዐወቀ. The manifold subject requires
years of study to master. ብዙ ፡ ዘርፍ ፡ ያለው
ን ፡ ትምህርት ፡ አጠናቆ ፡ ለማወቅ ፡ የብዙ ፡
ዓመታት ፡ ጥናት ፡ ያስፈልጋል
3. አጥርቶ ፡ ዐወቀ. He has mastered three foreign
languages. ሦስት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋዎች ፡
አጥርቶ ፡ ያውቃል
4. ገታ. It took him quite a while to master
his temper. ንዴቱን ፡ ለመግታት ፡ ብዙ ፡ ጊ
ዜ ፡ ወሰደበት

## master (n.)
1. ጌታ. No man can serve two masters. አንድ
ም ፡ ሰው ፡ ለሁለት ፡ ጌታ ፡ ሊገዛ ፡ አይችልም
The master beat the dog. ጌትዮው ፡ ውሻውን ፡
መታው
2. መምህር. The master taught his pupils how
to read. መምህሩ ፡ ተማሪዎቹን ፡ ንባብ ፡ አስተማ
ራቸው

*He is a master at story telling. ተረት ፡ ሲያወራ ፡ የሚያክለው ፡ የለም
*He is master of the situation. እንደ ፡ ሁኔታው ፡ የመሥራት ፡ ችሎታ ፡ አለው

**master of the house** ባለቤት
The master of the house is not in. ባለቤቱ ፡ እቤት ፡ የሉም

**master** (adj.) ዋና
The master bedroom has a large window. ዋናው ፡ መኝታ ፡ ቤት ፡ ትልቅ ፡ መስኮት ፡ አለው

**master musician** የሙዚቃ ፡ ሊቅ
He is a master musician, and everyone admires him. የሙዚቃ ፡ ሊቅ ፡ ስለሆነ ፡ ሁሉ ፡ ያደንቀዋል

**master plan** መሠረተ ፡ ፕላን
A master plan is needed for the city's development. ለከተማው ፡ እድገት ፡ መሠረተ ፡ ፕላን ፡ ያስፈልጋል

## masterful
1. ሥልጣን ፡ የተመላበት. His masterful tone frightened all the clerks. ሥልጣን ፡ የተመላበት ፡ ድምፁ ፡ ሻጮቹን ፡ ሁሉ ፡ አስደነገጣቸው
2. ጥበብ ፡ የተሞላበት. His masterful ways gained her love. ጥበብ ፡ የተሞላበት ፡ ሥራው ፡ የሷን ፡ ፍቅር ፡ አስገኘለት
3. ረቂቅ ፡ የሆነ. The masterful performance of the pianist enchanted the audience. የፒያኒስቱ ፡ ረቂቅ ፡ የሆነ ፡ የፒያኖ ፡ አመታት ፡ አዳማጮቹን ፡ አስደሰታቸው

## master key ዓይነተኛ ፡ ቁልፍ
This master key will unlock all the doors in this building. ይህ ፡ ዓይነተኛ ፡ ቁልፍ ፡ በሕንጻው ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ በሮች ፡ ሁሉ ፡ ይከፍታል

## masterly የጠቢብ
He did a masterly job of repair work. በጥገና ፡ በኩል ፡ የጠቢብ ፡ ሥራ ፡ ሠራ

## mastermind የወጠነ ፡ ሰው
The mastermind behind the revolt was caught. ሁከቱን ፡ ሁሉ ፡ የወጠነው ፡ ሰው ፡ ተያዘ

## Master of Arts ማስተር ፡ ኦፍ ፡ አርትስ
He received his Master of Arts from the University of California. የማስተር ፡ ኦፍ ፡ አርትስ ፡ ዲግሪውን ፡ ከካሊፎርንያ ፡ ዩንቨርሲቲ ፡ አገኘ

## master of ceremonies አስተዋዋቂ
He was master of ceremonies at the concert. በሙዚቃው ፡ በዓል ፡ ላይ ፡ አስተዋዋቂ ፡ ነበር

## masterpiece ታላቅ ፡ ቅርስ
His latest novel is a literary masterpiece. በቅርቡ ፡ ያወጣው ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ መጽሐፉ ፡ ታላቅ ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ቅርስ ፡ ነው
*This painting is an artistic masterpiece. ይህ ፡ ሥዕል ፡ ታላቅ ፡ ርቀት ፡ ያለው ፡ ሥነ ፡ ጥበብ ፡ ነው

## mastery
1. በላይነት. The two teams vied for mastery. ሁለቱ ፡ ቡድኖች ፡ ለበላይነት ፡ ተወዳደሩ
2. ችሎታ. His mastery of arithmetic is noticed by all. በሒሳብ ፡ ረገድ ፡ ያለው ፡ ችሎታ ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነው
3. ለመቈጣጠር ፡ ያለው ፡ ችሎታ. His mastery over his temper helped him greatly in life. ንዴቱን ፡ ለመቈጣጠር ፡ ያለው ፡ ችሎታ ፡ በሕይወቱ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ረዳው

## masticate አኘከ
He tried to masticate the tough leather. ጠንካራውን ፡ ጠፍር ፡ ለማኘክ ፡ ሞከረ

## mat (v.) በታተነ
The sea breeze matted his hair. ከባሕር ፡ የሚመጣው ፡ ነፋስ ፡ ጸጉሩን ፡ በታተነው

**be matted**
1. ተቈጣጠረ. His hair is matted with blood. ጸጉሩ ፡ በደም ፡ ተቈጣጥሯል
2. ተደመደመ. The grass was matted because the animals trampled and rolled on it. እንስሳት ፡ ስለረጋገጡትና ፡ ስለተንደባለሉበት ፡ ሣሩ ፡ ተደመደመ

## mat (n.) ሰሌን
Put a mat on the floor to sit on! ለመቀመጫ ፡ በወለሉ ፡ ላይ ፡ ሰሌን ፡ አንጥፍ

## match (vt.)
1. ተመሳሳይ ፡ ነው. This color matches that one. ይህ ፡ ቀለም ፡ ከዚያኛው ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው
2. አከለ. My skills in typing do not match his. የመኪና ፡ ጽሕፈት ፡ ችሎታዬ ፡ የሱን ፡ አያክልም
*I'm ready to match my strength with yours. እንተን ፡ በጉልበት ፡ ለመቋቋም ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ

**match** (vi.) ተመሳሳይ ፡ ነው ፤ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ነው
The two candles match exactly. ሁለቱ ፡ ሻማዎች ፡ ፍጹም ፡ ተመሳሳዮች ፡ ናቸው
Your socks do not match. የእግር ፡ ሹራብህ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ አይደለም

## match (n.)
1. ክብሪት. Give me a box of matches, please! አንድ ፡ ፓኮ ፡ ክብሪት ፡ ስጠኝ

Strike a match; I can't see in the dark. ክብሪት ፡ ጫር ። በጨለማ ፡ ለማየት ፡ አልችልም
2. ግጥሚያ. Who won the match? ግጥሚያውን ፡ ማን ፡ አሸነፈ ?
3. ተመሳሳይ. I am looking for a match for this paint. የዚህን ፡ ቀለም ፡ ተመሳሳይ ፡ እፈልጋለሁ
4. እኩያ. You're no match for him. He'll flatten you with one blow. እኩያው ፡ አይደለህም ። ባንድ ፡ ምት ፡ ይዘርርሃል
5. ጋብቻ. The parents did not approve of the match. ወላጆቹ ፡ ጋብቻውን ፡ አልፈቀዱም

**arrange a match** አጋባ
She tried to arrange a match between the bachelor and the widow. ወንደ ፡ ላጤውንና ፡ ባሏ ፡ የሞተባትን ፡ ሴት ፡ ለማጋባት ፡ ሞከረች

**be a good match**
1. ለጋብቻ ፡ ተስማማ. He is a good match. እሱ ፡ ለጋብቻ ፡ የሚስማማ ፡ ነው
2. ተስማማ. These colors aren't a good match. እነዚህ ፡ ቀለሞች ፡ አይስማሙም

**be a match** ተስተካከለ
She is not yet a match for her mother in cooking. በምግብ ፡ አሠራር ፡ እናቷን ፡ አትስተካከልም
[See also 'wrestling']

## matchmaker አማጭ
The matchmaker arranged a marriage between these two couples. አማጩ ፡ ሁለቱን ፡ ሰዎች ፡ ለጋብቻ ፡ አስማማ

## mate (v.)
1. ተጠቃ. The animals in the zoo haven't mated this year. በአራዊት ፡ መጠበቂያ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ እንስሶች ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ አልተጠቁም
2. ፈለፈለ. Birds mate in the spring and build their nests. ወፎች ፡ የሚፈለፍሉትና ፡ ጎጆ ፡ የሚሠሩት ፡ በጸደይ ፡ ነው

## mate (n.)
1. ጓደኛ. He and his mate left the school at 12 o'clock. እሱና ፡ ጓደኛው ፡ በስድስት ፡ ሰዓት ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ወጡ
I lost the mate of this glove. የዚህ ፡ ጓንቲ ፡ ጓደኛው ፡ ጠፋብኝ
2. የትዳር ፡ ጓደኛ. One should treat one's mate with consideration. አንድ ፡ ሰው ፡ የትዳር ፡ ጓደኛውን ፡ በሚገባ ፡ መያዝ ፡ አለበት
3. ባል. The lioness and her mate were sunning themselves in the cage. አንበሳይቱና ፡ ባሏ ፡ እብረት ፡ ጎጆው ፡ ውስጥ ፡ ፀሐይ ፡ ይሞቁ ፡ ነበር
*The lion and his mate were sunning themselves in the cage. አንበሳውና ፡ አንበሳይቱ ፡ እብረት ፡ ጎጆው ፡ ውስጥ ፡ ፀሐይ ፡ ይሞቁ ፡ ነበር

## material (n.)
1. ጨርቅ. I have enough material to make a coat. ኮት ፡ ለመስፋት ፡ በቂ ፡ ጨርቅ ፡ አለኝ
2. እቃ. We use only the best materials. እኛ ፡ የምንሠራባቸው ፡ ምርጥ ፡ እቃዎች ፡ ብቻ ፡ ናቸው
The raw material is processed by the factory and turned into plastics. ጥሬው ፡ እቃ ፡ ፋብሪካው ፡ ውስጥ ፡ ከተሠራ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ፕላስቲክነት ፡ ይለወጣል
3. ልዩ ፡ ልዩ ፡ ማስረጃዎች. He is collecting material for a book. መጽሐፍ ፡ ለመጻፍ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ማስረጃዎችን ፡ በመሰብሰብ ፡ ላይ ፡ ነው

## material (adj.)
1. ዓለማዊ. She's only interested in material things. እሷ ፡ በዓለማዊ ፡ ነገሮች ፡ ብቻ ፡ ትደሰታለች
2. ጉልህ. There's no material difference between the two. በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ምንም ፡ ጉልህ ፡ ልዩነት ፡ የለም
3. ጠቃሚ. The judge warned the witness not to hold back material evidence. ዳኛው ፡ ምስክሩ ፡ ጠቃሚ ፡ ማስረጃዎችን ፡ እንዳይደብቅ ፡ አስጠነቀቁት
4. ዋና. The baking is a material factor in making cake. ኬክ ፡ ሲሠራ ፡ ዋናው ፡ ሥራ ፡ መጋገሩ ፡ ነው
5. ለአካል ፡ የሚሰጥ. Food and shelter are material comforts. ምግብና ፡ መጠለያ ፡ ለአካል ፡ ምቾት ፡ የሚሰጡ ፡ ናቸው

**material needs** የሰውነት ፡ መሠረታዊ ፡ ፍላጎት
Every man needs to satisfy his material needs. ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሰውነት ፡ መሠረታዊ ፡ ፍላጎቱን ፡ ለማርካት ፡ ይፈልጋል

## materialize (vt.)
1. በመጀመሪያ ፡ አወጣ(ለት). An inventor materializes his ideas by building a model. ፈልሳፊው ፡ ሊሠራ ፡ ያሰበውን ፡ ነገር ፡ በመጀመሪያ ፡ ሞዴል ፡ ያወጣለታል
2. ከግብ ፡ አደረሰ. He materialized his ambition to become a doctor. ሐኪም ፡ ለመሆን ፡ የነበረውን ፡ ምኞት ፡ ከግብ ፡ አደረሰ

**materialize** (vi.) በሥራ ፡ ላይ ፡ ዋለ
Our plans did not materialize. እቅዶቻችን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አልዋሉም

**materially**

1. በጣም. The teacher's ideas helped materially in planning the play. ቲያትሩን ፡ በማዘጋጀት ፡ ረገድ ፡ ያስተማሪው ፡ ሐሳቦች ፡ በጣም ፡ ረዱ

2. በመሣሪያ ፡ ረገድ. The enemy was strong materially, but weak in leadership. ጠላት ፡ በመሣሪያ ፡ ረገድ ፡ ጠንካራ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ በመሪ ፡ በኩል ፡ ደካማ ፡ ነበር

3. በሀብት. The nation got better materially, but worse spiritually. አገሪቱ ፡ በሀብት ፡ ስትሻሻል ፡ በመንፈሳዊ ፡ ረገድ ፡ ግን ፡ እየተበላሸች ፡ ሄደች

**maternal**

1. የእናት. A child needs maternal love. ልጅ ፡ የእናት ፡ ፍቅር ፡ ያስፈልገዋል

2. በእናቱ ፡ በኩል. His maternal grandparents are still alive. በእናቱ ፡ በኩል ፡ አያቶቹ ፡ አሁንም ፡ በሕይወት ፡ አሉ

**maternal care** የሕፃናት ፡ አስተዳደግ

Maternal care is being taught by health teams. የሕፃናት ፡ አስተዳደግ ፡ ትምህርት ፡ በጤና ፡ ጓዶች ፡ ይሰጣል

**maternity** (n.) ወላድ ፡ መሆን

Maternity changes a woman in many ways. ወላድ ፡ መሆን ፡ ሴትን ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ይለውጣታል

**maternity** (adj.)

1. የማዋለጃ. This hospital has a maternity ward. ይህ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ የማዋለጃ ፡ ክፍል ፡ አለው

2. የእርጉዝ. She wears a maternity dress. የእርጉዝ ፡ ልብስ ፡ ትለብሳለች

**mathematician** የሒሳብ ፡ ዐዋቂ

A mathematician is needed to solve this problem. ይህንን ፡ ፕሮብሌም ፡ ለመሥራት ፡ የሒሳብ ፡ ዐዋቂ ፡ ያስፈልጋል

**mathematics** ሒሳብ

I study mathematics every day. ሁልቀን ፡ ሒሳብ ፡ አጠናለሁ

**matriarch** [ቤተ ፡ ሰብን ፡ ወይም ፡ ጐሳን ፡ የምታስተዳድር ፡ እመቤት]

**matriculate** ኮሌጅ ፡ ገባ

I matriculated last year. ዓምና ፡ ኮሌጅ ፡ ገባሁ

**matrimony** ጋብቻ

Matrimony is the goal of many young women. የብዙ ፡ ልጃገረዶች ፡ ዓላማ ፡ ጋብቻ ፡ ነው

**matron** [በዕድሜ ፡ ጠና ፡ ያሉ ፡ ያገቡ ፡ ወይም ፡ ባል ፡ የሞተባቸው ፡ ወይዘሮ]

**matter** (v.) አስፈላጊ ፡ ነው

It hardly matters one way or the other. ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ እጅግም ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም

**matter** (n.)

1. ጉዳይ. It's not a matter of price. የዋጋ ፡ ጉዳይ ፡ አይደለም

2. ነገር. I'll look into the matter. ነገሩን ፡ እመረምረዋለሁ

You're only making matters worse. ነገሩን ፡ ታባብሰዋለህ

3. ፍሬ ፡ ነገር. The matter of this book concerns everybody. የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ሁሉን ፡ የሚመለከት ፡ ነው

4. ዋጋ. This idea is of little matter. ይህ ፡ አሳብ ፡ አነስተኛ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ነው

5. ምክንያት. If a man is robbed, he has matter for complaint to the police. አንድ ፡ ሰው ፡ የተቀማ ፡ እንደሆነ ፡ ለፖሊስ ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ ምክንያት ፡ ይኖረዋል

6. ግዘፍ ፡ ያለው ፡ ነገር. Solids and liquids are matter. ጥጥርና ፡ ፈሳሽ ፡ ነገሮች ፡ ግዘፍ ፡ ያላቸው ፡ ነገሮች ፡ ናቸው

**matter of fact, as a ~**

1. እንዲያውም. As a matter of fact, I'm leaving for that country myself. እንዲያውም ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ ወደዚያ ፡ አገር ፡ መሄዴ ፡ ነው

2. እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከሆነ. As a matter of fact, I wasn't even there. እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከሆነ ፡ እዚያም ፡ አልነበርኩ

**a matter of** ለብዙ

We waited a matter of hours. ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ ጠበቅን

**be the matter** ነካ

What's the matter with this motor? ይህን ፡ ሞተር ፡ ምን ፡ ነካው ?

What's the matter? Why are you crying? ምን ፡ ነካህ ፡ (ምን ፡ ሆነሃል) ፤ ለምን ፡ ታለቅሳለህ ?

**for that matter** እንዲያውም

For that matter, he can stay where he is. እንዲያውም ፡ እዚያው ፡ ሊቆይ ፡ ይችላል

**in the matter of** በ - - - በኩል

He is strict in the matter of discipline. በሥርዓት ፡ በኩል ፡ ጥብቅ ፡ ነው

**it does not matter** ግድ ፡ የለም

It does not matter; I shall go myself. ግድ ፡ የለም ፤ እኔው ፡ ራሴ ፡ እሄዳለሁ

It did not matter to him whether he got paid or not. ቢከፈለው ፡ ባይከፈለው ፡ ግድ ፡ አልነበረ ውም

**it's of no matter** አያሳስብም
It's of no matter. The cut is a small one. የተቆረጠው ፡ ትንሽ ፡ ነው ፤ አያሳስብም

**no matter what** ምንም ፡ ብ + imperfect
No matter what I do, it doesn't please him. ምንም ፡ ብሠራ ፡ አያስደስተውም
Time moves on, no matter what we do. ምንም ፡ ብናደርግ ፡ ጊዜ ፡ ማለፍ ፡ አይቀርም
*We're going, no matter what you say. ያልከውን ፡ ብትል ፡ እንሄዳለን

**what does it matter** ምን ፡ ያደርጋል
What does it matter? I'm going anyway. ምን ፡ ያደርጋል ? ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ መሄዴ ፡ ነው
[See also 'course, dead, fact, form']

**matter-of-fact** (= adv.) ምንም ፡ እንዳልሆነ ፡ አድርጎ
His matter-of-fact explanation of the accident surprised everyone. ያደጋውን ፡ ሁኔታ ፡ ምንም ፡ እንዳልሆነ ፡ አድርጎ ፡ መናገሩ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ አስገ ረመው

**mattress** ፍራሽ
I need a new mattress for my bed. ለአልጋዬ ፡ አዲስ ፡ ፍራሽ ፡ ያስፈልገኛል

**mature** (vt.) አጐለመሰ
This experience matured his character. ይህ ፡ በ ሕይወቱ ፡ የደረሰበት ፡ ነገር ፡ ጠባዩን ፡ አጐለመ ሰው

**mature** (vi.)
1. በሰለ. Wine matures in three months. ወይኑ ፡ ለመብሰል ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ይፈጅበታል
2. ጐለመሰ. He seems to have matured as a result of his experience in the war. ከጦርነት ፡ ባ ገኘው ፡ ልምምድ ፡ የጐለመሰ ፡ ይመስላል
3. ጠነከረ. Most animals mature faster than human beings. ብዙ ፡ እንስሳት ፡ ከሰው ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ይጠነክራሉ
4. የክፍያ ፡ ጊዜ ፡ ደረሰ. When your saving bonds mature, you can collect their full value. የቁጠባ ፡ ቦንድህ ፡ የክፍያ ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ ሙሉ ፡ ዋጋው ን ፡ ልትወስድ ፡ ትችላለህ

**mature** (adj.)
1. የበሰለ. A mature mind is capable of comparing things. የበሰለ ፡ አእምሮ ፡ ነገርን ፡ ማመ ዛዘን ፡ ይችላል
2. የጉልምስና. Fifty is a mature age. ኀምሳ ፡ የ ጉልምስና ፡ ዕድሜ ፡ ነው
3. ዐዋቂ. This job can be done only by a mature woman. ይህን ፡ ልትሠራ ፡ የምትችል ፡ ዐዋቂ ፡ ሴት ፡ ብቻ ፡ ናት

**be mature**
1. በሰለ. The boy is very mature for his age. ልጁ ፡ በዚህ ፡ ዕድሜው ፡ በጣም ፡ በስሏል
2. ተጠናቀቀ. His plans are not yet mature. የሱ ፡ እቅድ ፡ ገና ፡ አልተጠናቀቀም

**of mature years** የበሰለ
Persons of mature years are needed for this job. ለዚህ ፡ ሥራ ፡ የበሰሉ ፡ ሰዎች ፡ ያስፈልጋሉ

**maturity**
1. ዐቅመ ፡ አዳም. He had reached maturity by the time he was twenty. ሃያ ፡ ዓመት ፡ ሲሞ ላው ፡ ለዐቅመ ፡ አዳም ፡ ደርሶ ፡ ነበር
2. ዐቅመ ፡ ሔዋን. She had reached maturity by the time she was twenty. ሃያ ፡ ዓመት ፡ ሲ ሞላት ፡ ለዐቅመ ፡ ሔዋን ፡ ደርሳ ፡ ነበር

**be far from maturity** ገና ፡ አልበሰለም
Even though he is 30 he is far from maturity. ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ቢሆነውም ፡ ገና ፡ አልበሰለም

**bring to maturity** ከግብ ፡ አደረሰ
We brought our plan to maturity. እቅዳችንን ፡ ከግብ ፡ አደረስን

**reach maturity**
1. ተሟላ. When their plans reached maturity, they were able to begin. እቅዳቸው ፡ በተሟላ ፡ ጊዜ ፡ ለመጀመር ፡ ቻሉ
2. በሰለ. The oranges on the tree will reach maturity in two more weeks. በዚህ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ብርቱካኖች ፡ ከሁለት ፡ ሳምንት ፡ በኋላ ፡ ይበስላሉ

**(not) reach maturity** ዕድሜው ፡ ሳይደርስ ፡ ሞተ
Many fish and frogs never reach maturity. ብዙ ፡ ዓሣዎችና ፡ እንቁራሪቶች ፡ ዕድሚያቸው ፡ ሳይደርስ ፡ ይሞታሉ

**maul** በማንገላታት ፡ ጐዳ
The lion mauled his trainer. አንበሳው ፡ አሠል ጣኙን ፡ በማንገላታት ፡ ጐዳው

**maxim** ምሳሌ
"Make hay while the sun shines" is a maxim. « አባት ፡ ሳለ ፡ አጊጥ ፤ ጀንበር ፡ ሳለ ፡ ሩጥ » ፡ የ ሚለው ፡ ምሳሌ ፡ ነው

**maximize**
1. አጋነነ. He maximized the importance of what he had done. የሠራውን ፡ ነገር ፡ ትልቅነት ፡ አጋነነ
2. አዳበረ. He will maximize profits by re-

ducing costs. ወጪን ፡ በመቀነስ ፡ ትርፍን ፡ ያዳብራል

**maximum** (n.)

1. መጨረሻ. I'm willing to pay twenty dollars, but that's the maximum. ሃያ ፡ ብር ፡ ለመክፈል ፡ እስማማለሁ ። ይህ ፡ ግን ፡ የመጨረሻው ፡ ነው

2. የመጨረሻ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍጥነት. The speed limit is 40 miles an hour; drivers must not exceed this maximum. የፍጥነቱ ፡ ወሰን ፡ በሰዓት ፡ አርባ ፡ ማይል ፡ ነው ። ነጂዎች ፡ ይህን ፡ የመጨረሻ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍጥነት ፡ ማለፍ ፡ የለባቸውም

**maximum** (adj.) ከፍተኛ

The maximum temperature ever recorded in the city is 100° F. እስካሁን ፡ በዚህ ፡ ከተማ ፡ የተመዘገበው ፡ ከፍተኛ ፡ሙቀት ፡ 100° ፋረንሃይት ፡ ነው

He pays the maximum amount for old books. ላሮጌ ፡ መጻሕፍት ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ይከፍላል

*The maximum weight for baggage in air travel is 44 pounds. በአውሮፕላን ፡ ላይ ፡ የሚፈቀደው ፡ የእቃ ፡ ክብደት ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ አርባ ፡ አራት ፡ ነጥር ፡ ነው

**May** ግንቦት

**may** (might)

1. (jussive). May I offer you a cup of coffee? አንድ ፡ ሲኒ ፡ ቡና ፡ ልስጥህ ?

May I go now? ልሂድ ?

May you be very happy! ደስ ፡ ይበልህ

2. (verb) + ይሆናል. That may be so. እንዲያ ፡ ይሆን ፡ ይሆናል

I may be able to come. ልመጣ ፡ እችል ፡ ይሆናል

I may be too late already. አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ዘግይቼ ፡ ይሆናል

Be good, and I might let you have my bicycle tomorrow. ጠባይህን ፡ ካሳመርክ ፡ ነገ ፡ ብስክሌቴን ፡ እሰጥህ ፡ ይሆናል

3. ሊሆን ፡ ይችላል. It may be true. እውነት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል

*If we had rushed, we might have caught the train. ብንሮጥ ፡ ኖሮ ፡ ባቡሩን ፡ ልንደርስበት ፡ እንችል ፡ ነበር

*You might at least say 'thank you'. ሌላው ፡ ቢቀር ፡ እግዜር ፡ ይስጥልኝ ፡ ልትል ፡ ይገባል

**may as well**

*We may as well stay where we are. ለዚህ ፡ ለዚህ ፡ ባለንበት ፡ እንቆይ

**(this) may or may not be** ሊሆንም ፡ ላይሆንም ፡ ይችላል

This may or may not be true, but we will look into it anyway. ይህ ፡ እውነት ፡ ሊሆንም ፡ ላይሆንም ፡ ይችላል ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ነገሩን ፡ እናጣራለን

**be that as it may** የሆነው ፡ ቢሆን ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ። ግራም ፡ ነፈሰ ፡ ቀኝ

Be that as it may, I will go to New York anyway. የሆነው ፡ ቢሆን ፡ (ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ። ግራም ፡ ነፈሰ ፡ ቀኝ) ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ኒውዮርክ ፡ መሄዴ ፡ ነው

**maybe**

1. ምናልባት. Will you come? Maybe. ትመጣለህ? ምናልባት

2. ምናልባት + gerundive + ይሆናል. Maybe he's lost. ምናልባት ፡ ጠፍቶ ፡ ይሆናል

**mayor**

1. ከንቲባ. Who is the mayor of Addis Ababa? የአዲስ ፡ አበባ ፡ ከንቲባ ፡ ማን ፡ ነው ?

2. የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ሹም. Who is the mayor of Dessie? የደሴ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ማን ፡ ነው ?

**maze** መግቢያ ፡ መውጫው ፡ የሚያደናግር

Many ancient palaces were mazes. ብዙዎቹ ፡ የጥንት ፡ ቤተ ፡ መንግሥቶች ፡ መግቢያ ፡ መውጫቸው ፡ የሚያደናግር ፡ ነበር

*This maze of facts and figures is hard to understand. የተወሳሰቡትን ፡ ፍሬ ፡ ነገሮችና ፡ ቁጥሮች ፡ መረዳት ፡ ያስቸግራል

**be in a maze** ተማታ

I was in such a maze, I couldn't answer. ተማቶብኝ ፡ ስለነበረ ፡ ልመልስ ፡ አልቻልኩም

**me,** expressed by the suffix pronoun -ኝ

Did you see me yesterday? ትናንት ፡ አይተኸኛል ?

Give me your book! መጽሐፍህን ፡ ስጠኝ

**mead** ጠጅ

Drink this mead! It's good. ይህንን ፡ ጠጅ ፡ ጠጣ ። ጥሩ ፡ ነው

**meadow** መስክ

The meadow is bordered by trees. በመስኩ ፡ ዙሪያ ፡ ዛፎች ፡ አሉ

**meager**

1. የማያጠግብ. He ate a meager meal of cold boiled potatoes. የማያጠግብ ፡ የበረደ ፡ ቅቅል ፡ ድንች ፡ በላ

2. የተጐሳቈለ. The meager face of the beggar aroused his compassion. የተጐሳቈለው ፡ የለማኙ ፡ ፊት ፡ አሳዘነው

3. እጅግም. The Central African Republic's resources are meager. የመሀከለኛ ፡ አፍሪካ ፡ ሪፑብሊክ ፡ ያላት ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ እጅግም ፡ ነው

**be meager** እምብዛም ፡ ጥሩ ፡ አልነበረም
The results were meager. ውጤቱ ፡ እምብዛም ፡ ጥሩ ፡ አልነበረም

**meal** ምግብ
Breakfast is the first meal of the day. ቁርስ ፡ የቀኑ ፡ የመጀመሪያው ፡ ምግብ ፡ ነው
I haven't eaten a decent meal in weeks. ለብዙ ፡ ሳምንት ፡ ጥሩ ፡ ምግብ ፡ አልበላሁም
*Three meals a day aren't enough for him. በቀን ፡ ሦስቱ ፡ መብላት ፡ አያጠግበውም

**humble meal** ተራ ፡ ምግብ
Will you partake of this humble meal? ይህችን ፡ ተራ ፡ ምግብ ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ ልትሳተፍ ፡ ትፈቅዳለህ ?
[See also 'festive, midday']

**mean** (v.)
1. ማለት ፡ ነው. Falling leaves mean winter is near. ቅጠላ ፡ ቅጠል ፡ ሲረግፍ ፡ ክረምት ፡ ተቃርቧል ፡ ማለት ፡ ነው
What do you mean by that? እንዲህ ፡ ስትል ፡ ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው ?
2. አሰበ. I meant to call, but I forgot. ልደውል ፡ አስቤ ፡ ነበር ፡ ግን ፡ ረሳሁት
I know he means well, but the way he does things annoys me. ቅን ፡ ማሰቡን ፡ አውቃለሁ ፤ ግን ፡ አሠራሩ ፡ ያናድደኛል
He says exactly what he means. የሚናገረው ፡ ልክ ፡ ያሰበውን ፡ ነው
3. ፈለገ. I didn't mean for you to see the letter. ደብዳቤውን ፡ አንተ ፡ እንድታየው ፡ አልፈለግሁም ፡ ነበር
4. የምሩን ፡ ነው. He certainly meant what he said. የምሩን ፡ ነው ፡ የተናገረው
5. ሰነዘረ. He meant those words for all of us. አስተያየቱን ፡ የሰነዘረው ፡ ለሁላችንም ፡ ነበር
6. አስከተለ. This frontier incident means war. ይህ ፡ የድንበር ፡ ግጭት ፡ ጦርነት ፡ ያስከትላል
7. የ---ምልክት ፡ ነው. Those black clouds mean rain. ያ ፡ ከባድ ፡ ደመና ፡ የዝናም ፡ ምልክት ፡ ነው
8. ትርጉም ፡ ሊኖረው ፡ ቻለ. One word often means several things. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ብዙ ፡ ትርጉም ፡ ሊኖረው ፡ ይችላል
9. ትርጉም ፡ ነው. What do those signs mean? እነዚያ ፡ ምልክቶች ፡ ትርጉማቸው ፡ ምንድነው ?
10. ትርጉም ፡ ሰጠ. The dictionary tells you what words mean. መዝገበ ፡ ቃላት ፡ የቃላትን ፡ ትርጉም ፡ ይሰጣል

*I am sorry I offended her; I really did not mean any harm. ስላስቀየምኳት ፡ አዝናለሁ ፤ በእርግጥ ፡ ክፉት ፡ አስቤ ፡ አልነበረም

**mean a lot** ትልቅ ፡ ነገር ፡ ነው
His friendship means a lot to me. የርሱ ፡ ጓደኝነት ፡ ለኔ ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ ነው

**mean business** የምሩን ፡ ነው
When you say you'll fight, do you mean business? እጣላለሁ ፡ ስትል ፡ የምርህን ፡ ነው ?

**mean everything**
*Money means everything to him. ገንዘብ ፡ ነፍሱ ፡ ነው

**mean nothing** ከምንም ፡ አይቈጥረውም ፤ ምንም ፡ አይደለም
The high cost of living means nothing to some people. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ የኑሮን ፡ መወደድ ፡ ከምንም ፡ አይቈጥሩትም
It means nothing to me. ለኔ ፡ ምንም ፡ አይደለም

**meant to be**
*Is this number meant to be a one or a seven? ይህ ፡ ቁጥር ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ሰባት ?

**mean to say** ማለቱ ፡ ነው
Do you mean to say you saw everything? ሁሉንም ፡ ነገር ፡ አይቻለሁ ፡ ማለትህ ፡ ነው ?

**mean well**
*When he punishes his child, I know he means well. ልጁን ፡ ሲቀጣ ፡ በጥሩ ፡ መንፈስ ፡ መሆኑን ፡ አውቃለሁ

**not mean much** ዋጋ ፡ የለውም
His promising to pay you back later doesn't mean much. ሌላ ፡ ጊዜ ፡ እከፍላለሁ ፡ ማለቱ ፡ ዋጋ ፡ የለውም

**mean** (n.)
1. አማካኝ ፡ ሐሳብ. We must seek the mean between the two extremes. ለሁለቱ ፡ የተራራቁ ፡ ሐሳቦች ፡ አማካኙን ፡ ሐሳብ ፡ መፈለግ ፡ አለብን
2. አማካይ. Gray is the mean between black and white. የጥቁርና ፡ የነጭ ፡ ቀለም ፡ አማካይ ፡ ግራጫ ፡ ነው

**means**
1. መንገድ. We won the game by fair means. ጨዋታውን ፡ ያሸነፍነው ፡ በትክክለኛ ፡ መንገድ ፡ ነው
2. ዐቅም. He doesn't have the means to do it. ያንን ፡ ለመሥራት ፡ ዐቅም ፡ የለውም
He lives beyond his means. ካቅሙ ፡ በላይ ፡ ይኖራል
*He uses paper as a means for sweeping up the dust. አቧራውን ፡ በወረቀት ፡ ይጠርጋል

**means to an end**
It was just a means to an end. ይህ ፡ ከግቡ ፡ ለመድረስ ፡ የሚረዳ ፡ ነገር ፡ ነው

**by all means** በምንም ፡ ዓይነት ፡ ቢሆን ፤ በምንም ፡ አኳኋን
By all means take the job! በምንም ፡ ዓይነት ፡ ቢሆን ፡ ሥራውን ፡ ተቀበል
Avoid that by all means! በምንም ፡ አኳኋን ፡ ያንን ፡ አስወግደው

**(not) by any means** ምንም + negative verb
He was not surprised at the news by any means. በወሬው ፡ ምንም ፡ አልተደነቀም

**by means of**
1. በ. You can regulate it by means of a screw. በቅርንፉድ ፡ ምስማር ፡ ልታስተካክለው ፡ ትችላለህ
2. በ - - አማካይነት. Among the deaf and dumb, communication is carried on by means of the sign alphabet. ደንቆሮና ፡ ድዳ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ሐሳብ ፡ የሚለዋወጡት ፡ በጣት ፡ ምልክት ፡ አማካይነት ፡ ነው

**by no means**
1. በምንም ፡ ዓይነት + (negative verb). By no means will I allow you to do what you planned. ያቀድከውን ፡ እንድትሠራ ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ አልፈቅድልህም
2. በፍጹም + (negative verb). He is by no means stupid. በፍጹም ፡ ደደብ ፡ አይደለም

**man of means** ባለጸጋ
He is a man of means; he can afford to pay more than other people. ባለጸጋ ፡ ስለሆነ ፡ ከሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ይበልጥ ፡ ሊከፍል ፡ ይችላል
[See also 'foul, ways']

**mean** (adj.)
1. ወራዳ. His mean thoughts are unworthy of a person who is a priest. ወራዳ ፡ አስተሳሰቡ ፡ ቄስ ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ ተገቢ ፡ አይደለም
2. (= noun) ወራዳነት. It is mean of him to treat you like that. አንተን ፡ እንደዚህ ፡ ማድረጉ ፡ ወራዳነቱ ፡ ነው
3. አስከፊ. His mean remarks lost him many friends. አስከፊ ፡ አስተያየቱ ፡ ከብዙ ፡ ጓደኞች ፡ አጣላው
4. መሀከለኛ. What is the mean temperature of Addis Ababa? የአዲስ ፡ አበባ ፡ መሀከለኛ ፡ ሙቀት ፡ ስንት ፡ ነው ?
5. ማእከላይ. The mean number between 3 and 9 is 6. የሦስትና ፡ የዘጠኝ ፡ ማእከላይ ፡ ቁጥር ፡ ስድስት ፡ ነው
6. ስግብግብ. A miser is mean about money. ጩቅ ፡ ለገንዘብ ፡ ስግብግብ ፡ ነው
7. ደሳሳ. He lives in a mean, little house. በትንሽ ፡ ደሳሳ ፡ ጎጆ ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል

**no mean** በዕውቀቱ ፡ ከፍተኛ
He is no mean scholar, and everyone knows it. በዕውቀቱ ፡ ከፍተኛ ፡ ምሁር ፡ መሆኑን ፡ ማንም ፡ ያውቀዋል

**of mean birth** ከድኻ ፡ የተወለደ
This boy is of mean birth. ይህ ፡ ልጅ ፡ ከድኻ ፡ የተወለደ ፡ ነው

**of mean quality** መናኛ
He wears clothes of mean quality. መናኛ ፡ ልብስ ፡ ይለብሳል
[See also 'trick']

**meander**
1. እየተጥመለመለ ፡ ፈሰሰ. The river meanders across the flat plain. ወንዙ ፡ ለጥ ፡ ባለው ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ እየተጥመለመለ ፡ ይፈሳል
2. ተንጐራደደ. We meandered through the park. በመናፈሻው ፡ ውስጥ ፡ ተንጐራደድን

**meaning**
1. ፍች. This word has several meanings. ይህ ፡ ቃል ፡ ብዙ ፡ ፍች ፡ አለው
2. ትርጉም. What is the meaning of life? የመኖር ፡ ትርጉሙ ፡ ምንድነው ?
*He does not know the meaning of fear. ፍርሃት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ አያውቅም

**meaningful**
1. ተገቢ. The choice of Amharic as the language of instruction was a meaningful decision. አማርኛን ፡ ለማስተማሪያ ፡ ቋንቋነት ፡ መምረጥ ፡ ተገቢ ፡ ውሳኔ ፡ ነበር
2. ሙሉ ፡ ስሜት ፡ የሚሰጥ. The teacher asked the students to make up meaningful sentences. መምህሩ ፡ ሙሉ ፡ ስሜት ፡ የሚሰጡ ፡ ዐረፍተ ፡ ነገሮች ፡ እንዲሠሩ ፡ ተማሪዎቹን ፡ ጠየቀ
3. (= adv.) በልዩ ፡ ስሜት. She gave me a meaningful look. በልዩ ፡ ስሜት ፡ ተመለከተችኝ

**meaningless**
1. ትርጉም ፡ የሌለው. His meaningless gestures showed that he was dazed by the blow. ትርጉም ፡ የሌለው ፡ እንቅስቃሴው ፡ በምቱ ፡ የፈዘዘ ፡ መሆኑን ፡ አመለከተ
2. ዋጋ ፡ የሌለው. Most scientists never do meaningless research. ብዙ ፡ የሳይንስ ፡ ሊቃውንት ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ጥናት ፡ ፈጽሞ ፡ አያደርጉም

**be meaningless** ትርጉም ፡ አልሰጠም
The argot of thieves is meaningless to other people. የሌቦች ፡ ልዩ ፡ ንግግር ፡ ለሌሎች ፡ ትርጉም ፡ አይሰጥም

**meantime** (n.), **in the ~**

1. በመሀሉ. The police were busy fighting the fire. In the meantime, the criminal escaped from jail. ፖሊሶቹ ፡ እሳቱን ፡ በመከላከል ፡ ይጣደፉ ፡ ነበር ፤ በመሀሉ ፡ ወንጀለኛው ፡ ከእስር ፡ ቤት ፡ አመለጠ
2. እስከዚያ ፡ ድረስ. In the meantime, I'll just have to wait. እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ ዝም ፡ ብዬ ፡ መጠበቅ ፡ አለብኝ

**for the meantime** ለጊዜው
I'll do as I've always done, for the meantime. ለጊዜው ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳደረግሁት ፡ አደርጋለሁ

**meanwhile** እስከዚያ ፡ ድረስ ፤ እስከዚያ
Meanwhile, it had gotten too late. እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ በጣም ፡ ዘግይቶ ፡ ነበር
We must wait for him here. Meanwhile, we can play cards. እሱን ፡ እዚሁ ፡ መጠበቅ ፡ አለብን ፤ እስከዚያ ፡ ካርታ ፡ እንጫወት

**measles** ኩፍኝ
He got the measles while in Harar. ሐረር ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ኩፍኝ ፡ ያዘው

**measly** አነስተኛ
He can't get along on his measly salary. በዛች ፡ ባነስተኛ ፡ ደሞዙ ፡ ሊኖር ፡ አይችልም

**measure** (vt.)

1. ለካ. We'll have to measure the room before we buy the rug. ምንጣፉን ፡ ከመግዛታችን ፡ በፊት ፡ ክፍሉን ፡ መለካት ፡ አለብን
2. ፈተነ. The novel measures the skill of an author in writing long stories. ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ፡ ደራሲው ፡ ረጅም ፡ ታሪኮች ፡ ለመጻፍ ፡ ያለውን ፡ ችሎታ ፡ ይፈትናል
3. መዘነ. You have to measure the importance of the issue before you make a decision. ውሳኔ ፡ ከመስጠትህ ፡ በፊት ፡ የጉዳዩን ፡ ጠቃሚነት ፡ መመዘን ፡ አለብህ

**measure** (vi.)

1. የ - - ልክ ፡ ነው. How much does he measure around the waist? የወገቡ ፡ ልክ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ?
2. ረዘመ. The front of the building measures 20 feet. ሕንጻው ፡ ከፊት ፡ ለፊቱ ፡ ሃያ ፡ ጫማ ፡ ይረዝማል

**measure off** ከፋፈለ
They measured off the ground into small lots. መሬቱን ፡ በትንንሽ ፡ መደብ ፡ ከፋፈሉት

**measure out** መዘነ
He measured out three kilos of sugar. ሦስት ፡ ኪሎ ፡ ስኳር ፡ መዘነ

**measure up** ብቁ ፡ ሆነ
As an administrator, he couldn't quite measure up. ለአስተዳዳሪነት ፡ ብቁ ፡ አልነበረም

**measure up to** እንደ - - ፡ ሆነ
The exhibition did not measure up to that of last year. ኤግዚቢሽኑ ፡ እንዳለፈው ፡ ዓመት ፡ አልሆነም
*The party did not measure up to her expectations. ድግሱ ፡ ያሰበችውን ፡ ያህል ፡ አላገኘችውም

**measure** (n.)

1. ልክ. The cloth is cut according to measure. ጨርቁ ፡ የተቀደደው ፡ በልክ ፡ ነው
2. መለኪያ. An inch is a measure of length. ኢንች ፡ የርዝመት ፡ መለኪያ ፡ ነው
3. መስፈሪያ. The measure I used for beer disappeared. ጠላ ፡ ለመቅዳት ፡ የተጠቀምኩበት ፡ መስፈሪያ ፡ ጠፋ
4. ሕግ. Congress passed a measure for flood control. ምክር ፡ ቤት ፡ የውኃን ፡ መጥለቅለቅ ፡ ለማገድ ፡ የተዘጋጀን ፡ ሕግ ፡ አሳለፈ
5. እርምጃ. All necessary measures have been taken. አስፈላጊው ፡ እርምጃ ፡ ሁሉ ፡ ተወስዷል
6. ሐሳብ. The administration and the staff locked horns over the proposed measure. አስተዳደሩና ፡ ሠራተኞቹ ፡ በቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ ላይ ፡ ሳይስማሙ ፡ ቀሩ

**beyond measure** ከመጠን ፡ በላይ
His joy was beyond measure. ደስታው ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ነበር

**in large measure** አብዛኛውን ፡ ጊዜ
His success is due in large measure to hard work. ሊሳካለት ፡ የቻለው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ጠንክሮ ፡ በመሥራቱ ፡ ነው

**in some measure** በመጠኑ
Their success was in some measure the result of careful preparation. በመጠኑ ፡ ውጤታቸው ፡ ሊያምር ፡ የቻለው ፡ በጥንቃቄ ፡ ከመዘጋጀታቸው ፡ የተነሣ ፡ ነው

**some measure** (= adv.) በመጠኑ
The government had, at that time, some measure of power. በዚያን ፡ ጊዜ ፡ መንግሥቱ ፡ በመጠኑ ፡ ኀይል ፡ ነበረው

**take the measure** ለካ
Did you take the measure of the lot? መሬቱን ፡ ለክተሃል ?
[See also 'defense']

**measured** (adj.) የተወሰነ
Drive over a measured mile to test your car's

speed! የመኪናህን ፡ ፍጥነት ፡ ለማወቅ ፡ ለተወሰነ ፡ ማይል ፡ ንዳ

**measured words** መርጦ ፡ የተናገራቸው ፡ ቃላት
The speaker's measured words brought applause. ተናጋሪው ፡ መርጦ ፡ የተናገራቸው ፡ ቃላት ፡ አድናቆትን ፡ አተረፉ

**with measured steps** በተመጠነ ፡ የዝግታ ፡ እርምጃ
The funeral cortege walked with measured steps. ለቀብተኛው ፡ በተመጠነ ፡ የዝግታ ፡ እርምጃ ፡ ተጓዘ

**measurements** ልክ
Her measurements are 36 — 24 — 38. የቧ ፡ ልክ ፡ ደረት ፡ ፴፮ ፤ ወገብ ፡ ፳፬ ፤ ዳሌ ፴፰ ፡ ነው

**meat**
1. ሥጋ. He won't eat raw meat. ጥሬ ፡ ሥጋ ፡ አይበላም
The meat of the nut is tasty. የለውዙ ፡ ሥጋ ፡ ጣፋጭ ፡ ነው
2. ፍሬ ፡ ነገር. The meat of the book is its description of 18th century Ethiopia. የመጽሐፉ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ በዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ የነበረችበትን ፡ የሚገልጽ ፡ ነው
[See also 'lean']

**meaty**
1. ሥጋ ፡ የበዛበት. Meaty broth is given to sick people. ሥጋ ፡ የበዛበት ፡ መረቅ ፡ ለበሽተኞች ፡ ይሰጣል
2. ቁም ፡ ነገር ፡ የተሞላ. His meaty speeches are listened to with great attention. ቁም ፡ ነገር ፡ የተሞላ ፡ ንግግሩን ፡ በጸጥታ ፡ አዳመጡ

**mechanic** መካኒክ
I need a mechanic to fix my car. መኪናዬን ፡ የሚሠራልኝ ፡ መካኒክ ፡ እፈልጋለሁ

**mechanical**
1. አውቶማቲክ. Some mechanical device opens the door. በሩ ፡ የሚከፈተው ፡ ባንድ ፡ አውቶማቲክ ፡ መሣሪያ ፡ ነው
2. የሞተር. A mechanical failure caused the plane to crash. አውሮፕላኑ ፡ ወድቆ ፡ ሊሰባበር ፡ የቻለው ፡ ከሞተሩ ፡ መበላሸት ፡ የተነሣ ፡ ነው
3. ደረቅ. His reading is very mechanical. አነባበቡ ፡ ደረቅ ፡ ነው

**mechanics** [ስለ ፡ መሣሪያ ፡ እንቅስቃሴና ፡ ኀይል ፡ የሚገልጽ ፡ ሳይንስ]

**mechanism** መሣሪያ
A pulley is a simple mechanism. መዘውር ፡ ቀላል ፡ መሣሪያ ፡ ነው
*Sand in the mechanism will stop a watch. አሸዋ ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ ከገባ ፡ ሰዓቱን ፡ ያቆመዋል
*The bones and muscles are parts of the mechanism of the body. አጥንቶችና ፡ ጡንቻዎች ፡ ያካል ፡ ክፍሎች ፡ ናቸው

**mechanize** በዘመናዊ ፡ መሣሪያ ፡ አካሄደ
We need to mechanize the gold mines. የወርቁን ፡ ማዕድኖች ፡ በዘመናዊ ፡ መሣሪያ ፡ ማካሄድ ፡ አለብን

**medal** ሜዳይ ፤ ኒሻን
He received a medal for bravery. የጀግንነት ፡ ሜዳይ ፡ (ኒሻን) ፡ አገኘ

**meddle** ገባ ፤ ጣልቃ ፡ ገባ
He likes to meddle in other people's business. በሌላ ፡ ሰው ፡ ጉዳይ ፡ መግባት ፡ (ጣልቃ ፡ መግባት) ፡ ይወዳል

**meddlesome** የእርጎ ፡ ዝንብ
His meddlesome wife is into everything he does. የእርጎ ፡ ዝንብ ፡ የሆነችው ፡ ሚስቱ ፡ እሱ ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ሁሉ ፡ ጥልቅ ፡ ትላለች

**media** ዘዴዎች
Radio is one of the news media. ራዲዮ ፡ ከወሬ ፡ ማሰራጫ ፡ ዘዴዎች ፡ አንዱ ፡ ነው

**medial** መሀከለኛ
The medial section is 15 cm. wide. የመሀከለኛው ፡ ክፍል ፡ ስፋት ፡ ዐሥራ ፡ አምስት ፡ ሳንቲሜትር ፡ ነው

**median** አማካይ ፡ ቁጥር
The median of 1, 3, 5, 8, 9 is 5. የ፩ ፤ ፫ ፤ ፭ ፤ ፰ ፤ ፱ ፡ አማካይ ፡ ቁጥር ፡ ፭ ፡ ነው

**mediate** በአስታራቂነት ፡ ገባ
Sweden will mediate in the dispute between the two countries. ስዊድን ፡ በሁለቱ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ በተፈጠረው ፡ ጭቅጭቅ ፡ በአስታራቂነት ፡ ትገባለች

**mediator** አስታራቂ
The mediator discussed the issue at length with both sides. አስታራቂው ፡ ስለ ፡ ጉዳዩ ፡ ከሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ጋር ፡ በሰፊው ፡ ተነጋገረ

**medical**

1. የሕክምና. He is attending medical school. በሕክምና ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በመማር ፡ ላይ ፡ ነው

2. የሐኪምነት. Family tradition destined him for the medical profession. የሐኪምነት ፡ ሥራ ፡ የዘራቸው ፡ በመሆኑ ፡ እሱም ፡ ሐኪም ፡ ሆነ

3. የጤንነት. During the President's illness, a medical bulletin was issued daily. ፕሬዚዳንቱ ፡ በታመመ ፡ ጊዜ ፡ የጤንነታቸው ፡ መግለጫ ፡ በየቀኑ ፡ ይወጣ ፡ ነበር

4. የጤና. A medical examination is required of all entrants. አዲስ ፡ ገቢዎች ፡ ሁሉ ፡ የጤና ፡ ምርመራ ፡ እንዲደረግላቸው ፡ ያስፈልጋል

**medical supplies** መድኃኒት
We need medical supplies because of the earthquake. በመሬቱ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ምክንያት ፡ ለደረሰው ፡ ጉዳት ፡ መድኃኒት ፡ ያስፈልገናል

**be under medical treatment** ታከመ
I am under medical treatment because of the car wreck. በመኪና ፡ አደጋ ፡ ለደረሰብኝ ፡ ጉዳት ፡ በመታከም ፡ ላይ ፡ ነኝ

**medicament** መድኃኒት
In the old days, they had few medicaments. በጥንት ፡ ጊዜ ፡ ሰዎች ፡ ጥቂት ፡ መድኃኒቶች ፡ ነበሯቸው

**medicate** ቀባ
The doctor medicated the wound with iodine. ሐኪሙ ፡ ቁስሉን ፡ አዮዲን ፡ ቀባው

**medicate oneself** መድኃኒት ፡ ወሰደ
It is often dangerous to medicate oneself without a doctor's advice. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሐኪም ፡ ሳያዝ ፡ መድኃኒት ፡ መውሰድ ፡ አደገኛ ፡ ነው

**be medicated** መድኃኒትነት ፡ አለው
These candies are medicated. ይህ ፡ ከረሜላ ፡ መድኃኒትነት ፡ አለው

**medication** መድኃኒት
I need some medication for my chapped lips. ለተሰነጣጠቀው ፡ ከንፈሬ ፡ መድኃኒት ፡ ያስፈልገኛል

**medicinal, ~ value** ፈዋሽነት
The medicinal value of this plant was discovered long ago. የዚህ ፡ ዕፅ ፡ ፈዋሽነት ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የታወቀ ፡ ነው

**have a medicinal taste** መድኃኒት ፡ መድኃኒት ፡ አለ
This liquor has a medicinal taste. ይህ ፡ የአልኮል ፡ መጠጥ ፡ መድኃኒት ፡ መድኃኒት ፡ ይላል

**medicine**

1. መድኃኒት. This medicine tastes bitter. ይህ ፡ መድኃኒት ፡ ይመራል

2. ሕክምና. My daughter is studying medicine. ልጄ ፡ ሕክምና ፡ ታጠናለች

**medieval** የመካከለኛ ፡ ዘመን
This country has medieval habits. ይህ ፡ አገር ፡ የመካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ጠባይ ፡ አለበት

**mediocre** ተራ
Despite the considerable research involved, the study is mediocre. ብዙ ፡ ጥናት ፡ የተደረገበት ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ ጽሑፉ ፡ ተራ ፡ ነው

**be mediocre**
*He is not an excellent student, just a mediocre one. ጎበዝ ፡ ተማሪ ፡ አይደለም ፤ ሆኖም ፡ ምንም ፡ አይል

**remain mediocre** ከምንም ፡ አይቈጠር
Even if we discount the irrelevant material, the thesis remains mediocre. የማይረባውን ፡ ጉዳይ ፡ እንኳ ፡ ከቁጥር ፡ ባናገባ ፡ ጹሑፉ ፡ ከምንም ፡ አይቈጠር

**meditate**

1. አወጣ ፡ አወረደ. The general was meditating on an attack. ጄኔራሉ ፡ ለማጥቃት ፡ ያወጣ ፡ ያወርድ ፡ ነበር
He meditated upon his misfortunes. ስለ ፡ መጥፎ ፡ ዕድሉ ፡ አወጣ ፡ አወረደ

2. አሰበ. He meditated revenge. ሊበቀል ፡ አሰበ

3. በአንክሮ ፡ አሰበ. Monks meditate on holy things for hours at a time. መነኰሴዎች ፡ ለብዙ ፡ ሰዓቶች ፡ ያለማቋረጥ ፡ ስለ ፡ ቅዱስ ፡ ነገሮች ፡ በአንክሮ ፡ ያስባሉ

**medium** (mediums, or media), n. ዘዴ
Radio is a medium of communication. ሬዲዮ ፡ የመገናኛ ፡ ዘዴ ፡ ነው
*A temperature of 70° is a happy medium. 70° ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ መሀከለኛ ፡ ሙቀት ፡ ነው

**through the medium of** በ
Vacant positions are made known through the medium of the press. ክፍት ፡ የሥራ ፡ ቦታዎች ፡ በጋዜጣ ፡ ላይ ፡ በማስታወቂያ ፡ ይወጣሉ

**medium** (adj.) መካከለኛ
He is of medium height. ቁመቱ ፡ መካከለኛ ፡ ነው

**medium-sized** መጠነኛ
It is a medium-sized business. መጠነኛ ፡ ንግድ ፡ ነው

**medley** ውጥንቅጥ
There is a medley of races in Hawaii. ሀዋዪ ፡ ውስጥ ፡ የዘር ፡ ውጥንቅጥ ፡ አለ

**meek** የዋህ

She is as meek as a dove. እንደ ፡ ርግብ ፡ የዋህ ፡ ናት

**be meek** ጠባዩ ፡ ለስላሳ ፡ ነው

His wife mistreats him because he is so meek. ጠባዩ ፡ ለስላሳ ፡ ስለሆነ ፡ ሚስቱ ፡ ታሠቃየዋለች

**meet** (met), vt.

1. አገኘ. Did you meet him on the street? መንገድ ፡ ነው ፡ ያገኘኸው ?

2. ተቀበለ. He met us with a smile. በፈገግታ ፡ ተቀበለን

I must go to the railway station and meet my mother. ወደ ፡ ባቡር ፡ ጣቢያ ፡ ሄጄ ፡ እናቴን ፡ መቀበል ፡ አለብኝ

3. ተዋወቀ. Pleased to meet you! ስለ ፡ ተዋወቅሁህ ፡ ደስ ፡ ብሎኛል

4. ከ - - ተዋወቀ. Have you met my sister? ከእኅቴ ፡ ጋር ፡ ተዋውቀሃል ?

5. ፈጸመ ፤ ፈጸመ(ለት). They couldn't meet their obligations. ግዳጃቸውን ፡ ለመፈጸም ፡ አልቻሉም

He met all my demands. የጠየቅሁትን ፡ ሁሉ ፡ ፈጸመልኝ

6. ከፈለ. He did not have enough money to meet his bills. ያለበትን ፡ ሒሳብ ፡ ለመክፈል ፡ የሚበቃ ፡ ገንዘብ ፡ አልነበረውም

7. ሸፈነ. I can barely meet my expenses. ወጪዬን ፡ የምሸፍነው ፡ በችግር ፡ ነው

8. ተቋቋመ. We must modify our requirements for admission to the university to meet the new situation. አዲሱን ፡ ሁኔታ ፡ ለመቋቋም ፡ ለዩኒቨርሲቲ ፡ መግቢያ ፡ የተደነገገውን ፡ ደንብ ፡ ማሻሻል ፡ አለብን

Whatever befalls them, they are ready to meet it. የሚያጋጥማቸውን ፡ ሁሉ ፡ ሊቋቋሙ ፡ ተዘጋጅተዋል

*We met the boat at 2 o'clock. በስምንት ፡ ሰዓት ፡ መርከቡ ፡ ሲመጣ ፡ እዚያ ፡ ነበርን

**meet** (vi.)

1. ተገናኘ. We meet once a week. በሳምንት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንገናኛለን

He met with the President and spoke with him for an hour. ከፕሬዚዳንቱ ፡ ጋር ፡ ተገናኝቶ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ አነጋገረው

The two ends don't meet. ሁለቱ ፡ ጫፎች ፡ አይገናኙም

2. ስብሰባ ፡ አደረገ. The Senate will meet next month. የሕግ ፡ መወሰኛው ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በሚመጣው ፡ ወር ፡ ስብሰባ ፡ ያደርጋል

3. ተሰበሰበ. The UN General Assembly meets tomorrow. የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ነገ ፡ ይሰበሰባል

4. ተጋጠመ. The two teams met to play for the African Cup. ሁለቱ ፡ ቡድኖች ፡ ለአፍሪካ ፡ ዋንጫ ፡ ተጋጠሙ

**be met** ሊፈጸም ፡ ቻለ ፤ ተፈጸመ

My demands are easily met. የጠየቅሁት ፡ በቀላሉ ፡ ሊፈጸም ፡ ይችላል

The stipulations have not been met, so the contract has been invalidated. በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሱት ፡ ግዴታዎች ፡ ስላልተፈጸሙ ፡ ውሉ ፡ ፈርሷል

**meet halfway**

*I am willing to meet him halfway. እሱም ፡ ይተው ፡ እኔም ፡ ልተው

**meet (one's) needs** አስፈለገው

They starved because they did not take enough food to meet their needs. የሚያስፈልጋቸውን ፡ ምግብ ፡ ባለ ፡ መያዛቸው ፡ ተራቡ

**meet with** አጋጠመ(ው)

On his trip in the desert, he met with misfortune and never returned. በበረሃው ፡ ሲጓዝ ፡ ባጋጠመው ፡ መጥፎ ፡ ዕድል ፡ ምክንያት ፡ እንደ ወጣ ፡ ቀረ

The proposal met with unexpected opposition. የቀረበው ፡ አስተያየት ፡ ያልታሰበ ፡ ተቃውሞ ፡ አጋጠመው

**meet with one's approval** በ - - ተስማማ

+Does this explanation meet with your approval? በዚህ ፡ ማብራሪያ ፡ ትስማማለህ ?

**make both ends meet** አብቃቃ

I am having difficulty on my salary making both ends meet. ደሞዜን ፡ ማብቃቃት ፡ አቅቶኛል

[See also 'death, disapproval, doom, end, obligation, refusal, response, reverse']

**meeting** ስብሰባ

There were five hundred people at the meeting. በስብሰባው ፡ ላይ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ

*I had a chance meeting with a friend. ጓደኛዬን ፡ የማግኘት ፡ ዕድል ፡ አጋጠመኝ

**meeting place** የሚገናኙበት ፡ ስፍራ

We chose a central meeting place. የምንገናኝበትን ፡ ማእከላዊ ፡ ስፍራ ፡ መረጥን

**arrange for a meeting** እንዲገናኙ ፡ አደረገ

I arranged for a meeting of the two. ሁለቱ ፡ እንዲገናኙ ፡ አደረግሁ

[See also 'order, summit']

**melancholy** (n.) ሐዘንና ፡ ትካዜ
He suffers from melancholy. በሐዘንና ፡ በትካዜ ፡ ተውጧል

**melancholy** (adj.) ሐዘንና ፡ ትካዜ ፡ ያጠቃው
Hamlet was a melancholy person. ሃምሌት ፡ ሐዘንና ፡ ትካዜ ፡ ያጠቃው ፡ ሰው ፡ ነበር

**mellow** (vt.) አለሰለሰ
Sorrow mellowed his nature. ሐዘን ፡ ጠባዩን ፡ አለሰለሰው

**mellow** (vi.) በሰለ
The mead has mellowed for two years. ጠጁ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ በመክረሙ ፡ በስሏል

**mellow** (adj.)
1. ረጋ ፡ ያለ. His father is a mellow old gentleman. አባቱ ፡ ረጋ ፡ ያሉ ፡ አዛውንት ፡ ናቸው
2. ለዛ ፡ ያለ. An expensive violin has a mellow tone. ውድ ፡ የሆነ ፡ ቫዮሊን ፡ ለዛ ፡ ያለው ፡ ድምፅ ፡ አለው
3. ጥዑም. This is a mellow wine. ይህ ፡ ጥዑም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ነው

**be mellow** በሰለ
If mangoes are not mellow, they have a sour taste. ማንጎ ፡ ካልበሰለ ፡ ይጎመዝዛል

**melodious** ለዛ ፡ ያለ
The priest's melodious voice makes the service beautiful. የቄሱ ፡ ለዛ ፡ ያለው ፡ ድምፅ ፡ ቅዳሴውን ፡ ያሳምራል

**melody** (melodies)
1. ዜፈን. We sang a familiar melody. አንድ ፡ የምናውቀውን ፡ ዜፈን ፡ ዘፈንን
2. ቃና ፡ ያለው ፡ ሙዚቃ. I heard him playing a wonderful melody. ግሩም ፡ ቃና ፡ ያለው ፡ ሙዚቃ ፡ ሲጫወት ፡ ሰማሁት

**melon** ሐብሐብ

**melt** (vt.)
1. አነጠረ. The good housewife gets up in the morning and melts butter. ባለሙያይቱ ፡ የቤት ፡ እመቤት ፡ ጧት ፡ ተነሥታ ፡ ቅቤ ፡ ታነጥራለች
He is melting gold in a melting pot. በማቅለጫው ፡ ውስጥ ፡ ወርቅ ፡ ያነጥራል
2. አሟሟ. He melted the sugar in hot water. ስኳሩን ፡ በሙቅ ፡ ውኃ ፡ አሟሟው
3. ውኃ ፡ አደረገ. Tears melt my heart. ለቅሶ ፡ ልቤን ፡ ውኃ ፡ ያደርገዋል

**melt** (vi.)
1. ሟሟ. Sugar melts in tea. ስኳር ፡ በሻይ ፡ ውስጥ ፡ ይሟሟል
The candy melted in his mouth. ከረሜላው ፡ አፉ ፡ ውስጥ ፡ ሟሟ
2. ቀለጠ. The butter melts easily on the fire. ቅቤ ፡ እሳት ፡ ሲነካው ፡ በቀላሉ ፡ ይቀልጣል
3. ልቡ ፡ ውኃ ፡ ሆነ. I melted at her smile. ፈገግ ፡ ስትል ፡ ልቤ ፡ ውኃ ፡ ሆነ

**melt away**
1. ተገፈፈ. The clouds melted away, and the sun came out. ደመናው ፡ ተገፈፈና ፡ ፀሐይ ፡ ወጣች
2. ጠፋ. His fear melted away. ፍርሃቱ ፡ ጠፋ

**melting pot** ማቅለጫ
He is melting gold in a melting pot. በማቅለጫው ፡ ውስጥ ፡ ወርቅ ፡ ያነጥራል

**member**
1. አባል. Are you a member of this club? የዚህ ፡ ክበብ ፡ አባል ፡ ነህ ?
He is a member of parliament. የፓርላማ ፡ አባል ፡ ነው
2. ከ - - አንዱ. A member of my family came to her wedding. ከቤተ ፡ ሰቦቼ ፡ አንዱ ፡ ለሰርጓ ፡ መጣ
3. ተከታይ. Christian practices have occasionally been adopted by members of other religions. አንዳንድ ፡ የክርስቲያን ፡ ምግባሮች ፡ በሌሎች ፡ እምነት ፡ ተከታዮች ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይነት ፡ አግኝተዋል
4. ባልደረባ. The members of the company have to report to their superior officer. የጓዱ ፡ ባልደረቦች ፡ ከበላይ ፡ መኰንኑ ፡ ዘንድ ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው
5. እጅና ፡ እግር. All his members were covered by a plaster cast. እጅና ፡ እግሩ ፡ በጄሶ ፡ ተሸፍኗል

**membership** (n.)
1. አባልነት. Membership in the organization costs $3.00 a year. በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ ላባልነት ፡ የሚከፈለው ፡ ገንዘብ ፡ በዓመት ፡ ሦስት ፡ ብር ፡ ነው
2. የአባሎች ፡ ቁጥር. Our membership is down to less than one hundred. የአባሎቻችን ፡ ቁጥር ፡ ከመቶ ፡ በታች ፡ ሆኗል

**membership** (adj.) የአባልነት
I don't have my membership card on me. የአባልነት ፡ መታወቂያ ፡ ወረቀቱን ፡ አልያዝኩም

**memento**
1. መታሰቢያ. He gave me a ring as a memento of our friendship. ለጓደኝነታችን ፡ መታሰቢያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ቀለበት ፡ ሰጠኝ
2. ማስታወሻ. He has some mementos of the

Italian occupation. ስለ ፡ ኢጣልያን ፡ ወረራ ፡ አንዳንድ ፡ ማስታወሻ ፡ ይዟል

*He wrote a book dealing with mementos of the past. የጥንት ፡ ነገሮችን ፡ የሚያወሳ ፡ መጽሐፍ ፡ ጽፏል

**memoirs**

1. የሕይወት ፡ ታሪክ. Winston Churchil wrote his memoirs. ዊንስተን ፡ ቸርችል ፡ የሕይወት ፡ ታሪኩን ፡ ጻፈ

2. ትዝታ. He wrote his father's memoirs. አባቱ ፡ ያላቸውን ፡ ትዝታ ፡ ጽፏል

**memorabilia** ትዝታ

His book is filled with memorabilia of the war years. መጽሐፉ ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ትዝታ ፡ የተሞላ ፡ ነው

**memorable** የማይረሳ

This was a memorable day. ይህ ፡ የማይረሳ ፡ ቀን ፡ ነበር

**memorandum** (memorandums, or memoranda) ማስታወሻ

Here is a memorandum from the Foreign Ministry. ከውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ የመጣ ፡ ማስታወሻ ፡ ይኸው

**memorial** (n.) መታሰቢያ ፡ ሐውልት

At Siddist Kilo, there is a memoral to the Yekatit massacre. ስድስት ፡ ኪሎ ፡ ላይ ፡ ለየካቲት ፡ እልቂት ፡ የቆመ ፡ መታሰቢያ ፡ ሐውልት ፡ አለ

**memorial service** የመታሰቢያ ፡ ጸሎት ፤ ተዝካር

They are holding a memorial service for my father. ላባቴ ፡ የመታሰቢያ ፡ ጸሎት ፡ ያደርጋሉ

Ethiopian Christians celebrate a memorial service on the fortieth day after burial. የኢትዮጵያ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሰው ፡ በሞተ ፡ ባርባኛው ፡ ቀን ፡ ተዝካር ፡ ያወጣሉ

**memorize** በቃል ፡ አጠና

I have to memorize my speech. ንግግሬን ፡ በቃል ፡ ማጥናት ፡ አለብኝ

**memory** (memories)

1. ትዝታ. I have pleasant memories of this town. ይህ ፡ ከተማ ፡ ጥሩ ፡ ትዝታ ፡ ቀርጾብኛል

His memory will serve as an inspiration to posterity. ትዝታው ፡ የትውልድን ፡ መንፈስ ፡ ያነቃቃል

2. ማስታወስ. He suffers from an occasional lapse of memory. አንዳንዴ ፡ የማስታወስ ፡ ችግር ፡ አለበት

3. የማስታወስ ፡ ችሎታ. My memory is not what it used to be. የማስታወስ ፡ ችሎታዬ ፡ እንደ ፡ ድሮው ፡ አይደለም

**from memory** በቃሉ

He recited the poem from memory. ግጥሙን ፡ በቃሉ ፡ ወጣው

**have a good memory**

*He has a good memory for names. ስም ፡ የማስታወስ ፡ ጥሩ ፡ ችሎታ ፡ አለው

**have a poor memory**

*I have a poor memory for names. ስም ፡ ማስታወስ ፡ አይሆንልኝም

**honor the memory**

*We honor the memory of our heroes. የጀግኖቻችንን ፡ መታሰቢያ ፡ እናከብራለን

**in memory of** ለ - - - መታሰቢያ

The inscription reads: "In memory of ...". የተቀረጸው ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ « ለ - - - መታሰቢያ »

**retain a memory of** አስታወሰ

She retains a clear memory of her childhood. የልጅነት ፡ ጊዜዋን ፡ በደንብ ፡ ታስታውሳለች

**within one's memory** እሱ ፡ እንደሚያውቀው ፡ ከሆነ

This has been the hottest summer within my memory. እኔ ፡ እንደማውቀው ፡ ከሆነ ፡ የዘንድሮ ፡ በጋ ፡ ከመቼውም ፡ ይበልጥ ፡ ሞቃት ፡ ነው

[See also 'lapse, lose, refresh, search']

**men,** see **man**

**menace** (v.) አሰጋ

War menaces the entire world. ጦርነት ፡ መላውን ፡ ዓለም ፡ ያሰጋዋል

**menace** (n.)

1. ዛቻ. The radio broadcast a speech filled with menace. ዛቻ ፡ የሞላበት ፡ ንግግር ፡ በራዲዮ ፡ ተላለፈ

2. ጠንቅ. He is a menace to society. ለኅብረተ ፡ ሰቡ ፡ ጠንቅ ፡ ነው

**mend**

1. ጠቀመ. When will you mend my shirts? ሸሚዜን ፡ መቼ ፡ ትጠቅምልኛለህ ?

2. ጠገነ. The workers are mending the road. ሠራተኞቹ ፡ መንገዱን ፡ በመጠገን ፡ ላይ ፡ ናቸው

3. አሻሻለ. You'll have to mend your ways. ጠባይህን ፡ ማሻሻል ፡ አለብህ

**mendacious** ዋሾ

The mendacious old man cheated me again. ዋሾው ፡ ሽማግሌ ፡ እንደገና ፡ አታለለኝ

**mendacity** ዋሾነት
His mendacity is well known, so don't trust him. ዋሾነቱ ፡ የታወቀ ፡ ስለሆነ ፡ አትመነው

**mendicant** ለማኝ
Mendicants are forbidden to sit in front of our hotel. ለማኞች ፡ ሆቴላችን ፡ ደጃፍ ፡ እንዳይ ቀመጡ ፡ ተከልክለዋል

**mendicity** መለመን
Mendicity is not allowed in the streets. መንገድ ፡ ላይ ፡ መለመን ፡ አይፈቀድም

**menial** ዝቅተኛ
She spends a lot of time on menial tasks such as washing dishes. ሳሕን ፡ ማጠብን ፡ በመሳሰሉ ፡ ዝቅተኛ ፡ ሥራዎች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ታጠፋለች

**menses**
She is having her menses. ጾጌ ፡ ነች

**menstruate** አደፈች
Women menstruate from the time they become sexually mature. ሴቶች ፡ ለዐቅመ ፡ ሔዋን ፡ ከ ደረሱበት ፡ ጀምሮ ፡ ያድፋሉ

**menstruation** አደፍ
Menstruation occurs once a month. ሴት ፡ ልጅ ፡ አደፍ ፡ የሚታያት ፡ በወር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነው

**mental**
1. የአእምሮ. Her illness is mental, not physical. በሽታዋ ፡ የአእምሮ ፡ እንጂ ፡ የሰውነት ፡ አይደለም
Mental patients must be treated like those who suffer from diseases of the flesh. የአእም ሮ ፡ ሕመምተኞች ፡ እንደ ፡ አካል ፡ በሽተኞ ች ፡ መታየት ፡ አለባቸው
2. የእብዶች. A mental hospital treats the insane. የእብዶች ፡ ሆስፒታል ፡ የአእምሮ ፡ ሕ መምተኞችን ፡ ያክማል

**mental institution** የአእምሮ ፡ በሽተኞች ፡ ሐኪ ም ፡ ቤት
One of the inmates of the mental institution escaped. የአእምሮ ፡ በሽተኞች ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ነዋሪ ፡ ከሆኑት ፡ በሽተኞች ፡ አንዱ ፡ አ መለጠ

**mentality** (mentalities)
1. አስተሳሰብ. His mentality is that of a five year old. አስተሳሰቡ ፡ እንደ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነው
2. የአእምሮ ፡ ችሎታ. He is a person of average mentality. መካከለኛ ፡ የአእምሮ ፡ ችሎታ ፡ ያለ ው ፡ ሰው ፡ ነው

**mentally**
*He is mentally ill. የአእምሮ ፡ በሽተኛ ፡ ነው
*He is strong mentally. አእምሮው ፡ ንቁ ፡ ነው
[See also 'deficient, disturbed, retard, unbalanced']

**mention** (v.)
1. ተናገረ. He didn't mention the price. ዋጋውን ፡ አልተናገረም
2. አነሣ ፤ ጠራ. I heard his name mentioned. ስሙን ፡ ሲያነሡ ፡ ሰማሁ
Mention my name, and you will be admitted. ስሜን ፡ ጥራ ፡ ያስገቡሃል
3. ጠቀሰ. I would also like to mention that … . በተጨማሪ ፡ ልጠቅሰው ፡ የምፈልገው

**don't mention it!** ምንም ፡ አይደል
Thank you, Mrs. Graham. Don't mention it! እግዚር ፡ ይስጥልኝ ፡ ሚሲስ ፡ ግራሃም ፤ ምንም ፡ አይደል !

**not to mention** -ማ ፡ ተወው
I enjoyed the meal, not to mention the conversation. ምግቡ ፡ በጣም ፡ አስደሰተኝ ፤ ጨዋታ ውንማ ፡ ተወው
*We are too busy to take a holiday, not to mention the fact that we can't afford it. ወጪው ን ፡ ካለመቻላችንም ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ ስለሚበዛብን ፡ ለዕረፍት ፡ ለመሄድ ፡ አንችልም

**mention** (n.) ማንሣት
Mention of the incident caused surprise. ነገ ሩን ፡ ማንሣቱ ፡ አስገረመን

**mention is given** ተጠቀሰ
A brief mention of the flood was given in the newspaper. ስለ ፡ ውኃው ፡ መጥለቅለቅ ፡ ጋዜጣ ው ፡ ውስጥ ፡ ባጭሩ ፡ ተጠቅሷል

**make mention** ጠቀሰ
He made mention of his coming to Ethiopia. ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መምጣቱን ፡ ጠቀሰ

**receive honorable mention** ስሙ ፡ በክብር ፡ ተጠራ
He didn't win a prize, but received honorable mention. ሽልማት ፡ ባያገኝም ፡ ስሙ ፡ በክብር ፡ ተጠርቷል

**mentioned, above ~** ከላይ ፡ የተጠቀሰ
The above-mentioned people will not be admitted to class. ከላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ሰዎች ፡ ክፍል ፡ እንዲገቡ ፡ አይፈቀድላቸውም

**menu** የምግብ ፡ ዝርዝር
The waiter brought me the menu. አሳላፊው ፡ የ ምግብ ፡ ዝርዝር ፡ አቀረበልኝ

**mercantile** የንግድ
Mercantile law specifies how contracts must be drawn up. የንግድ ፡ ሕግ ፡ ውል ፡ እንዴት ፡ መዋዋል ፡ እንደሚገባ ፡ ይወስናል

**mercenary** (mercenaries), n. ቅጥር ፡ ወታደር
The mercenaries deserted when they were not paid. ቅጥር ፡ ወታደሮቹ ፡ ደሞዝ ፡ ሳይከፈላቸው ፡ በቀረ ፡ ጊዜ ፡ ከዱ

**mercenary,** adj. (= adv.) ለገንዘብ ፡ ሲል
His mercenary reasons for helping the rich man were soon discovered. ሀብታሙን ፡ ሰው ፡ የሚረዳው ፡ ለገንዘብ ፡ ሲል ፡ መሆኑ ፡ ወዲያው ፡ ታወቀ

**merchandise** (v.) ነገደ
My father merchandises office furniture. አባቴ ፡ የቢሮ ፡ እቃ ፡ ይነግዳል

**merchandise** (n.) ሸቀጣ ፡ ሸቀጥ
The merchandise arrived in good order. ሸቀጣ ፡ ሸቀጡ ፡ በደኅና ፡ ሁኔታ ፡ ደርሷል

**merchant** (n.) ነጋዴ
The merchants live in a special quarter. ነጋዴዎቹ ፡ በተለየ ፡ ሰፈር ፡ ይኖራሉ

**merchant** (adj.) የንግድ
Ethiopia's merchant marine is still small. የኢትዮጵያ ፡ የንግድ ፡ መርከቦች ፡ አሁንም ፡ ጥቂት ፡ ናቸው
[See also 'retail']

**(be) merciful** ራራ
The judge was merciful to the offender. ዳኛው ፡ ለጥፋተኛው ፡ ራራለት

**merciless** ጨካኝ
The people did not like the merciless ruler. ሕዝቡ ፡ ጨካኙን ፡ ገዢ ፡ አልወደደውም

**mercilessly** ያለ ፡ ርኅራኄ
He whipped the horse mercilessly. ፈረሱን ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ ፡ ገረፈው

**mercury** ባዜቃ
If you swallow mercury, you will get sick. ባዜቃ ፡ ከዋጥክ ፡ ትታመማለህ

**mercy** ምሕረት
He pleaded for mercy, but the judge sentenced him to death. ምሕረት ፡ እንዲደረግለት ፡ ለመነ ፤ ግን ፡ ዳኛው ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ፈረደበት
He has no mercy. ምሕረት ፡ የለውም

**at the mercy of**
*He is at the mercy of his employer. ቀጣሪው ፡ እንዳሻው ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል

**have mercy on** ይቅር ፡ አለ
Have mercy on the poor sinner! ምስኪኑን ፡ ኀጢአተኛ ፡ ይቅር ፡ በለው

**show mercy** ምሕረት ፡ አደረገ
They showed mercy to the defeated enemy. ለተሸነፈው ፡ ጠላት ፡ ምሕረት ፡ አደረጉ

**mere,** adj. (= adv.) ብቻ
The mere thought of it disturbs me. ማሰቡ ፡ ብቻ ፡ ይረብሸኛል
The mere sight of a dog makes him afraid. ውሻ ፡ ማየቱ ፡ ብቻ ፡ ያስፈራዋል

**merely**
1. እንዲያው. I was merely joking. እንዲያው ፡ ቀልዴን ፡ ነበር
2. ዝም ፡ ብሎ. The police did nothing to stop the rioters, but merely looked on. ፖሊሶቹ ፡ ረብሸኞቹን ፡ ለማቆም ፡ እርምጃ ፡ ሳይወስዱ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ይመለከቷቸው ፡ ነበር

**merest** በጣም ፡ አነስተኛ
The merest trifle upsets him. በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ነገር ፡ ያበሳጨዋል

**merge** (vt.) አዋሐደ
The big company merged various small businesses. ትልቁ ፡ ኩባንያ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አነስተኛ ፡ ንግዶችን ፡ አዋሐደ

**merge** (vi.)
1. ተዋሐደ. The two companies merged into one. ሁለቱ ፡ ኩባንያዎች ፡ ተዋሐዱ
2. ተቀላቀለ. The blue slowly merges into the green. ሰማያዊው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ከአረንጓዴው ፡ ጋር ፡ ይቀላቀላል
3. ተጋጠመ. Traffic merges here. መንገዱ ፡ እዚህ ፡ ይጋጠማል

**meridian** [ደቡባዊውንና ፡ ሰሜናዊውን ፡ ዋልታ ፡ ያገናኛል ፡ የሚባለው ፡ መሥመር ፡ «ሜሪዲየን» ፡ ይባላል]

**merit** (v.) ተገባ(ው)
+I think he merits a raise. የደሞዝ ፡ ጭማሪ ፡ የሚገባው ፡ ይመስለኛል

**merit** (n.), **merits**
1. መልካም ፡ ሥራ. His merits have been widely recognized. መልካም ፡ ሥራው ፡ በሰፊው ፡ ታውቆለታል
2. መልካም ፡ ተግባር. His vanity detracts from his merits. ግብዝነቱ ፡ መልካም ፡ ተግባሩን ፡ ይቀንስበታል
3. ችሎታ. His merits as a teacher have been

recognized. ያስተማሪነት ፡ ችሎታው ፡ ታውቆለታል
Promotion should be made on the basis of merit. የሥራ ፡ እድገት ፡ በችሎታ ፡ መሠረት ፡ መሆን ፡ አለበት
4. ሁኔታ. Judge the case on its merits, not on your feelings! ጉዳዩን ፡ እንደ ፡ ሁኔታው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ስሜትህ ፡ አትፍረድ
*There isn't much merit in giving away things you don't want. የማትፈልገውን ፡ ነገር ፡ መስጠት ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የሚያስመሰግን ፡ አይደለም

**meritorious** አስመስጋኝ ፤ ዝና ፡ የሚያተርፍ
He received a medal for meritorious conduct. ባስመስጋኝ ፡ ሥራው ፡ ሜዳይ ፡ ተሸለመ
The saving of lives is a meritorious action. የሰውን ፡ ሕይወት ፡ ማዳን ፡ ዝና ፡ የሚያተርፍ ፡ ተግባር ፡ ነው

**merriment** ቡረቃ
The children's merriment annoyed the old man. የልጆቹ ፡ ቡረቃ ፡ ሽማግሌውን ፡ አበሳጨው

**merry** ደስተኛ
She is always merry. ሁልጊዜ ፡ ደስተኛ ፡ ናት
**Merry Christmas!** እንኳን ፡ ለብርሃን ፡ ልደቱ ፡ አደረሳችሁ !
**make merry** ፈንጠዝያ ፡ አደረገ
They were making merry during the holidays. በበዓሉ ፡ ጊዜ ፡ ፈንጠዝያ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር
[See also 'vein']

**merry-go-round** [በሞተር ፡ የሚዞር ፡ ክብ ፡ የሆነ ፡ መድረክ ፤ በላዩ ፡ ላይ ፡ አግዳሚ ፡ ወንበሮችና ፡ ከዕንጨት ፡ የተቀረጹ ፡ ፈረሶች ፡ ያሉበት]

**merrymaking** ፈንጠዝያ
Sounds of merrymaking came from the house. የፈንጠዝያ ፡ ድምፅ ፡ ከቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ይሰማል

**mesh** (v.) ተገጣጠመ
The teeth of a zipper mesh. የዚፐር ፡ ጥርስ ፡ ይገጣጠማል

**mesh** (n.) ቀዳዳ
The net has five-inch meshes. መረቡ ፡ አምስት ፡ ኢንች ፡ ስፋት ፡ ያላቸው ፡ ቀዳዳዎች ፡ አሉት

**mess** (v.), ~ **around** ተንጐዳጐደ
She likes to mess around at home. እቤት ፡ ውስጥ ፡ መንጐዳጐድ ፡ ትወዳለች

**mess up**
1. አዘበራረቀ. Who messed up the papers on my desk? ጠረጴዛዬ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ወረቀት ፡ ማን ፡ አዘበራረቀው ?
2. አጨማለቀ. Don't mess up the floor with your wet feet! በርጥብ ፡ እግርህ ፡ ወለሉን ፡ አታጨማልቅ
3. አቃወሰ(በት). The late arrival of the train messed up our plans. የባቡሩ ፡ ዘግይቶ ፡ መድረስ ፡ ሐሳባችንን ፡ ሁሉ ፡ አቃወሰብን

**mess** (n.)
1. ምግብ ፡ ቤት. Common soldiers cannot eat at the officers' mess. ተራ ፡ ወታደሮች ፡ መኰንኖች ፡ ምግብ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ እንዲበሉ ፡ አይፈቀድላቸውም
2. ጣጣ. Cheating got him into a mess. ቅጥፈት ፡ ጣጣ ፡ ውስጥ ፡ ከተተው
3. ቆሻሻ. Call the janitor and have him clean up the mess! ጠራጊውን ፡ ጥራና ፡ ቆሻሻ ፡ እንዲጠርግ ፡ ንገረው
4. ምስቅልቅል. The house is in an awful mess. ቤቱ ፡ ምስቅልቅሉ ፡ ወጥቷል
5. ውጥንቅጥ. I can't find anything in this mess. በዚህ ፡ ውጥንቅጥ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ላገኝ ፡ አልችልም
6. ዝብርቅርቅ. He burdened me with the responsibility of cleaning up the mess. ይህን ፡ ዝብርቅርቅ ፡ እንዳስተካክል ፡ ኀላፊነት ፡ ጫነብኝ
7. ዝርክርክ. She's a mess! ዝርክርክ ፡ ነች
**make an awful mess** አዝረከረከ
When the baby got into the flour, he made an awful mess. ልጁ ፡ ዱቄቱ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ አዝረከረከው

**message** መልእክት
Is there a message for me? ለኔ ፡ መልእክት ፡ አለ ?
He found a message written in code. በምስጢር ፡ ጽሑፍ ፡ የተጻፈ ፡ መልእክት ፡ አገኘ

**messenger**
1. መልእክተኛ. The messenger is waiting for your reply. መልእክተኛው ፡ መልስህን ፡ ይጠብቃል
2. አብሳሪ. Dawn is the messenger of the day. ጎሕ ፡ የቀን ፡ አብሳሪ ፡ ነው

**Messiah** መሲሕ
Some religions wait for the arrival of the Messiah. አንዳንድ ፡ ሃይማኖቶች ፡ መሲሕ ፡ ይመጣልናል ፡ ብለው ፡ ይጠብቃሉ

**messy**
1. የተዝረከረከ. I have to put my messy room in order. የተዝረከረከውን ፡ ክፍሌን ፡ ማደራጀት ፡ አለብኝ

2. የተበላሸ. There was a messy political situation in the Congo. በኮንጎ ፡ ውስጥ ፡ የተበላሸ ፡ የፖለቲካ ፡ ሁኔታ ፡ ነበር

**be messy** ዝብርቅርቅ ፡ አለ
The kitchen was messy. ማድ ፡ ቤቱ ፡ ዝብርቅርቅ ፡ ብሎ ፡ ነበር

**met,** see **meet**

**metal** (n.)
1. ብረት. Gold is a precious metal. ወርቅ ፡ የከበረ ፡ ብረት ፡ ነው
Is it made of wood or metal? የተሠራው ፡ ከዕንጨት ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ከብረት ?
2. ብረታ ፡ ብረት. Cars are made of metal. መኪናዎች ፡ ከብረታ ፡ ብረት ፡ ይሠራሉ
Copper is a metal. መዳብ ፡ ከብረታ ፡ ብረቶች ፡ አንዱ ፡ ነው

**metal** (adj.) ከብረት ፡ የተሠራ
He washed his hands in a metal basin. እጆቹን ፡ ከብረት ፡ በተሠራ ፡ ጐድጓዳ ፡ ሳሕን ፡ ውስጥ ፡ ታጠበ
[See also 'sheet']

**mete, ~ out** ወሰነ
The judge meted out punishment to each criminal. ዳኛው ፡ ለያንዳንዱ ፡ ወንጀለኛ ፡ ቅጣት ፡ ወሰነ

**meteor** በራሪ ፡ ኮከብ
A meteor was seen in the sky last night. በራሪ ፡ ኮከብ ፡ ትናንት ፡ ማታ ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ታየ

**meteorology** ያየር ፡ ጠባይ ፡ ትምህርት
Meteorology instructs us about atmospheric changes. ያየር ፡ ጠባይ ፡ ትምህርት ፡ ስለ ፡ አየር ፡ መለዋወጥ ፡ ያስረዳል

**meter**
1. ሜትር. A meter is about one yard long. አንድ ፡ ሜትር ፡ አንድ ፡ ያርድ ፡ ያህል ፡ ይረዝማል
2. ቈጣሪ. The water meter is not working. ውኃ ፡ ቈጣሪው ፡ አይሠራም
3. ምጣኔ. Poetry is written in various meters. ግጥም ፡ በተለያየ ፡ ምጣኔ ፡ ይጻፋል

**method** ዘዴ
Broiling is a common method of cooking meat. መጥበስ ፡ የተለመደ ፡ የሥጋ ፡ ማብሰያ ፡ ዘዴ ፡ ነው
This student worked with method. ይህ ፡ ተማሪ ፡ በዘዴ ፡ አጠና

**methodical**
1. ሥርዓት ፡ ያለው. His wife is a methodical housekeeper. ሚስቱ ፡ በቤት ፡ አያያዝ ፡ ሥርዓት ፡ ያላት ፡ ናት
2. (= adv.) በዘዴ. His methodical habits enable him to solve many problems. በዘዴ ፡ የመሥራት ፡ ልማዱ ፡ ለብዙ ፡ ችግሮች ፡ መፍትሔ ፡ እንዲያገኝ ፡ ያስችለዋል

**meticulous** ጥንቁቅ
He is very meticulous in his work. በሥራው ፡ በጣም ፡ ጥንቁቅ ፡ ነው

**metric**
*Ethiopia uses the metric system. ኢትዮጵያ ፡ በሜትር ፡ ላይ ፡ በተመሠረተ ፡ መለኪያ ፡ ዘዴ ፡ ትሠራለች

**metropolis** ትልቅ ፡ ከተማ
New York is a metropolis. ኒው ፡ ዮርክ ፡ ትልቅ ፡ ከተማ ፡ ነው

**mew** ሙኸ
The kittens mewed loudly. ድመቶቹ ፡ በኀይል ፡ ሙኹ

**mice,** see **mouse**

**microbe(s)** ረቂቅ ፡ ነፍሳት
Microbes can be seen only through the microscope. ረቂቅ ፡ ነፍሳትን ፡ ማየት ፡ የሚቻለው ፡ በማጕያ ፡ መነጽር ፡ ብቻ ፡ ነው

**microphone** ድምፅ ፡ ማጕያ
Please use the microphone so everybody can hear you. ሁሉ ፡ ሰው ፡ ሊሰማህ ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ በድምፅ ፡ ማጕያው ፡ ተናገር

**microscope** የማጕያ ፡ መነጽር
Our laboratory bought a new microscope. ቤተ ፡ ሙከራችን ፡ አዲስ ፡ የማጕያ ፡ መነጽር ፡ ገዛ

**mid** አጋማሽ
The term lasts from mid-June to mid-August. ተርሙ ፡ ከሰኔ ፡ አጋማሽ ፡ እስከ ፡ ነሐሴ ፡ አጋማሽ ፡ ይቆያል

**midair, in ~** ሰማይ ፡ ላይ
The bomb exploded in midair. ቦምቡ ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ ፈነዳ

**midday** (n.) ቀትር ፡ ጊዜ
The town is quiet at midday because of the heat. ከሙቀቱ ፡ የተነሣ ፡ ከተማው ፡ በቀትር ፡ ጊዜ ፡ ጭር ፡ ይላል

**midday** (adj.) በቀትር ፡ የሚደረግ
The midday rest period in hot countries is

called the siesta. በሞቃት ፡ አገሮች ፡ በቀትር ፡ የ ሚደረገው ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ ሲዬስታ ፡ ይባላል

**midday meal** ምሳ
I take my midday meals in the hotel. ምሳዬን ፡ የምበላው ፡ ሆቴል ፡ ነው

**midday sun** የጠራራ ፡ ፀሐይ
Don't go out in the midday sun! በጠራራ ፡ ፀሐ ይ ፡ አትውጣ

**middle** (n.)
1. ወገብ. He seized her around the middle. ወገቧን ፡ አቅፎ ፡ ያዛት
2. አጋማሽ. I'm leaving the middle of next week. በሚመጣው ፡ ሳምንት ፡ አጋማሽ ፡ ላይ ፡ እሄዳለሁ
3. መኻል. The man collapsed in the middle of the street. ሰውዬው ፡ መንገዱ ፡ መኻል ፡ ተዝ ለፍልፎ ፡ ወደቀ
*They were in the middle of dinner when I called. ስደውልላቸው ፡ ራት ፡ ይበሉ ፡ ነበር
*He's put on weight around the middle. ቦርጭ ፡ አውጥቷል

**middle** (adj.) መካከለኛ ፤ መሀከለኛ
Open the middle window! መካከለኛውን ፡ መስኮ ት ፡ ክፈት
He is a man of middle height. መሀከለኛ ፡ ቁመ ት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነው
*He is in his middle forties. ዕድሜው ፡ ወደ ፡ አርባ ፡ አምስቱ ፡ ነው
[See also 'finger']

**middle-aged** ጠና ፡ ያለ
He is a middle-aged man and is still strong. ጠና ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ቢሆንም ፡ ጠንካራ ፡ ነው

**Middle Ages** መካከለኛ ፡ ዘመን
The Middle Ages stretched from the fifth to the fifteenth century. መካከለኛው ፡ ዘመን ፡ ከአ ምስተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አምስ ተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ነበር

**middle class** መካከለኛ ፡ ገቢ ፡ ያለው ፡ ሕዝብ
The middle class was hard hit because of the war. በጦርነቱ ፡ ምክንያት ፡ መካከለኛ ፡ ገቢ ፡ ያ ለው ፡ ሕዝብ ፡ በጣም ፡ ተጐዳ

**Middle East** መካከለኛ ፡ ምሥራቅ
He is studying in the Middle East. መካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ ውስጥ ፡ በመማር ፡ ላይ ፡ ይገኛል

**middleman** አትራፊ
Don't deal with middlemen; write directly to the manufacturer! ከአትራፊ ፡ ጋር ፡ አትዋዋል ፤ ቀጥታ ፡ ለባለፋብሪካው ፡ ጻፍ

**midget** ድንክ
In olden times, midgets used to be chosen as palace jesters. በጥንት ፡ ጊዜ ፡ ድንኮች ፡ ለቤተ ፡ መንግሥት ፡ አጫዋችነት ፡ ይመረጡ ፡ ነበር

**midnight** እኩለ ፡ ሌሊት
It was past midnight when we fell asleep. እንቅልፍ ፡ ሲወስደን ፡ እኩለ ፡ ሌሊት ፡ አልፎ ፡ ነበር

**midst, in the ~** በ - - መሃከል
In the midst of the crowd, we saw a policeman. በተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መሃከል ፡ አንድ ፡ ፖሊስ ፡ አየን

**midway** አማካይ ፡ ስፍራ
Addis Ababa is approximately midway between Asmara and Nairobi. ከሞላ ፡ ጐደል ፡ አ ዲስ ፡ አበባ ፡ ለአሥመራና ፡ ለናይሮቢ ፡ አማካይ ፡ ስ ፍራ ፡ ናት

**midway through** በ - - - አጋማሽ ፡ ላይ
He caught cold midway through the campaign. በውድድሩ ፡ አጋማሽ ፡ ላይ ፡ ጉንፋን ፡ ያዘው

**midwife** አዋላጅ
Call the midwife when the labor pains begin. ምጥ ፡ ሲይዛት ፡ አዋላጇን ፡ ጥራ

**midyear** የዓመት ፡ አጋማሽ
He just passed his midyear examination. የዓመት ፡ አጋማሽ ፡ ፈተናውን ፡ ገና ፡ ማለፉ ፡ ነው
This store has a midyear sale. ይህ ፡ መደብር ፡ የዓመት ፡ አጋማሽ ፡ ሽያጭ ፡ አለው

**might** (n.)
1. ጉልበት. He works with all his might. ባለው ፡ ጉልበት ፡ ሁሉ ፡ ይሠራል
2. ኀይል. Might does not make right. ኀይል ፡ መብት ፡ አይደለም

**might,** see **may**

**mightily** በጣም
The workers tried mightily to finish before dark. ሠራተኞቹ ፡ ከመምሸቱ ፡ በፊት ፡ ለመጨረ ስ ፡ በጣም ፡ ጣሩ

**mighty** (adj.)
1. ታላቅ. He is a mighty man from a mighty nation. ከታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ የመጣ ፡ ታላቅ ፡ ሰው ፡ ነው
2. ኀይለኛ ፤ ጐበዝ. Theodore was a mighty warrior. ቴዎድሮስ ፡ ኀይለኛ ፡ (ጐበዝ) ፡ ጦረኛ ፡ ነበር

**mighty** (adv.) በጣም
I was mighty glad to see him again. እንደገና ፡ ሳ የው ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ አለኝ

He has done mighty little work today. ዛሬ ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ሥርቶ ፡ ዋለ

**migraine** ኀይለኛ ፡ የራስ ፡ ምታት
He has been suffering from migraines lately. ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ኀይለኛ ፡ የራስ ፡ ምታት ፡ ያመዋል

**migrant** ተዘዋዋሪ
He hired migrant workers to harvest his fruit. ፍሬ ፡ ለማስለቀም ፡ ተዘዋዋሪ ፡ ሠራተኞች ፡ ቀጠረ

**migrate**
1. ፈለሰ. The Galla migrated from the South and settled in central Ethiopia. ጋሎች ፡ ከደቡብ ፡ ፈልሰው ፡ መሀል ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰፈሩ
2. ተጓዘ. Ducks and geese migrate southward in the fall. ዳክዬና ፡ ዝዬ ፡ በመፀው ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ይጓዛሉ

**migrate into** ወደ --- ፡ ፈልሶ ፡ ገባ
The Arabs migrated across the Red Sea into Ethiopia. ዐረቦች ፡ ቀይ ፡ ባሕርን ፡ ተሻግረው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ፈልሰው ፡ ገቡ

**migration**
1. ከቦታ ፡ ወደ ፡ ቦታ ፡ መዘዋወር. The government is trying to prevent the migration of the nomads. መንግሥቱ ፡ የዘላኖችን ፡ ከቦታ ፡ ወደ ፡ ቦታ ፡ መዘዋወር ፡ ለመከልከል ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ነው
2. (= verb) ፈለሰ. The migration of the Boers was from the coast into the interior. ቦሮች ፡ ከጠረፍ ፡ ፈልሰው ፡ ወደ ፡ መሀል ፡ ገቡ

**migratory** ተዘዋዋሪ
Migratory workers travel about from one job to another. ተዘዋዋሪ ፡ ሠራተኞች ፡ ካንዱ ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ይዘዋወራሉ

**mild**
1. ቀላል. He received only a mild punishment for his crime. ለወንጀሉ ፡ ቀላል ፡ ቅጣት ፡ ተቀበለ
2. ገር. He is a mild person who wouldn't harm a soul. ማንንም ፡ ለመጒዳት ፡ የማይፈልግ ፡ ገር ፡ ሰው ፡ ነው
3. ለስላሳ. They prefer mild tobacco for cigarettes. ሲጋራ ፡ ለመሥራት ፡ ለስላሳ ፡ ትምባሆ ፡ ይመርጣሉ
This sauce is mild. ይህ ፡ ወጥ ፡ ለስላሳ ፡ ነው
4. መካከለኛ. Because Addis Ababa is in the mountains, it has a mild climate. አዲስ ፡ አበባ ፡ በተራራዎች ፡ መሀከል ፡ በመሆኗ ፡ መካከለኛ ፡ አየር ፡ አላት

**mildew**
1. ሻጋታ. The bread is full of mildew. እንጀራው ፡ ሻጋታ ፡ በዝቶበታል
2. መሻገት. The moisture in the air causes mildew. ያየር ፡ ርጥበት ፡ መሻገትን ፡ ይፈጥራል

**be covered with mildew** ሻገተ
The bread is covered with mildew. ዳቦው ፡ ሻግቷል

**mile** ማይል
He ran a mile in 4 minutes. ባራት ፡ ባራት ፡ ደቂቃ ፡ አንድ ፡ ማይል ፡ ሮጠ
[See also 'stretch']

**mileage**
*His mileage on the trip to Asmara was close to five hundred. አሥመራ ፡ ሲሄድ ፡ ወደ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ማይል ፡ ርቀት ፡ ደርሶ ፡ ነበር
*He gets good mileage from a gallon of gasoline. ባንድ ፡ ጋሎን ፡ ቤንዚን ፡ ብዙ ፡ ማይል ፡ ይሄዳል

**milestone**
1. ርቀት ፡ የሚያመለክት ፡ ድንጋይ. The milestone shows the town is ten miles away. ርቀት ፡ የሚያመለክተው ፡ ድንጋይ ፡ ከተማው ፡ ዐሥር ፡ ማይል ፡ መራቁን ፡ ያሳያል
2. አዲስ ፡ ምዕራፍ. The coming of the Portuguese is a milestone in Ethiopian history. የፖርቱጊዞች ፡ መምጣት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ አዲስ ፡ ምዕራፍ ፡ ነው

**militant**
1. ለመዋጋት ፡ የቈረጠ. A militant defender of freedom is prepared to fight in its defense. ለመዋጋት ፡ የቈረጠ ፡ ጀግና ፡ ለነጻነት ፡ ለመዋጋት ፡ ዝግጁ ፡ ነው
2. ነውጠኛ. The crowd was led by a militant leader. የተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ በነውጠኛ ፡ መሪ ፡ ይመራ ፡ ነበር

**become militant** ለመዋጋት ፡ ቈረጠ
The Indians became very militant as settlers began to move west. መጤዎቹ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ሲገፉ ፡ ህንዶች ፡ ለመዋጋት ፡ ቈረጡ

**militarism** በጦር ፡ ኀይል ፡ መተማመን
The UN tries to combat militarism. የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ በጦር ፡ ኀይል ፡ መተማመንን ፡ ለመቋቋም ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ነው

**militarize** በጦር ፡ ኀይል ፡ አደረጀ
Hitler militarized Germany after 1933. ሂትለር ፡ ከ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ. ም. በኋላ ፡ ጀርመንን ፡ በጦር ፡ ኀይል ፡ አደረጀ

**military** (n.) ሰራዊት
The military took charge of the village. ሰራዊቱ ፡ መንደሪቱን ፡ በእጁ ፡ አደረገ

**military** (adj.)
1. የወታደር. He was wearing a military uniform. የወታደር ፡ የደንብ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ ነበር
2. የጦር ፡ ኀይል. The distribution of our troops is a military secret. የወታደሮቻችን ፡ ድልድል ፡ የ ጦር ፡ ኀይል ፡ ምስጢር ፡ ነው
3. የውትድርና. A soldier should have a military bearing. ወታደር ፡ የውትድርና ፡ አቋም ፡ እንዲኖ ረው ፡ ያሻል

**militate, ~ against** ጉዳት ፡ ላይ ፡ ጣለው
His rashness militated against him. ችኩልነቱ ፡ ጉዳት ፡ ላይ ፡ ጣለው

**militia** ብሔራዊ ፡ ጦር
The governor exercised his power to call out the militia. ገዢው ፡ በሥልጣኑ ፡ ተጠቅሞ ፡ ብሔራዊ ፡ ጦሩን ፡ አስከተተ

**milk** (v.)
1. አለበ. They milk their cows twice a day. ላሞቻቸውን ፡ በቀን ፡ ሁለቴ ፡ ያልቧታል
2. ገንዘብ ፡ ጠርጎ ፡ ወሰደ. He is milking his business as much as he can. ከንግዱ ፡ ያገኘውን ፡ ያ ህል ፡ ገንዘብ ፡ ጠርጎ ፡ ይወስዳል

**milk** (n.) ወተት
Don't drink unboiled milk! ያልፈላ ፡ ወተት ፡ አትጠጣ
[See also 'powdered milk']

**milk tooth** የወፍ ፡ ጥርስ
The baby's milk teeth fell out one by one. የሕፃኑ ፡ የወፍ ፡ ጥርሶች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ረገፉ

**lose (one's) milk teeth** ግግ ፡ ወጣ(ለት)
The baby has lost all his milk teeth. ሕፃኑ ፡ ግግ ፡ ወጥቶለታል

**milky** ወተት ፡ ያለበት
The milky sauce tastes good. ወተት ፡ ያለበት ፡ ወጥ ፡ ይጣፍጣል

**Milky Way** የወተት ፡ ጐዳና
The Milky Way forms a band of light across the night sky. በሌሊት ፡ ሰማይ ፡ ላይ ፡ የወተት ፡ ጐዳና ፡ ውጋጋን ፡ ይታያል

**mill** (v.) ፈጨ
The women mill a little grain for their household. ሴቶች ፡ ለቤት ፡ የሚሆን ፡ ጥቂት ፡ እ ህል ፡ ይፈጫሉ

**mill about** ተተረማመሰ
The frightened cattle began to mill about. የተደናገጡት ፡ የቀንድ ፡ ከብቶች ፡ መተረማመስ ፡ ጀመሩ

**mill flour** ፈጨ
The stones mill flour from the wheat. ወፍጮዎ ቹ ፡ ስንዴ ፡ ይፈጫሉ

**mill** (n.)
1. ወፍጮ ፡ ቤት. When are you going to take the grain down to the mill? እህሉን ፡ ወፍጮ ፡ ቤት ፡ የምትወስደው ፡ መቼ ፡ ነው ?
2. ወፍጮ. A pepper mill is used to grind pepper. የበርበሬ ፡ ወፍጮ ፡ በርበሬ ፡ ለመፍጨት ፡ ያገ ለግላል
3. ፋብሪካ. We ordered the paper straight from the mill. ወረቀቱን ፡ በቀጥታ ፡ ከፋብሪካው ፡ አ ዘዝን

**millenium** አንድ ፡ ሺ ፡ ዓመታት
The Axumite Empire came to an end a millenium ago. የአክሱም ፡ መንግሥት ፡ የወደቀው ፡ ከ አንድ ፡ ሺ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ነው

**millet** ማሽላ
Millet is widespread in Ethiopia. ማሽላ ፡ በኢት ዮጵያ ፡ በብዛት ፡ ይገኛል

**million** ሚሊዮን

**millionaire** ሀብታም
The charity was established in perpetuity by the millionaire. ሀብታሙ ፡ የበጎ ፡ አድራጎቱን ፡ ድርጅት ፡ ያቋቋመው ፡ ለምንጊዜም ፡ ነው

**millstone** የድንጋይ ፡ ወፍጮ
This millstone is too heavy to lift. ይህን ፡ የድን ጋይ ፡ ወፍጮ ፡ ለማንሣት ፡ ከባድ ፡ ነው

**nether millstone** ወፍጮ ፤ እናት ፡ ወፍጮ
The nether millstone is made of a hard kind of stone. ወፍጮው ፡ (እናት ፡ ወፍጮው) ፡ ከጠን ካራ ፡ ድንጋይ ፡ የተሠራ ፡ ነው

**upper millstone** መጅ
So that the grain can be ground thoroughly, the upper and nether millstones have to be carved. እህል ፡ በደንብ ፡ መፍጨት ፡ እንዲቻ ል ፡ መጁና ፡ ወፍጮው ፡ መወቀር ፡ አለበት

**milt** ጣፊያ
When a sheep is killed, milt is given to the cat. በግ ፡ ሲታረድ ፡ ጣፊያው ፡ ለድመት ፡ ይሰጣል

**mimic** (v.)
1. መስሎ ፡ ቀለደ. We will get him to mimic

our old music teacher. ሽማግሌውን ፡ የሙዚቃ ፡ አስተማሪያችንን ፡ መስሎ ፡ እንዲቀልድ ፡ እናደርገዋለን

2. ቀዳ. Parakeets mimic human voices. በቀበቃ ፡ የሰውን ፡ ድምፅ ፡ ይቀዳል

**mimic** (n.)

*Some comedians are skillful mimics. አንዳንድ ፡ የኮሜዲ ፡ ተጫዋቾች ፡ የመቅዳት ፡ ችሎታ ፡ አላቸው

**mimosa** የግራር ፡ ዓይነት ፡ ዛፍ

**minaret** የጸሎት ፡ መጥሪያ ፡ ግምብ

Each mosque has a minaret. እያንዳንዱ ፡ መስጊድ ፡ የጸሎት ፡ መጥሪያ ፡ ግምብ ፡ አለው

**mince** ከተፈ

The woman is mincing onions. ሴትዮዋ ፡ ሽንኩርት ፡ ትከትፋለች

Mince the meat finely and cook it! ሥጋውን ፡ አድቅቀሽ ፡ ክተፊና ፡ ሥሪው

**not mince words**

*I won't mince words with you. እቅጩን ፡ እነግርሃለሁ

**mind** (v.)

1. ጠበቀ. Who is going to mind the baby? ሕፃኑን ፡ ማን ፡ ይጠብቃል ?

2. ተቀበለ. If you don't mind my warning, you'll be hurt. ማስጠንቀቂያዬን ፡ ካልተቀበልክ ፡ ትጐዳለህ

3. ተጠነቀቀ. Mind your step! The stair is loose here. ተጠንቀቀህ ፡ ተራመድ ። እዚያ ፡ ጋ ፡ ደረጃው ፡ ላልቷል

4. ሰማ. My son doesn't mind me anymore. ልጄ ፡ እኔን ፡ መስማት ፡ ትቷል

5. ታዘዘ. You must mind the policeman. ለፖሊስ ፡ መታዘዝ ፡ አለብህ

6. ቅር ፡ አለ(ው). Do you mind if I smoke? ባጨስ ፡ ቅር ፡ ይልሃል ?

*If you don't mind, I would like to have another cup of coffee. ቡና ፡ ብትደግሙኝ ፡ ደስ ፡ ይለኛል

**mind now!** ልብ ፡ አድርግ

Mind now, this is not a definite promise. ልብ ፡ አድርግ ። ይህ ፡ የተቈረጠ ፡ ቃል ፡ አይደለም

**mind you** ልብ ፡ በል

I have no objection, mind you, but I think it's unwise. ልብ ፡ በል ። የምቃወመው ፡ ነገር ፡ የለኝም ። ግን ፡ ተገቢ ፡ አይመስለኝም

**never mind!** ግድ ፡ የለም

Never mind! I am not hungry. ግድ ፡ የለም ። አልራበኝም

**not mind**

1. ችላ ፡ አለ. Don't mind what he says! እሱ ፡ የሚለውን ፡ ችላ ፡ በለው

2. ግድ ፡ የለውም. He doesn't mind the cold weather at all. ለብርዱ ፡ ፍጹም ፡ ግድ ፡ የለውም

**mind** (n.)

1. ሐሳብ. I have changed my mind. ሐሳቤን ፡ ለውጫለሁ

Is he still of the same mind? አሁንም ፡ ሐሳቡ ፡ ያው ፡ ነው ?

On my way home, the thought flashed through my mind. ወደ ፡ ቤቴ ፡ ስሄድ ፡ ሐሳብ ፡ ብልጭ ፡ አለልኝ

2. አንጐል. He has a very keen mind. በጣም ፡ ንቁ ፡ አንጐል ፡ አለው

3. አእምሮ. You need an agile mind to solve the problem. ለችግሩ ፡ መፍትሔ ፡ ለማስገኘት ፡ ንቁ ፡ አእምሮ ፡ ያስፈልግሃል

4. ጠቢብ. Who are the great minds of our day? የዘመናችን ፡ ታላላቅ ፡ ጠቢባን ፡ እነማን ፡ ናቸው ?

**bear in mind** አስታወሰ

You must bear in mind that he is a foreign student. እሱ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ተማሪ ፡ መሆኑን ፡ ማስታወስ ፡ አለብህ

**bring to mind** አስታወሰ

That brings to mind a funny story. አሥቂኝ ፡ ታሪክ ፡ ያስታውሰናል

**call to mind** አስታወሰ

That calls to mind a story I know. ያ ፡ አንድ ፡ የማውቀውን ፡ ታሪክ ፡ ያስታውሰኛል

**cross one's mind** በሐሳቡ ፡ መጣ

It never crossed my mind that he would object. ይቃወማል ፡ ብዬ ፡ በሐሳቤም ፡ አልመጣም

**give someone a piece of one's mind** ቅር ፡ እንደተሰኘ ፡ ገለጸለት

I will give him a piece of my mind for telling such a lie. ይህን ፡ መሳይ ፡ ውሸት ፡ ስለነገረኝ ፡ ቅር ፡ እንደተሰኘሁ ፡ እገልጽለታለሁ

**have a mind** አሰበ

I have a mind to punish him. እሱን ፡ ለመቅጣት ፡ አስባለሁ

**have (one's) mind set on** ቈርጦ ፡ ተነሣ

She has her mind set on going shopping today. ዛሬ ፡ ገበያ ፡ ለመውጣት ፡ ቈርጣ ፡ ተነሥታለች

**have in mind** አሰበ

Have you anyone definite in mind for the job? ለሥራው ፡ በተለይ ፡ ያሰብከው ፡ ሰው ፡ አለ ?

**keep in mind** አስታወሰ

We must keep in mind that foreign students

have different training. የውጭ ፡ አገር ፡ ተማሪዎች ፡ የተለያየ ፡ ትምህርት ፡ እንዳላቸው ፡ ማስታወስ ፡ አለብን

**keep one in mind** አስታወሰ
I expect that there will be a job open soon, so I will keep you in mind. በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ሥራ ፡ ይገኛል ፡ ብዬ ፡ ስለምገምት ፡ አስታውስሃለሁ

**keep one's mind on** ሐሳቡን - - - ላይ ፡ አሳረፈ
I can't keep my mind on my studies when the radio is playing. ራዲዮ ፡ ሲጫወት ፡ ሐሳቤን ፡ ጥናቴ ፡ ላይ ፡ ለማሳረፍ ፡ አልችልም

**know (one's) own mind**
*He's too young to know his own mind. የሚጠቅመውንና ፡ የሚጐዳውን ፡ ለመለየት ፡ ገና ፡ ልጅ ፡ ነው

**make up one's mind** ቈረጠ ፤ ሐሳቡን ፡ ቈረጠ ፤ ወጠነ
I cannot make up my mind which girl I like better. የትኛዋን ፡ ልጃገረድ ፡ የበለጠ ፡ እንደምወድ ፡ ልቈርጥ ፡ አልቻልኩም
Sooner or later, we will have to make up our minds. ግራም ፡ ነፈሰ ፡ ቀኝ ፡ ሐሳባችንን ፡ መቊረጥ ፡ አለብን
A man of decision makes up his mind what to do and then does it. ቈርጠኛ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ እንደሚያደርግ ፡ ወጥኖ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ያውለዋል

**(be) of one mind** ተስማማ
We are all of one mind on this matter. በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ሁላችንም ፡ ተስማምተናል

**(be) of two minds** አወላወለ
I am of two minds regarding the proposal. ስለቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ አወላውላለሁ

**(be) on (one's) mind** አሰበ
What's on your mind? ምን ፡ ታስባለህ ?

**(be) out of (one's) mind** አበደ
Are you out of your mind to go out in this heavy rain? በዚህ ፡ ከባድ ፡ ዝናብ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ የምትሄደው ፡ አብደሃል ?

**presence of mind** የአእምሮ ፡ እርጋታ
She had enough presence of mind to remember the license plate of the speeding car. በፍጥነት ፡ የሚበረውን ፡ የመኪና ፡ ሰሌዳ ፡ ለማስታወስ ፡ የሚያስችል ፡ የአእምሮ ፡ እርጋታ ፡ ነበራት

**(have) presence of mind** አእምሮው ፡ ንቁ ፡ ነው
He has presence of mind and is never at a loss for an answer. አእምሮው ፡ ንቁ ፡ ስለሆነ ፡ መልስ ፡ አይቸግረውም

**(show) presence of mind** ሳይደነግጥ ፡ ረጋ ፡ አለ
When his clothes caught fire, he showed great presence of mind by extinguishing the fire. ልብሱ ፡ በእሳት ፡ ሲያያዝ ፡ ሳይደነግጥ ፡ ረጋ ፡ ብሎ ፡ አጠፋው

**set one's mind on** ቈረጠ
He has set his mind on learning English. እንግሊዝኛ ፡ ለመማር ፡ ቈርጧል

**(have a) small mind** ሐሳቡ ፡ ጠባብ ፡ ነው
He has a small mind and cannot be persuaded to accept new things. ሐሳቡ ፡ ጠባብ ፡ ስለሆነ ፡ አዲስ ፡ ሐሳብ ፡ እንዲቀበል ፡ ልታግባባው ፡ አትችልም

**take one's mind off**
*Try to take his mind off his troubles! ስለ ፡ ችግሮቹ ፡ እንዳያሰላስል ፡ አድርገው

**to my mind** እንደኔ
To my mind, she is the right person for the job. እንደኔ ፡ ለሥራው ፡ ተገቢ ፡ ሰው ፡ እሷ ፡ ናት

**would you mind**
*Would you mind opening the window? መስኮቱን ፡ ብትከፍተው ?
[See also 'flash, frame, keen, load, open, peace, piece, put, read, reel, rest, right, sink, speak, turn over, weigh']

## minded, be so ~ ፈለገ
He could do it if he were so-minded. ቢፈልግ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል

**be --- minded** ለ - - - ዝንባሌ ፡ አለው
He is mathematically minded and grasps every problem. ለሒሳብ ፡ ዝንባሌ ፡ ስላለው ፡ ማንኛቸውም ፡ ዓይነት ፡ ፕሮብሌም ፡ ይገባዋል

## mindful, ~ of በመስማት
Mindful of your advice, I went slowly. ምክርህን ፡ በመስማት ፡ ዝግ ፡ ብዬ ፡ ሄድኩ

**be mindful**
1. ዐወቀ. Father was always mindful of the needs of the family. አባቴ ፡ የቤተ ፡ ሰቡን ፡ ፍላጎት ፡ ሁልጊዜ ፡ ያውቅ ፡ ነበር
2. ልብ ፡ አለ. Be mindful of the many dangers you face! ስለሚገጥሙህ ፡ ብዙ ፡ ችግሮች ፡ ልብ ፡ በል

## mindless ግዴለሽ
He is mindless of all dangers. ለማንኛውም ፡ አደጋ ፡ ግዴለሽ ፡ ነው

**in a mindless sort of way** ሳያስብ
He does things in a mindless sort of way. አንድ ፡ ነገር ፡ ሲያደርግ ፡ ሳያስብ ፡ ነው

## mine (v.)
1. አወጣ. Do they mine gold in this region? እዚህ ፡ አካባቢ ፡ ወርቅ ፡ ያወጣሉ ?

2. ፈንጂ ፡ ቀበረ. The enemy mined the road to the harbor. ጠላት ፡ ወደ ፡ ወደቡ ፡ በሚያመራው ፡ መንገድ ፡ ፈንጂ ፡ ቀበረ

**mine** (n.)
1. ማዕድን. Are there coal mines in Ethiopia? በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የድንጋይ ፡ ከሰል ፡ ማዕድኖች ፡ አሉ ?
2. ፈንጂ. The rebels planted mines in the road. ዐመፀኞቹ ፡ መንገዱ ፡ ላይ ፡ ፈንጂ ፡ ቀበሩ
3. ምንጭ. A good dictionary is a mine of information. ጥሩ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ የዕውቀት ፡ ምንጭ ፡ ነው
*He is a mine of information about ships. ስለ ፡ መርከቦች ፡ ብዙ ፡ ያውቃል

**mine** (pron.) የኔ
It's not your hat, it's mine. ያንተ ፡ ባርኔጣ ፡ አይደለም ፤ የኔ ፡ ነው
**of mine** (suffix pronoun)
A friend of mine gave me this. አንድ ፡ ወዳጄ ፡ ይህንን ፡ ሰጠኝ

**miner** ማዕድን ፡ ቈፋሪ
Miners often endanger their lives. ማዕድን ፡ ቈፋሪዎች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሕይወታቸው ፡ በሚያሰጋ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ነው

**mineral** ማዕድን
Coal and salt are minerals. የድንጋይ ፡ ከሰልና ፡ ጨው ፡ ማዕድኖች ፡ ናቸው

**mineral oil** የነዳጅ ፡ ዘይት
Mineral oil is used in cars. የነዳጅ ፡ ዘይት ፡ ለመኪና ፡ ያገለግላል

**mineral water** ጠበል
This mineral water is effervescent. ይህ ፡ ጠበል ፡ ይፈላል

**mingle** (vt.)
1. አጻበለ. One should not mingle sheep with tigers. በጎችን ፡ ከነብሮች ፡ ጋር ፡ ማጻበል ፡ አይገባም
2. (= vi.) ተቀላቀለ. The two rivers mingle their waters. የሁለቱ ፡ ወንዞች ፡ ውኃ ፡ ይቀላቀላል
**mingle** (vi.)
1. ተደባለቀ. The detectives mingled with the crowd. ጆሮ ፡ ጠቢዎቹ ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋር ፡ ተደባለቁ
2. ገጠመ. He is very shy and does not mingle much with the children at school. በጣም ፡ ዓይን ፡ አፋር ፡ ስለሆነ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ከልጆች ፡ ጋር ፡ እምብዛም ፡ አይገጥምም
3. ተቀላቀለ. The waters of the Missouri and the Mississippi rivers mingle near St. Louis. የሚዙሪና ፡ የሚሲሲፒ ፡ ወንዞች ፡ ሴይንት ፡ ሉዊስ ፡ አጠገብ ፡ ይቀላቀላሉ

**miniature** (n.)
1. ሞዴል. In the museum, there is a miniature of the ship 'America'. ቤተ ፡ መዘክሩ ፡ ውስጥ ፡ «አሜሪካ» ፡ የተሰኘችው ፡ መርከብ ፡ ሞዴል ፡ አለ
2. በጣም ፡ ትንሽ ፡ ሥዕል. There is only one miniature in this manuscript. በዚህ ፡ የብራና ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ሥዕል ፡ ብቻ ፡ ነው
**miniatures** ጥቃቅን ፡ ሥዕሎች
There are many miniatures in this manuscript. በዚህ ፡ የብራና ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ጥቃቅን ፡ ሥዕሎች ፡ አሉ
**miniature** (adj.)
1. ጥቃቅን. There are miniature paintings in the old Geez manuscript. በጥንቱ ፡ የግዕዝ ፡ የብራና ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ጥቃቅን ፡ ሥዕሎች ፡ ይገኛሉ
2. አነስተኛ. There is a miniature train in the park. መናፈሻው ፡ ውስጥ ፡ አነስተኛ ፡ ባቡር ፡ አለ

**minimize**
1. ቀነሰ. Proper care will minimize the danger of fire. ተገቢ ፡ ጥንቃቄ ፡ የእሳትን ፡ አደጋ ፡ ሊቀንሰው ፡ ይችላል
2. አቃለለ. He minimized his act of bravery. የጀግንነት ፡ ሙያውን ፡ አቃለለው
An ungrateful person minimizes the help others have given him. ውለታ ፡ ቢስ ፡ ሰው ፡ ሌሎች ፡ ያደረጉለትን ፡ እርዳታ ፡ ያቃልላል

**minimum,** n. (= adv.) እጅግ ፡ ቢያንስ
Eight hours of sleep is the minimum that children should have. ሕፃናት ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ መተኛት ፡ አለባቸው
**a minimum of** ቢያንስ ፡ ቢያንስ
Study a minimum of three hours a day! ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ በቀን ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ አጥና
**minimum** (adj.) አነስተኛ
The minimum salary is a hundred dollars a month. አነስተኛው ፡ ደሞዝ ፡ በወር ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ነው

**mining** (n.) ማውጣት
Coal mining is the chief industry of several states. የድንጋይ ፡ ከሰል ፡ ማውጣት ፡ የብዙ ፡ ግዛቶች ፡ ዋና ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ነው

**mining** (adj.) የማዕድን
A mining region produces gold and silver. የማዕድን ፡ ቀበሌ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ይወጣታል

**minister, ~ to**
1. አከመ. I need someone to minister to my wounds. ቁስሌን ፡ የሚያክምልኝ ፡ ሰው ፡ እፈልጋለሁ
2. አከናወነ. After his wife's death, his sister ministered to his needs. ሚስቱ ፡ ከሞተች ፡ በኋላ ፡ እኅቱ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሁሉ ፡ ታከናውንለት ፡ ነበር

**minister** (n.)
1. አለቃ. Our church has a new minister. ቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ አዲስ ፡ አለቃ ፡ አለው
2. ሚኒስትር. The Minister of Education visited our school today. የትምህርት ፡ ሚኒስትሩ ፡ ዛሬ ፡ ትምህርት ፡ ቤታችንን ፡ ጐበኙ
[See also 'deputy']

**ministry** (ministries)
1. ሚኒስቴር. He works at the Ministry of Education. ትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ይሠራል
2. ቅስና. His son is intended for the ministry. ልጁ ፡ ለቅስና ፡ ታጭቷል
*The ministry is sometimes chosen by parents for their children. ልጆች ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልጋዮች ፡ እንዲሆኑ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ሰቦቻቸው ፡ ያሳስቧቸዋል

**minor** (n.)
1. ለአካለ ፡ መጠን ፡ ያልደረሰ ፡ ሰው. No liquor will be served to minors. ለአካለ ፡ መጠን ፡ ላልደረሱ ፡ ሰዎች ፡ መጠጥ ፡ አይሸጥም
2. ለዐቅመ ፡ ሔዋን ፡ ያልደረሰች ፡ ሴት. Sexual relations with a minor is a criminal offense. ለዐቅመ ፡ ሔዋን ፡ ካልደረሰች ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ ፍትወተ ፡ ሥጋ ፡ መፈጸም ፡ በሕግ ፡ ያስቀጣል
3. (በትምህርት) ፡ ተጨማሪ ፡ ምርጫ. He has a major in history with a minor in sociology. ዋናው ፡ ትምህርቱ ፡ ታሪክ ፡ ሲሆን ፡ ተጨማሪ ፡ ምርጫው ፡ ደግሞ ፡ የኅብረ ፡ ሰብ ፡ ትምህርት ፡ ነው

**minor** (adj.)
1. ቀላል. He suffered minor injuries in his fall. በመውደቁ ፡ የደረሰበት ፡ ቁስል ፡ ቀላል ፡ ነው
2. አነስተኛ. I made only minor changes. ያደረግሁት ፡ ለውጥ ፡ አነስተኛ ፡ ነበር
3. ዝቅተኛ. He plays a minor part in the government. በመንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ኀላፊነት ፡ ዝቅተኛ ፡ ነው
His brother is a minor official. ወንድሙ ፡ ዝቅተኛ ፡ ባለሥልጣን ፡ ነው
4. ጥቃቅን. The office boy takes care of minor things. ተላላኪው ፡ ጥቃቅን ፡ ሥራዎችን ፡ ያከናውናል
5. ዝርዝር. Minor details are circumstantial compared with the main facts. ከዋናው ፡ ጉዳይ ፡ ጋር ፡ ሲመዛዘኑ ፡ ዝርዝሮቹ ፡ ነገሮች ፡ አጋጣሚዎች ፡ ናቸው

**minority** (minorities) .
1. በቁጥር ፡ አነስተኛ ፡ የሆነ ፡ ሕዝብ. The minority must often do what the majority decides to do. በቁጥር ፡ አነስተኛ ፡ የሆነው ፡ ሕዝብ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አብዛኛው ፡ ሕዝብ ፡ ለማድረግ ፡ የሚወስነውን ፡ ማድረግ ፡ አለበት
2. በቁጥር ፡ አነስተኛ ፡ ወገን. We were in the minority. በቁጥር ፡ አነስተኛ ፡ የሆነው ፡ ወገን ፡ ነበርን

**minstrel** አዝማሪ
A minstrel will play songs at our wedding feast. ሰርጋችን ፡ ላይ ፡ አዝማሪ ፡ ይዘፍንልናል

**mint** ገንዘብ ፡ መሥሪያ
The mint is coining pennies. ገንዘብ ፡ መሥሪያው ፡ ሳንቲሞች ፡ በማተም ፡ ላይ ፡ ነው

**a mint of** እጅግ ፡ ብዙ
He made a mint of money. እጅግ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አተረፈ

**minus** (adj.)
1. የመቀነስ. The minus sign is — . የመቀነስ ፡ ምልክት ፡ — ነው
2. (= adv.) ከዜሮ ፡ በታች. Minus three is a negative quantity. ከዜሮ ፡ በታች ፡ ሦስት ፡ የአሉታ ፡ ጠባይ ፡ ነው

**minus** (prep.)
1. ሲቀነስ ፤ ሲነሣ. Three minus two equals one. ከሦስት ፡ ሁለት ፡ ሲቀነስ ፡ (ሲነሣ) ፡ አንድ ፡ ይቀራል
2. ያለ. I found the book minus its cover. መጽሐፉን ፡ ያለ ፡ ሽፋኑ ፡ አገኘሁት

**minus** (adv.) ከዜሮ ፡ በታች
The temperature is minus five degrees. ያየሩ ፡ ቅዝቃዜ ፡ ከዜሮ ፡ በታች ፡ አምስት ፡ ዲግሪ ፡ ወርዷል

**minute** (n.) ደቂቃ
I'll be back in five minutes. ባምስት ፡ ደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ እመለሳለሁ

**minutes** ቃለ ፡ ጉባኤ
The secretary will read the minutes of the last meeting. ጸሓፊው ፡ ያለፈውን ፡ ስብሰባ ፡ ቃለ ፡ ጉባኤ ፡ ያነባል

**any minute** አሁን
The train will pull out any minute. ባቡሩ ፡ አሁን ፡ ይነሣል

**in a minute** በቶሎ ፤ በደቂቃ ፡ ውስጥ
He'll be done in a minute. በቶሎ ፡ ይጨርሳል ፡ (በደቂቃ ፡ ውስጥ ፡ ይጨርሳል)

**just a minute** እስቲ ፡ ቆይ
Just a minute, please; I have to answer the door. እስቲ ፡ ቆይ ፤ በሩን ፡ የሚያንኳኳው ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ልይ

**the minute** እንደ + perfect + ወዲያው
I'll call you the minute I know. እንደሰማሁ ፡ ወዲያው ፡ እደውልልሃለሁ

**this minute!** አሁኑኑ
Come here this minute! አሁኑኑ ፡ ና

**up to the minute** እጅግ ፡ ዘመናዊ
As far as fashion is concerned, she is up to the minute. በፋሽን ፡ ረገድ ፡ እጅግ ፡ ዘመናዊ ፡ ናት

**minute** (adj.)
1. ረቂቅ. It was so minute, you could hardly see it. ረቂቅ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ለማየት ፡ ያስቸግራል
2. ዝርዝር. He gave me minute instructions about how to do my work. ሥራዬን ፡ እንዴት ፡ እንደምሠራ ፡ ዝርዝር ፡ የሆነ ፡ መምሪያ ፡ ሰጠኝ
3. (= adv.) አንድ ፡ ባንድ. I have checked every minute detail. ጉዳዩን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ተመልክቼዋለሁ
*His story is of minute importance. የሱ ፡ ታሪክ ፡ ብዙም ፡ ጠቃሚነት ፡ የለው

**minutely** በዝርዝር
The plan of attack was minutely prepared. አደጋ ፡ የመጣሉ ፡ እቅድ ፡ በዝርዝር ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ነበር

**miracle** ተአምር (pl. ተአምራት)
It was a miracle that he escaped unharmed from the crash. በግጭቱ ፡ ሳይጐዳ ፡ መቅረቱ ፡ ተአምር ፡ ነው
Christ performed many miracles. ክርስቶስ ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ ሠርቷል

**miraculous**
1. ተአምር. Her recovery is miraculous. መዳኗ ፡ ተአምር ፡ ነው
2. ለተአምር ፡ የሚነገር. He had miraculous success in his business. በንግድ ፡ ሥራው ፡ ለተአምር ፡ የሚነገር ፡ ውጤት ፡ አገኘ
3. ተአምራዊ. Penicillin is a miraculous drug. ፔኒሲሊን ፡ ተአምራዊ ፡ መድኃኒት ፡ ነው

**mire,** vt. (= intr.) ማጥ ፡ ውስጥ ፡ ገባ
He mired his car and had to go for help. መኪናው ፡ ማጥ ፡ ውስጥ ፡ ስለገባ ፡ ሄዶ ፡ እርዳታ ፡ መፈለግ ፡ ግድ ፡ ሆነበት

**mire** (n.)
1. ማጥ. We waded through the mire to reach the road. ከመንገድ ፡ ለመድረስ ፡ በማጡ ፡ ውስጥ ፡ ተጓዝን
2. መጨቅየት. The mire of the road delayed the travelers. የመንገዱ ፡ መጨቅየት ፡ መንገደኞቹን ፡ አዘገያቸው

**turn into mire** አጨቀየ
The rain turned the dust of the road into mire. ዝናቡ ፡ መንገዱን ፡ አጨቀየው

**mirror** (v.)
1. ገለጸ. His face mirrored his feelings. ፊቱ ፡ ስሜቱን ፡ ገለጸ
2. ቁልጭ ፡ አድርጎ ፡ አሳየ. The book mirrors life in the countryside. መጽሐፉ ፡ የገጠርን ፡ ኑሮ ፡ ቁልጭ ፡ አድርጎ ፡ ያሳያል
3. ጥላ ፡ አሳየ. The water was so still that it mirrored the trees along the bank. ውኃው ፡ በጣም ፡ የረጋ ፡ ስለነበረ ፡ በዳርቻው ፡ ያሉትን ፡ የዛፎች ፡ ጥላ ፡ አሳየ

**mirror** (n.)
1. መስታወት. Her mirror is old. መስታወቷ ፡ አሮጌ ፡ ነው
This book is a mirror of life in Ethiopia. ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የኑሮ ፡ ሁኔታ ፡ የሚያሳይ ፡ መስታወት ፡ ነው
2. ምሳሌ. That soldier was a mirror of bravery. ያ ፡ ወታደር ፡ የጀግንነት ፡ ምሳሌ ፡ ነበር

**mirth** ሣቅ
His sides shook with mirth. ልቡ ፡ በሣቅ ፡ ፈረሰ

**miry** ማጥ ፡ የበዛበት
He couldn't press forward because of the miry road. መንገዱ ፡ ማጥ ፡ የበዛበት ፡ ስለሆነ ፡ ሊገሰግስ ፡ አልቻለም

**misadventure** መጥፎ ፡ዕድል ፤ መጥፎ ፡ ነገር ፤ የደረሰበት ፡ ችግር
They failed through misadventures, not from lack of skill. ችሎታ ፡ አጥተው ፡ ሳይሆን ፡ በመጥፎ ፡ ዕድል ፡ ምክንያት ፡ ወደቁ
We had several misadventures on the trip. በጉዞው ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ መጥፎ ፡ ነገሮች ፡ አጋጥመውን ፡ ነበር
She spoke in a merry vein of her misadventure. ስለደረሰባት ፡ ችግር ፡ ሁሉ ፡ እየቀለደች ፡ ተናገረች

**misalliance** ያላቻ ፡ ጋብቻ
A misalliance should not become a marriage. ያላቻ ፡ ጋብቻ ፡ ትዳር ፡ አይሆንም

**misapprehend** በደንብ ፡ አልገባ(ውም)
+The workers misapprehended the orders given by the boss. ሠራተኞቹ ፡ አለቅዬው ፡ የሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ በደንብ ፡ አልገባቸውም

**misapprehension** ሳይገባው ፡ መቅረት
Their misapprehension of the orders caused a delay in the work. ትእዛዙ ፡ ሳይገባቸው ፡ መቅረቱ ፡ ሥራው ፡ እንዲዘገይ ፡ አደረገ

**misappropriate** አጐደለ
The treasurer has misappropriated the club funds. ገንዘብ ፡ ያዢው ፡ የክበቡን ፡ ገንዘብ ፡ አጐደለ

**misbehave** ባለገ
The children misbehave when their father is away. ልጆቹ ፡ አባታቸው ፡ ሳይኖር ፡ ይባልጋሉ

**miscalculate** አጉል ፡ ገመተ
He miscalculated the distance he had to jump. መዝለል ፡ የነበረበትን ፡ ርቀት ፡ አጉል ፡ ገመተ

**miscarriage**
*She is in the hospital as a result of a miscarriage. ስላስወረዳት ፡ ሆስፒታል ፡ ገብታለች

**have a miscarriage** አስወረዳት
She had a miscarriage and had to go to the hospital. ስላስወረዳት ፡ ሆስፒታል ፡ መሄድ ፡ ነበረባት

**miscarry** (miscarried)
1. አስወረዳት. Our neighbor's wife miscarried, and had to go to the hospital. የጐረቤታችን ፡ ባለቤት ፡ ስላስወረዳት ፡ ሆስፒታል ፡ መሄድ ፡ ነበረባት
2. ተጨናገፈ. I am prepared to admit that my plan has miscarried. የሐሳቤን ፡ መጨናገፍ ፡ ለማመን ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ

**miscellaneous** (= adv.) በየዓይነቱ
He owns a miscellaneous collection of Ethiopian-made things. ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የተሠሩ ፡ ነገሮች ፡ በየዓይነቱ ፡ ሰብስቧል

**mischief**
1. ተንኰል. A child's mischief may cause a serious fire. የልጅ ፡ ተንኰል ፡ ከባድ ፡ ቃጠሎ ፡ ሊያስነሣ ፡ ይችላል
2. ጉዳት. People who tell tales about others can do great mischief. አሳባቂዎች ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ ሊያደርሱ ፡ ይችላሉ

**you little mischief!** አንተ ፡ ከይሲ
You little mischief! You tore my book. አንተ ፡ ከይሲ ! መጽሐፌን ፡ ቀደድክ

**mischievous**
1. ተጫዋች. The mischievous puppy amused us greatly. ተጫዋቿ ፡ ቡችላ ፡ በጣም ፡ አሣቀችን
2. የተንኰለኞች. Mischievous slander cost him his job. የተንኰለኞች ፡ አሉባልታ ፡ ሥራውን ፡ አሳጣው

**misconceive** በትክክል ፡ አልተረዳ(ውም)
He misconceived the problem. ችግሩን ፡ በትክክል ፡ አልተረዳውም

**misconception** አለማወቅ
Many mistakes result from misconceptions. ካለማወቅ ፡ የተነሣ ፡ ብዙ ፡ ስሕተት ፡ ይደርሳል

**misconduct**
1. መጥፎ ፡ አመል. He was punished for his misconduct. በመጥፎ ፡ አመሉ ፡ ተቀጣ
2. ጥፋት. I'm honor bound to report your misconduct to the police. ጥፋትህን ፡ ለፖሊስ ፡ እንድገልጽ ፡ ኅሊናዬ ፡ ያስገድደኛል
[See also 'flagrant']

**misconstrue** በስሕተት ፡ ተረዳ(ው)
He misconstrued her silence as approval. ዝምታዋን ፡ እንደ ፡ መስማማት ፡ አድርጎ ፡ በስሕተት ፡ ተረዳው

**misdemeanor** አነስተኛ ፡ ወንጀል
It is a misdemeanor to throw litter in the streets. ቆሻሻ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ መጣል ፡ አነስተኛ ፡ ወንጀል ፡ ነው

**miser** ንፉግ
A miser does not spend money on his children. ንፉግ ፡ ለልጆቹ ፡ ገንዘብ ፡ አያወጣም

**miserable**
1. አሰቃቂ. He talked about the miserable life of the refugees after the war. ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ ስደተኞቹ ፡ ስለነበሩበት ፡ አሰቃቂ ፡ ኑሮ ፡ አወራ
2. መጥፎ. What a miserable meal that was! ምን ፡ ዓይነት ፡ መጥፎ ፡ ምግብ ፡ ነበር
3. ደሳሳ. They live in a miserable shack. ደሳሳ ፡ ጎጆ ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ
4. ብስጩ. A sick child is often miserable. የታመመ ፡ ልጅ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ብስጩ ፡ ነው

**feel miserable** ቀፈፈ(ው)
I feel miserable today; my stomach is upset. ዛሬ ፡ ሆዴን ፡ ስላመመኝ ፡ ቀፎኛል

**make miserable**
She makes life miserable for him. ኑሮውን ፡ መራራ ፡ ታደርግበታለች

## miserly ጩቅ

This is a novel about a miserly man. ይህ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ጩቅ ፡ የሚናገር ፡ ነው

**miserly habits** ንፉግነት
His miserly habits are noticed by everybody. የሱ ፡ ንፉግነት ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ታውቋል

**in a miserly fashion** በሥሥት
He lives in a miserly fashion. በሥሥት ፡ ይኖራል

## misery (miseries)

1. ችግር. The poor live in misery; they lack everything. ምንም ፡ ነገር ፡ ስለሌላቸው ፡ ድሆች ፡ በችግር ፡ ይኖራሉ
2. ችግረኛነት. Some people rose from misery to fortune. አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ከችግረኛነት ፡ ተነሥተው ፡ ሀብታሞች ፡ ሆኑ
3. መከራ. Misery follows war. መከራ ፡ ጦርነትን ፡ ይከተላል
4. ሥቃይ. The misery of loneliness was now compounded by his poverty. ድኽነት ፡ የብቸኝነት ፡ ሥቃይን ፡ አባሰበት

**be in misery** በጣም ፡ ተሠቃየ
He was in misery from a toothache. በጥርስ ፡ ሕመም ፡ በጣም ፡ ይሠቃይ ፡ ነበር

## misfire ከሸፈ

The gun misfired, and the deer ran away. ጥይቱ ፡ በመክሸፉ ፡ አጋዘኑ ፡ አመለጠ
Our plans misfired, and the criminal got away. እቅዶቻችን ፡ ስለከሸፉ ፡ ወንጀለኛው ፡ አመለጠ

## misfit ከሰው ፡ ጋር ፡ የማይግባባ ፡ ሰው

A misfit never finds friends. ከሰው ፡ ጋር ፡ ለማይግባባ ፡ ሰው ፡ ጓደኛ ፡ የለውም

**be a misfit** ልክ ፡ አልሆነውም
His coat was a misfit and his trousers baggy. ኮቱ ፡ ልክ ፡ አልሆነውም ፤ ሱሪውም ፡ ሰፍቶበታል

## misfortune

1. መከራ. He commiserated with his friend on his misfortunes. ወዳጁ ፡ ለደረሰበት ፡ መከራ ፡ ሐዘኑን ፡ ገለጸ
2. መጥፎ ፡ ዕድል. He is brooding all day long over his misfortunes. በመጥፎ ፡ ዕድሉ ፡ ሙሉ ፡ ቀን ፡ በሐዘን ፡ ሲተክዝ ፡ ይውላል
3. ክፉ ፡ ቀን. Misfortune tests a person's character. ክፉ ፡ ቀን ፡ የሰውን ፡ ጠባይ ፡ ይፈትናል

**be a misfortune**
1. ጎዳ. It won't be a great misfortune if you don't get it. ባታገኘውም ፡ ብዙ ፡ አይጎዳህም
2. ዕጣ ፡ ከዳ(ው). It was his misfortune to be killed in the war. በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ የሞተው ፡ ዕጣ ፡ ከድቶት ፡ ነው

**suffer misfortune** መከራ ፡ ደረሰ(በት)
He suffered great misfortune when his wife died. ሚስቱ ፡ በሞተች ፡ ጊዜ ፡ ትልቅ ፡ መከራ ፡ ደረሰበት

## misgivings ጥርጣሬ

He had no misgivings about his ability. ስለ ፡ ችሎታው ፡ ጥርጣሬ ፡ አልነበረውም

**have misgivings** ቅር ፡ አለ(ው)
We had some misgivings about hiring a servant who was suspected of theft. በሌብነት ፡ የተጠረጠረ ፡ አሽከር ፡ ለመቅጠር ፡ ጥቂት ፡ ቅር ፡ ብሎን ፡ ነበር

## misguide አሳሳተ

The lawyer misguided his clients about the inheritance. ስለ ፡ ውርሱ ፡ ጉዳይ ፡ ጠበቃው ፡ ደንበኞቹን ፡ አሳሳታቸው

## mishandle

1. አጒላላ. The night watchman mishandled the dog. ዘበኛው ፡ ውሻውን ፡ አጒላላው
2. በሚገባ ፡ አልጠበቀም. The heirs mishandled the estate. ወራሾቹ ፡ ርስቱን ፡ በሚገባ ፡ ሳይጠብቁት ፡ ቀሩ

## mishap

1. አደጋ. The mishap was reported in the papers. አደጋው ፡ በጋዜጦች ፡ ተገልጾ ፡ ነበር
2. ጥፋት. The spilling of the sauce was his only mishap. ያደረሰው ፡ ጥፋት ፡ ወጥ ፡ መድፋት ፡ ብቻ ፡ ነው

## misinform ውሸት ፡ ነገረ

He deliberately misinformed his employer about the situation. ለቀጣሪው ፡ ስለ ፡ ሁኔታው ፡ ሆን ፡ ብሎ ፡ ውሸት ፡ ነገረው

## misinformation የተሳሳተ ፡ መረጃ

His report is a hodgepodge of lies and misinformation. ሪፖርቱ ፡ ውሸትና ፡ የተሳሳተ ፡ መረጃ ፡ የተቀላቀለበት ፡ ነው

## misinterpret

1. በስሕተት ፡ ተረጎመ. He misinterpreted his silence as giving consent. ዝምታውን ፡ ተስማምቷል ፡ በማለት ፡ በስሕተት ፡ ተረጎመው

2. በመጥፎ ፡ አየ. He misinterpreted my intentions and was offended. ሐሳቤን ፡ በመጥፎ ፡ ስላየው ፡ ቅር ፡ ተሰኘ

**misjudge**
1. በስሕተት ፡ ገመተ. He misjudged the distance and fell into the water. ርቀቱን ፡ በስሕተት ፡ በመገመቱ ፡ ውኃው ፡ ውስጥ ፡ ወደቀ
2. በተሳሳተ ፡ አስተያየት ፡ ገመተ. I have misjudged his character. ጠባዩን ፡ በተሳሳተ ፡ አስተያየት ፡ ገመትኩ
3. ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ ገመተ. We mustn't misjudge the seriousness of the situation. የሁኔታውን ፡ አሳሳቢነት ፡ ዝቅ ፡ አድርገን ፡ መገመት ፡ የለብንም
4. (= intr.) ተሳሳተ. You misjudge him if you think he is trying to hurt you. ሊጎዳኝ ፡ ያስባል ፡ ብለህ ፡ እንደሆነ ፡ ተሳስተሃል

**mislaid**, see **mislay**

**mislay** (mislaid) የት ፡ እንዳስቀመጠው ፡ አላወቀም
I've mislaid my glasses. መነጽሬን ፡ የት ፡ እንዳስቀመጥኩ ፡ አላውቅም

**mislead** (misled)
1. በስሕተት ፡ መራ. Our guide misled us in the woods, and we got lost. መንገድ ፡ መሪያችን ፡ በስሕተት ፡ ስለመራን ፡ ጫካ ፡ ውስጥ ፡ ገብተን ፡ ጠፋን
2. አሳሳተ. He misled me into thinking that I could buy the house cheaply. ቤቱን ፡ በርካሽ ፡ ለመግዛት ፡ የምችል ፡ በማስመሰል ፡ አሳሳተኝ
3. አበላሸ. Bad companions often mislead young people. አጉል ፡ ጓደኞች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ወጣቶችን ፡ ያበላሻሉ

**misleading** አሳሳች
The description is misleading. መግለጫው ፡ አሳሳች ፡ ነው

**mismanage** በመጥፎ ፡ አመራር ፡ መራ
He mismanaged his father's store and soon became bankrupt. ያባቱን ፡ መደብር ፡ በመጥፎ ፡ አመራር ፡ ስለመራው ፡ ወዲያውኑ ፡ ከሰረ

**misplace** ያለቦታው ፡ አኖረ
He misplaced the book of poems in the science section. የግጥሙን ፡ መጽሐፍ ፡ ያለቦታው ፡ ከሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ክፍል ፡ አኖረው

**misprint** የእትም ፡ ስሕተት
This word is not a real word; it is only a misprint. ይህ ፡ ቃል ፡ ትክክል ፡ አይደለም ፤ የእትም ፡ ስሕተት ፡ ነው

**mispronounce** በተሳሳተ ፡ ሁኔታ ፡ አነበበ
Some foreigners mispronounce Amharic words. አንዳንድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ያማርኛ ፡ ቃላትን ፡ በተሳሳተ ፡ ሁኔታ ፡ ያነቧቸዋል

**misquote** ያላለውን ፡ አለ
The student misquoted the teacher in reporting the accident. ተማሪው ፡ አደጋውን ፡ በሚያስረዳበት ፡ ጊዜ ፡ መምህሩ ፡ ያላለውን ፡ አለ

**misread** (misread)
1. ሲያነብ ፡ ተሳሳተ. She misread the recipe and spoiled the cake. የምግብ ፡ አሠራር ፡ መምሪያውን ፡ ስታነብ ፡ ስለተሳሳተች ፡ ኬኩን ፡ አበላሸችው
2. አልገባውም. She sometimes misreads my expression and thinks I am angry. አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የፊቴ ፡ ሁኔታ ፡ ሳይገባት ፡ የተናደድኩ ፡ ይመስላታል

**misrepresent** በማይገባ ፡ ሁኔታ ፡ አቀረበ
The salesman misrepresented the product. አሻሻጩ ፡ እቃውን ፡ በማይገባ ፡ ሁኔታ ፡ አቀረበ

**miss** (v.)
1. አመለጠ(ው). +I missed the first part of his speech. የንግግሩ ፡ የመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ አመለጠኝ
+Do you think I'll miss my train? ባቡሩ ፡ የሚያመልጠኝ ፡ ይመስልሃል ?
+I missed the chance of a ride to town. ወደ ፡ ከተማ ፡ በመኪና ፡ የመሄድ ፡ ዕድል ፡ አመለጠኝ
2. ቀረ. He missed school for a week. ላንድ ፡ ሳምንት ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ቀረ
3. አላየም. I missed the beginning of the race. የውድድሩን ፡ የመጀመሪያ ፡ ክፍል ፡ አላየሁትም
4. አልገባውም. +You missed the point of the story. የታሪኩ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ አልገባህም
5. ሳተ. Our house is so easy to find, you can't miss it. ቤታችን ፡ በቀላሉ ፡ ስለሚገኝ ፡ ልትስተው ፡ አትችልም
He fired, but missed the target. ተኰሰ ፡ ዒላማውን ፡ ሳተ
6. ናፈቀ ፤ ናፈቀ(ው). I'll miss you terribly. በጣም ፡ እናፍቅሃለሁ
+He is a precious friend, and I shall miss him when he leaves. የሚወደድ ፡ ጓደኛ ፡ ስለሆነ ፡ ሲሄድ ፡ ይናፍቀኛል
7. መጥፋቱን ፡ ዐወቀ. When did you miss your briefcase? ቦርሳህ ፡ መጥፋቱን ፡ መቼ ፡ ዐወቅህ ?

**miss** (n.)
*His first shot was a miss. የመጀመሪያውን ፡ ተኰሰ ፡ ሳተ
[See also 'hit']

**Miss** ወይዘሪት
Did you see Miss Laqetch? ወይዘሪት ፡ ላቀችን ፡ አየሃት ?

**misshapen** የተበላሸ
His misshapen body results from an accident in his youth. የሰውነቱ ፡ ቅርጽ ፡ የተበላሸው ፡ በልጅነቱ ፡ በደረሰበት ፡ አደጋ ፡ ምክንያት ፡ ነው

**(be) missing**
1. ጠፋ. The child has been missing for three days. ልጁ ፡ ከጠፋ ፡ ሦስት ፡ ቀኑ ፡ ነው
2. ጐደለ. There are two pages missing in this book. ከዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ገጽ ፡ ጐድሏል
3. ቀረ. Four children were missing from class today. ዛሬ ፡ አራት ፡ ልጆች ፡ ከክፍል ፡ ቀር ተዋል
[See also 'action']

**mission**
1. መልእክት. He completed his mission successfully. መልእክቱን ፡ በሚገባ ፡ አከናወነ
2. መልእክተኞች. The Japanese trade mission visited Ethiopia. የጃፓን ፡ የንግድ ፡ መልእክተኞች ፡ ኢትዮጵያን ፡ ጐበኙ
3. ተልእኮ. The mission of the troops is to catch a band of robbers. የወታደሮቹ ፡ ተልእኮ ፡ የቀማኞችን ፡ ጓድ ፡ መያዝ ፡ ነው
4. ዓላማ. His mission in life is to help the poor. የሕይወቱ ፡ ዓላማ ፡ ድኾችን ፡ መርዳት ፡ ነው
5. ሚስዮን. There is a Catholic mission near here. በዚህ ፡ አቅራቢያ ፡ አንድ ፡ የካቶሊክ ፡ ሚስዮን ፡ አለ

**go on a mission** ዘመተ
The chaplain who went on a mission with the soldiers gave the blessing. ከወታደሮቹ ፡ ጋር ፡ የዘመቱት ፡ ቄስ ፡ ቡራኬ ፡ ሰጡ

**missionary** (missionaries)
1. የወንጌል ፡ ሰባኪ. Missionaries disseminate the Christian belief all over the world. የወንጌል ፡ ሰባኪዎች ፡ የክርስቲያንን ፡ እምነት ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ያሰራጫሉ
2. ሚስዮናዊ. Missionaries are trying to convert the pagans. ሚስዮናውያን ፡ አረመኔዎችን ፡ ለማሳመን ፡ በመሞከር ፡ ላይ ፡ ናቸው

**misspell** ሲጽፍ ፡ ፊደሉን ፡ አሳሳተ
He misspelled the word "rhinoceros". አውራሪስ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ሲጽፍ ፡ ፊደሉን ፡ አሳሳተ

**misspent** የባከነ
He mourned his misspent youth. በባከነው ፡ የወጣትነት ፡ ዘመኑ ፡ ተጸጸተ

**mist** (v.)
*Tears misted her eyes. ዐይኖቿ ፡ እንባ ፡ አቀረሩ

**mist** (n.) ጭጋግ
The hills are hidden in the mist. ኮረብታዎቹ ፡ በጭጋግ ፡ ተሸፍነዋል

**mistake** (mistook), v. አልገባ(ውም)
+You mistake his real purpose. ትክክለኛው ፡ ዓላማው ፡ አልገባህም
*Please don't mistake me! የምለውን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አትተርጉመው
*Sorry, I mistook you for someone else. አዝናለሁ ፤ ሌላ ፡ ሰው ፡ መስለኸኝ ፡ ነው

**mistake** (n.)
1. ስሕተት. How could I make such a mistake? እንዴት ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ስሕተት ፡ ላደርግ ፡ እችላለሁ ?
Sorry, I took it by mistake. አዝናለሁ ፤ በስሕተት ፡ ነው ፡ የወሰድኩት
2. ጥፋት. I am sorry; it's my mistake. አዝናለሁ ፤ የኔ ፡ ጥፋት ፡ ነው

**make a mistake** ተሳሳተ
He made a mistake when he married her. እሷን ፡ ማግባቱ ፡ ተሳሳተ

**mistaken** (adj.) የተሳሳተ
That's a mistaken belief. የተሳሳተ ፡ እምነት ፡ ነው
A mistaken person should admit that he was wrong. የተሳሳተ ፡ ሰው ፡ መሳሳቱን ፡ ማመን ፡ አለበት

**be mistaken** ተሳሳተ
With regard to what you say about the French, there you are mistaken. ስለ ፡ ፈረንሳይ ፡ በተናገርከው ፡ ነገር ፡ ተሳስተሃል

**be mistaken for**
*He's often mistaken for his twin brother. እሱንና ፡ መንታ ፡ ወንድሙን ፡ ያሳስቷቸዋል
*He is often mistaken for an American. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሰዎች ፡ አሜሪካዊ ፡ ይመስላቸዋል

**mistaking** ጥርጥር
There is no mistaking what we ought to do. መሥራት ፡ ስላለብን ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ ጥርጥር ፡ የለም
*There's no mistaking his intention. ዓላማው ፡ ስውር ፡ አይደለም

**Mister,** see **Mr.**

**mistook,** see **mistake**

**mistranslate** አሳስቶ ፡ ተረጐመ

He mistranslated the passage and got a bad grade. ምንባቡን ፡ አሳስቶ ፡ ስለተረጐመው ፡ መጥፎ ፡ ማርክ ፡ አገኘ

**mistreat**

1. በደለ. He mistreated the children. ልጆቹን ፡ በደላቸው

2. አሠቃየ. His wife mistreats him because he is so meek. ጠባዩ ፡ ለስላሳ ፡ ስለሆነ ፡ ሚስቱ ፡ ታሠቃየዋለች

**mistress**

1. እመቤት. Servants obey a kind mistress. አሽከሮች ፡ ለደግ ፡ እመቤት ፡ ይታዘዛሉ

2. ዕቁባት. He considered her his mistress. ዕቁባቱ ፡ አድርጎ ፡ ቈጠራት

**mistrust** (v.) ተጠራጠረ ፤ አላመነም

He mistrusts my intentions. ሐሳቤን ፡ ይጠራጠራል

I mistrust the story he told about his discovery. ስለ ፡ ፍልስፍናው ፡ የተናገረውን ፡ ታሪክ ፡ አላምንም ፡ (እጠራጠራለሁ)

**mistrust** (n.) አለመተማን

Mistrust prevents them from reaching an agreement. አለመተማመን ፡ ከስምምነት ፡ እንዳይደርሱ ፡ ያደርጋቸዋል

**feel mistrust of** ተጠራጠረ

He felt mistrust of the stranger. እንግዳውን ፡ ሰው ፡ ተጠራጠረው

**(be) misty**

1. ጭጋግ ፡ በዛ(በት) ፤ ጉም ፡ በዛ(በት). August is misty. ነሐሴ ፡ ጭጋግ ፡ (ጉም) ፡ ይበዛበታል

2. እንባ ፡ አዘለ. She didn't cry, but her eyes were misty. አላለቀሰችም ፤ ዓይኖቿ ፡ ግን ፡ እንባ ፡ አዝለው ፡ ነበር

**misunderstand** (misunderstood)

1. በደንብ ፡ አልተረዳም. First of all, you misunderstood me. መጀመሪያ ፡ ነገር ፡ በደንብ ፡ አልተረዳኸኝም

2. አልገባ(ውም). +You misunderstood when I said that I was coming on Tuesday. ማክሰኞ ፡ እመጣለሁ ፡ ያልኩህ ፡ አልገባህም

*Don't misunderstand me! የምለው ፡ ይግባህ

**misunderstanding**

1. አለመግባባት. They are trying to clear up the misunderstanding between Poland and Czechoslovakia. በፖላንድና ፡ በቼኮዝሎቫኪያ ፡ መካከል ፡ የተፈጠረውን ፡ አለመግባባት ፡ ለማስወገድ ፡ በመጣር ፡ ላይ ፡ ናቸው

2. በደንብ ፡ አለመረዳት. Her misunderstanding of the recipe caused her to make a mess of the cake. የምግብ ፡ አሠራሩን ፡ መምሪያ ፡ በደንብ ፡ ባለመረዳቷ ፡ ኬኩ ፡ ተበላሸ

**misuse**

1. አጕሳቈለ. He misuses his horses by giving them loads that are too heavy. ከመጠን ፡ በላይ ፡ ከባድ ፡ የሆኑ ፡ ጭነቶች ፡ በመጫን ፡ ፈረሶቹን ፡ ያጕሳቍላቸዋል

2. ያለ ፡ አግባብ ፡ አወጣ. He misused public funds to buy a car for himself. ለራሱ ፡ መኪና ፡ ለመግዛት ፡ የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ያለ ፡ አግባብ ፡ አወጣ

3. ያለ ፡ አግባብ ፡ ተጠቀመ(በት). He doesn't know Amharic well and misuses the words. አማርኛ ፡ በደንብ ፡ ስለማያውቅ ፡ ቃላቱን ፡ ያለ ፡ አግባብ ፡ ይጠቀምባቸዋል

**mitigate** አቃለለ

He asked the judge to mitigate his sentence. ዳኛው ፡ ፍርዱን ፡ እንዲያቃልልለት ፡ ጠየቀ

**mitigating**

*There are no mitigating circumstances for your behavior. የሠራኸው ፡ ሥራ ፡ ሊታለፍ ፡ አይችልም

**mix** (vt.)

1. አቀላቀለ. I mixed yellow and red. ብጫና ፡ ቀይ ፡ ቀለም ፡ አቀላቀልኩ

2. ደባለቀ. Don't mix business with pleasure! ሥራን ፡ ከጨዋታ ፡ አትደባልቅ

3. ጨመረ. The servant mixed a little oil into the dough. ገረዲቱ ፡ ሊጡ ፡ ውስጥ ፡ ጥቂት ፡ ዘይት ፡ ጨመረች

4. ለወሰ. He mixed pepper with bile. በርበሬውን ፡ በአሞት ፡ ለወሰው

**mix** (vi.)

1. ተዋሐዳ. Water and oil don't mix. ውኃና ፡ ዘይት ፡ ሊዋሐዱ ፡ አይችሉም

2. ተስማማ. The two colors mix very well. እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ቀለሞች ፡ በሚገባ ፡ ይስማማሉ

3. ጥልቅ ፡ አለ. She likes to mix in other people's business. በሰው ፡ ነገር ፡ ጥልቅ ፡ ማለት ፡ ትወዳለች

**mix in** ጥልቅ ፡ አለ

Don't mix in. This is none of your business. ጥልቅ ፡ አትበል ፤ አያገባህም

**mix up**
1. አደበላለቀ. He has mixed up everything. ሁሉንም ፡ አደበላልቆታል
2. አመሳቀለ. Don't mix up the cards! ካርታውን ፡ አታመሳቅል

**mix (one) up**
1. አገባ. Don't mix me up in your argument! ጭቅጭቃችሁ ፡ ውስጥ ፡ አታግቡኝ
2. አደናገረ. His explanation mixed me up completely; I can't understand the problem at all. የሱ ፡ አገላለጽ ፡ ጭራሽ ፡ አደናገረኝ ። ፕሮብሌሙን ፡ በፍጹም ፡ ልረዳው ፡ አልችልም

**(be) mixed up** ተገኘ(በት)
The mayor is mixed up in the scandal. በመጥፎ ፡ ድርጊት ፡ ውስጥ ፡ ከንቲባውም ፡ ይገኝበታል

**(be all) mixed up**
1. ተማታ(በት). I'm all mixed up. Is he coming on Tuesday or Friday? ተማቶብኛል ። የሚመጣው ፡ ማክሰኞ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ዓርብ ?
2. ተመሰቃቀለ. The books are all mixed up, and it took me some time to sort them out. መጽሐፎቹ ፡ ተመሰቃቅለው ፡ ስለነበር ፡ በየመልኩ ፡ ለማስቀመጥ ፡ ጊዜ ፡ ወሰደብኝ

**(get) mixed up** ገጠመ
Don't get mixed up with that gang! ከነዚህ ፡ ዱሪዬዎች ፡ ጋር ፡ አትግጠም

**mix well** ተግባባ
He mixes well with all kinds of people. ከማንም ፡ ጋር ፡ ይግባባል

**mixed** (adj.)
1. የተደባለቀ. He bought three boxes of mixed nuts. ሦስት ፡ ሣጥን ፡ የተደባለቀ ፡ ገውዝ ፡ ገዛ
2. የተለያዩ ፡ ሰዎች ፡ የሚኖሩበት. He lives in a mixed neighborhood. የተለያዩ ፡ ሰዎች ፡ የሚኖሩበት ፡ አካባቢ ፡ ይኖራል
3. የመንግሥትና ፡ የግል ፡ አቋም ፡ ያለበት. The mixed economy of the country proved to be fairly successful. የመንግሥትና ፡ የግል ፡ አቋም ፡ ያለበት ፡ ያገሪቱ ፡ ኤኮኖሚ ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ አሳየ

**mixture**
1. ቅልቅል. This drink is a mixture of fruit juices. ይህ ፡ መጠጥ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ፍሬዎች ፡ ጭማቂ ፡ ቅልቅል ፡ ነው
2. ድብልቅ. Nigerians are a mixture of several different ethnic groups. ናይጂሪያውያን ፡ የብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጐሳዎች ፡ ድብልቅ ፡ ናቸው
3. የተቀመመ ፡ መድኃኒት. He takes a special cough mixture for his cold. ለጉንፋኑ ፡ በተለይ ፡ የተቀመመ ፡ የሳል ፡ መድኃኒት ፡ ይወስዳል
[See also 'indiscriminate']

**mix-up** ምስቅልቅል
That was an awful mix-up. ያ ፡ ልክ ፡ የሌለው ፡ ምስቅልቅል ፡ ነበር

**moan** (v.) አቃሰተ
I could hear him moaning in the next room. እሚቀጥለው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ ሲያቃስት ፡ እሰማው ፡ ነበር

**moan** (n.) ማቃሰት
His moans disturbed me all night long. የሱ ፡ ማቃሰት ፡ ሌሊቱን ፡ በሙሉ ፡ አወከኝ

**moat** [በጥንት ፡ ዘመን ፡ ጠላት ፡ እንዳይገባ ፡ ለመከላከል ፡ በግምብ ፡ ዙሪያ ፡ የሚቈፈር ፡ ጥልቀትና ፡ ስፋት ፡ ያለው ፡ ጉድጓድ]

**mob** (mobbed), v. ወረረ
The crowd mobbed the consulate. ሕዝቡ ፡ ቆንስላውን ፡ ወረረው
Spectators mobbed the courtroom. ተመልካቾች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ወረሩት

**be mobbed**
*The stores are always mobbed right before Christmas. ገና ፡ ሲደርስ ፡ መደብሮች ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ይሆናሉ

**mob** (n.) ሕዝብ ። የሚረብሽ ፡ ሕዝብ ። ሲተራመስ ፡ የነበረ ፡ ሕዝብ
He barely escaped being beaten by the mob. ከሕዝቡ ፡ ድብደባ ፡ ለትንሽ ፡ አመለጠ
The soldiers were forced to the extremity of firing to scatter the mob. ወታደሮቹ ፡ የሚረብሸውን ፡ ሕዝብ ፡ ለመበተን ፡ ተኩስ ፡ መክፈት ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው
The mob almost lynched him. ሲተራመስ ፡ የነበረው ፡ ሕዝብ ፡ ሕጋዊ ፡ ባልሆነ ፡ መንገድ ፡ ሊገድለው ፡ ምንም ፡ አልቀረውም ፡ ነበር

**mobile** ተዘዋዋሪ
The Ministry of Education organized two mobile libraries. ትምህርት ፡ ሚኒስቴር ፡ ሁለት ፡ ተዘዋዋሪ ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ አዘጋጅቷል
*She has mobile features. ፊቷ ፡ ይለዋወጣል

**mobilization** የክተት ፡ ሰራዊት ፡ ትእዛዝ
Mobilization was decreed by the Emperor. የክተት ፡ ሰራዊት ፡ ትእዛዝ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ታወጀ

**mobilize**
1. አስከተተ. The President mobilized the armed forces. ፕሬዚዳንቱ ፡ የጦር ፡ ኀይሉን ፡ አስከተተ
2. ለመንግሥት ፡ ተግባር ፡ አዋለ. The President mobilizes industry in time of war. በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ፕሬዚዳንቱ ፡ ኢንዱስትሪዎችን ፡ ለመንግሥት ፡ ተግባር ፡ ያውላቸዋል

**be mobilized** ተከተተ
The army was mobilized to meet the attack. ወራሪውን ፡ ለመቋቋም ፡ ሰራዊት ፡ ተከተተ

**mock** (v.)
1. አላገጠ(በት)፤አፌዘ(በት)፤ አሾፈ(በት). The boys mocked the blind man. ልጆቹ ፡ ዕውሩን ፡ ሰውዬ ፡ አላገጡበት ፡ (አፌዙበት ፤ አሾፉበት)
2. አፈረሰ. His actions mock convention. አድራጎቱ ፡ ልማድን ፡ ያፈርሳል

**mock at** እንደ ፡ ቀልድ ፡ ቈጠረ
He mocked at the idea of a peaceful settlement. የሰላማዊ ፡ ውሳኔ ፡ ጉዳይን ፡ እንደ ፡ ቀልድ ፡ ቈጠረው

**mock** (adj.) የቀልድ
The dance represented a mock battle. ጭፈራው ፡ የቀልድ ፡ ጦርነት ፡ ይመስል ፡ ነበር

**mockery**
1. የመቀለድ ፡ ያህል. His trial was a mockery of justice. ፍርዱ ፡ በሕግ ፡ የመቀለድ ፡ ያህል ፡ ነበር
2. ፌዝ. Their mockery and insults made me cry. ፌዛቸውና ፡ ስድባቸው ፡ አስለቀሰኝ
3. መሳለቂያ. Through his foolishness, he became the mockery of the village. በጅልነቱ ፡ ምክንያት ፡ የመንደሩ ፡ መሳለቂያ ፡ ሆነ

**mode**
1. ሞድ. He dresses in the latest mode. አዲስ ፡ የወጣውን ፡ ሞድ ፡ ይለብሳል
2. ዘዴ. Riding on a donkey is a mode of travel. አህያ ፡ መቀመጥ ፡ የመጓጓዣ ፡ ዘዴ ፡ ነው

**model** (v.)
1. ምስል ፡ ሠራ. He modeled the minister's head in clay. የሚኒስትሩን ፡ ራስ ፡ ምስል ፡ በሸክላ ፡ ሠራ
2. በመከተል ፡ አደራጀ. He modeled his strategy on Napoleon's. የናፖሊዮንን ፡ የጦር ፡ ስልት ፡ በመከተል ፡ የጦር ፡ ዘዴውን ፡ አደራጀ
3. ሞዴል ፡ አሳየ. They model dresses in this shop. እዚህ ፡ መደብር ፡ ውስጥ ፡ የልብስ ፡ ሞዴል ፡ ያሳያሉ

**model oneself** መንገድ ፡ ተከተለ
He modeled himself after his hero. የሚያደንቀውን ፡ ጀግና ፡ መንገድ ፡ ተከተለ

**model** (n.)
1. ሞዴል. He is working on the model of a bridge. የድልድይ ፡ ሞዴል ፡ በመሥራት ፡ ላይ ፡ ነው
His sister works as a model. እኅቱ ፡ ሞዴል ፡ ሆና ፡ ትሠራለች
2. አርአያ. His behavior is a model for others. ምግባሩ ፡ ለሌሎች ፡ አርአያ ፡ ነው
3. ዓይነት. I want a dress like yours because the model is becoming to me. ዓይነቱ ፡ ስለሚስማማኝ ፡ ያንቺ ፡ ዓይነት ፡ ልብስ ፡ መልበስ ፡ እፈልጋለሁ

**model** (adj.) ምሳሌ ፡ የሆነ
A model farm was set up to spread new farming methods. አዲስ ፡ የእርሻ ፡ ዘዴዎችን ፡ ለማስፋፋት ፡ ምሳሌ ፡ የሚሆን ፡ እርሻ ፡ ተቋቋመ
*She is a model housewife. የቤት ፡ ቁንጮ ፡ ናት

**moderate** (v.)
1. በሊቀ ፡ መንበርነት ፡ መራ. We need someone to moderate our meeting. ስብሰባችንን ፡ በሊቀ ፡ መንበርነት ፡ የሚመራልን ፡ ሰው ፡ ያስፈልገናል
2. ለስለስ ፡ አደረገ. During the argument, he moderated his views. በክርክሩ ፡ ጊዜ ፡ ሐሳቡን ፡ ለስለስ ፡ አደረገ

**moderate** (n.) መሀከለኛ ፡ የሆነ
The radicals got many of the moderates to follow them. ተራማጆቹ ፡ በፖለቲካ ፡ አስተያየታቸው ፡ መሀከለኞች ፡ የሆኑት ፡ እንዲከተሏቸው ፡ አደረጉ

**moderate** (adj.)
1. መጠነኛ. He is a moderate drinker. መጠነኛ ፡ ጠጪ ፡ ነው
He has a moderate income and cannot afford to buy a house. ገቢው ፡ መጠነኛ ፡ ስለሆነ ፡ ቤት ፡ ለመግዛት ፡ አይችልም
2. መካከለኛ. His political views are moderate. የፖለቲካ ፡ አስተያየቱ ፡ መካከለኛ ፡ ነው
3. ለስለስ ፡ ያለ. He wrote a moderate reply to my angry letter. በንዴት ፡ ለጻፍኩት ፡ ደብዳቤ ፡ ለስለስ ፡ ያለ ፡ መልስ ፡ ጻፈ
4. ደኅና. Wheat is sold today at moderate prices. ዛሬ ፡ ስንዴ ፡ በደኅና ፡ ዋጋ ፡ ይሸጣል
He has moderate success as a painter. በሠዓሊነት ፡ ደኅና ፡ ስም ፡ አለው

**moderately**
1. ለስለስ ፡ አድርጎ. They expected him to give a fiery speech, but he spoke moderately. የጋለ ፡ ንግግር ፡ ያደርጋል ፡ ብለው ፡ አስበው ፡ ነበር ፡ ግን ፡ ለስለስ ፡ አድርጎ ፡ ተናገረ
2. በመጠኑ. He drank moderately. በመጠኑ ፡ ጠጣ
*He acted moderately. ትሕትና ፡ አሳየ

**moderating**
*The UN exercises a moderating influence in world affairs. የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ በዓለም ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ሽማግሌ ፡ ሆኖ ፡ ይሠራል

**moderation** (= verbal noun) መመጠን
Moderation is necessary in eating. አበላልን ፡ መመጠን ፡ ያስፈልጋል

**practice moderation** መጠነ
People who are too fat must practice moderation in what they eat. በጣም ፡ ወፍራም ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ የሚመገቡትን ፡ መመጠን ፡ አለባቸው

**with moderation** በመጠኑ
Eat and drink with moderation! በመጠኑ ፡ ብላ ፡ ጠጣ

**moderator** የውይይት ፡ መሪ
The moderator kept the two men from becoming very angry at each other. የውይይቱ ፡ መሪ ፡ ሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ እንዳይጣረሩ ፡ አደረገ

**modern** ዘመናዊ ፤ የዘመን
The university gives courses in modern languages. ዩኒቨርሲቲው ፡ የዘመናዊ ፡ ቋንቋዎች ፡ ትምህርት ፡ ይሰጣል
Television is a modern invention. ቴሌቪዥን ፡ ዘመናዊ ፡ ፍልሰፋ ፡ ነው
Schools should adapt their curriculum to modern needs. ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሥርዓተ ፡ ትምህርቱን ፡ ከዘመኑ ፡ ፍላጎት ፡ ጋር ፡ ማራመድ ፡ አለባቸው

**modernization** ዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ
Ethiopia is making great strides in modernization. ኢትዮጵያ ፡ በዘመናዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ታላቅ ፡ እርምጃ ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ ነች

**modernize**
1. ዘመናዊ ፡ አደረገ. We must modernize our house. ቤታችንን ፡ ዘመናዊ ፡ ማድረግ ፡ አለብን
2. አሻሻለ. We must modernize English spelling. የእንግሊዝኛን ፡ ጽሕፈት ፡ ማሻሻል ፡ አለብን

**modest**
1. ትሑት. She's a very modest person. በጣም ፡ ትሑት ፡ ሰው ፡ ናት
2. መጠነኛ. Though his income is modest, he dresses well. ገቢው ፡ መጠነኛ ፡ ቢሆንም ፡ አለባበሱ ፡ ጥሩ ፡ ነው
3. አነስ ፡ ያለ. He lives in a modest little house. አነስ ፡ ባለች ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል

**modesty** ትሕትና
Everyone likes her modesty. ሁሉም ፡ ትሕትናዋን ፡ ይወዳል

**modify** (modified)
1. ለወጠ. Having learned the facts, he modified his opinion. እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ ካወቀ ፡ በኋላ ፡ አስተያየቱን ፡ ለወጠ
2. አሻሻለ. The judge modified the jail sentence. ዳኛው ፡ የእስራቱን ፡ ቅጣት ፡ አሻሻለ
We must modify our requirements for admission to the university to meet the new situation. አዲሱን ፡ ሁኔታ ፡ ለመቋቋም ፡ ለዩኒቨርሲቲ ፡ መግቢያ ፡ የተደነገገውን ፡ ደንብ ፡ ማሻሻል ፡ አለብን
3. ገለጸ. In the phrase 'old man', the adjective 'old' modifies the noun 'man'. ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ በሚለው ፡ ሐረግ ፡ ውስጥ ፡ « ሽማግሌ » ፡ የሚለው ፡ ቅጽል ፡ «ሰው» ፡ የሚለውን ፡ ስም ፡ ይገልጻል

**modulate**
1. አስተካከለ. The cantor wants to modulate the hymn. ሊቀ ፡ መዘምራኑ ፡ ዜማውን ፡ ለማስተካከል ፡ ይፈልጋል
2. አለሰለሰ. He modulated his tone considerably when he discovered that it was the minister, and not the secretary, who was on the phone. በስልክ ፡ የሚያነጋግረው ፡ ጸሐፊው ፡ ሳይሆን ፡ ሚኒስትሩ ፡ መሆናቸውን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ድምፁን ፡ በጣም ፡ አለሰለሰ

**moist** እርጥብ
The ground is moist. መሬቱ ፡ እርጥብ ፡ ነው

**moisten** አረጠበ
He moistened his lips and went on talking. ከንፈሩን ፡ አርጥቦ ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለ

**moisture**
1. ርጥበት. The moisture in the air causes mildew. ያየር ፡ ርጥበት ፡ መሻገትን ፡ ይፈጥራል
2. ተን. The heaviness of the air is due to moisture. ያየሩ ፡ ከባድነት ፡ ከተኑ ፡ የተነሣ ፡ ነው

**molar, ~ tooth** መንጋጋ
My brother does not have his molar teeth yet. የኔ ፡ ወንድም ፡ ገና ፡ መንጋጋ ፡ አላወጣም

**mold** (v.)
1. ምስል ፡ ሠራ. He will mold the head in clay before he makes the statue. ሐውልቱን ፡ ከመሥራቱ ፡ በፊት ፡ የራስ ፡ ምስል ፡ ከሸክላ ፡ ይሠራል
2. አረቀ. His father's discipline molded his character. ያባቱ ፡ አያያዝ ፡ ጠባዩን ፡ አረቀው
3. መራ. His speeches were intended to mold public opinion. ንግግሮቹ ፡ የሕዝብን ፡ አስተያየት ፡ ለመምራት ፡ የታሰቡ ፡ ነበሩ

**mold** (n.)
1. ቃሊብ. When he poured the metal in the mold, it cracked. ብረቱን ፡ ቃሊብ ፡ ላይ ፡ ሲያፈሰው ፡ ተሰነጠቀ
2. ቅርጽ ፡ ማውጫ. You can use this mold for the cake. ይህን ፡ ለኬኩ ፡ ቅርጽ ፡ ማውጫ ፡ ተጠቀምበት
*There was a layer of mold on the cheese. አይቡ ፡ ሻገት ፡ ዘርሮበታል
*The son is formed in his father's mold. ልጅዬው ፡ አባቱን ፡ ቁርጥ ፡ ነው

**molding** ክፈፍ
The moldings around the windows of this room are made of wood. የዚህ ፡ ክፍል ፡ መስኮት ፡ ክፈፎች ፡ ከዕንጨት ፡ የተሠሩ ፡ ናቸው

**(be) moldy** ሻገተ
Since the bread is moldy, throw it away. ዳቦው ፡ ስለሻገተ ፡ ጣለው

**mole** ፍልፈል
The mole heaped up the dug-out earth. ፍልፈሉ ፡ አፈሩን ፡ ቈልሎታል
**have a mole** ማርያም ፡ ሳመችው
She has a mole on her cheek. ጉንጯ ፡ ላይ ፡ ማርያም ፡ ስማታለች

**molest**
1. አበሳጨ. The child molested her older sister. ልጅቷ ፡ ታላቅ ፡ እኅቷን ፡ አበሳጨቻት
2. ነዘነዘ. The beggars molested the tourists. ለማኞቹ ፡ አገር ፡ ጎብኚዎቹን ፡ ነዘነዙዋቸው

**mollify** (mollified)
1. አባበለ. She mollifed the crying child. የሚያለቅሰውን ፡ ልጅ ፡ አባበለችው
2. ቀነሰ. He mollified his demands after he understood the situation. ሁኔታውን ፡ ከተረዳ ፡ በኋላ ፡ ያስፈልገኛል ፡ የሚለውን ፡ ነገር ፡ ቀነሰ

**molten**
1. ከቀለጠ ፡ ብረት ፡ የሚሠራ. A molten statue was worshipped by idol worshippers. ከቀለጠ ፡ ብረት ፡ የሚሠራ ፡ ሐውልት ፡ ጣዖት ፡ በሚያመልኩ ፡ ሰዎች ፡ ይሰገድለት ፡ ነበር
2. የተቀለጠ. The molten metal cracked the mold. የተቀለጠው ፡ ብረት ፡ ቃሊቡን ፡ ሰበረው

**moment**
1. ጊዜ. At that moment, there was no one around. በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በአካባቢው ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አልነበረም
2. ዕለት. The moment of her arrival was a happy one. እሷ ፡ የምትመጣበት ፡ ዕለት ፡ የደስታ ፡ ጊዜ ፡ ነበር

**a moment**
1. ትንሽ. Wait a moment! ትንሽ ፡ ቆይ
2. ለጥቂት ፡ ጊዜ. He stood on the doorsill a moment. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ደፉ ፡ ላይ ፡ ቆመ

**a moment ago** ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት
He was here a moment ago. ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ እዚህ ፡ ነበረ

**at a moment's notice** ማስታወቂያ ፡ እንደተሰጠው ፡ ወዲያውኑ
Be ready to leave at a moment's notice! ማስታወቂያ ፡ እንደተሰጠህ ፡ ወዲያውኑ ፡ ለመነሣት ፡ ተዘጋጅ

**at any moment**
1. አሁን ፡ ከሁን. He was afraid he would be captured at any moment. አሁን ፡ ከሁን ፡ ተያዝኩ ፡ እያለ ፡ ይበረግግ ፡ ነበር
2. አሁን. He will come at any moment. አሁን ፡ ይመጣል
3. ምን ፡ ጊዜም. This wall is so weak that it may go at any moment. ግድግዳው ፡ ልል ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ሊፈርስ ፡ ይችላል

**at the last moment** ጥቂት ፡ ሲቀረው
He arrived at the last moment. ጥቂት ፡ ሲቀረው ፡ መጣ

**at the moment** ለጊዜው ፤ አሁን
At the moment, I can't give you any further information. ለጊዜው ፡ የምሰጥህ ፡ ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ የለኝም
At the moment, our friendship is somewhat strained. አሁን ፡ ጓደኝነታችን ፡ ትንሽ ፡ ሻክሯል

**for a moment** ለጥቂት ፡ ጊዜ
A bright light blinded him for a moment. ብሩህ ፡ ብርሃን ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ዓይኑን ፡ ከለለው

**great moment** ታላቅ ፡ ምዕራፍ
The Emperor's return was a great moment in Ethiopia's history. የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መመለስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ታላቅ ፡ ምዕራፍ ፡ ነበር

**(be of) great moment** ታላቅነት ፡ አለው
This decision was of great moment. ይህ ፡ ውሳኔ ፡ ታላቅነት ፡ ያለው ፡ ነበር

**important moment, be an ~** ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ ያዘ
His presentation at the court was an important moment of his life. ቤተ ፡ መንግሥት ፡ መቅረቡ ፡ በሕይወቱ ፡ ውስጥ ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ የያዘ ፡ ነው

**in a few moments** ባንድ ፡ አፍታ
It was all over in a few moments. ባንድ ፡ አፍታ ፡ አለቀ

**in a moment**
1. ከመቅጽበት. In a moment, all was changed. ከመቅጽበት ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ተለወጠ
2. አሁን. I'll give you your change in a moment. አሁን ፡ መልስህን ፡ እሰጥሃለሁ

**just a moment** እንዴ ፡ ቆይ
Just a moment, please; I am on the phone. እንዴ ፡ ቆይ ፣ ስልክ ፡ ይዤያለሁ

**just this moment** አሁን ፡ ገና
I have just this moment heard the news. ወሬውን ፡ አሁን ፡ ገና ፡ መስማቴ ፡ ነው

**not for a moment** ፈጽሞ
Have you thought of doing it yourself? Not for a moment! ራስህ ፡ ልትሠራው ፡ አስበህ ፡ ነበር ? ፈጽሞ !

**of moment** ከፍ ፡ ያለ
The President is busy on a matter of moment. ፕሬዚዳንቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ናቸው

**the moment** ልክ ፡ እንደ + perfect
I started the moment your letter arrived. ልክ ፡ ደብዳቤህ ፡ እንደደረሰኝ ፡ ተነሣሁ
[See also 'crucial, lucid, only, precise, spur, unguarded, very']

## momentarily
1. ለጥቂት ፡ ደቂቃ ፣ ለጥቂት ፡ ጊዜ. I saw him momentarily between two classes. በሁለት ፡ ክፍለ ፡ ጊዜያት ፡ መሃከል ፡ ለጥቂት ፡ ደቂቃ ፡ አየሁት
The luminous room blinded him momentarily. ብርሃን ፡ የበዛበት ፡ ክፍል ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ዓይኑን ፡ አሳወረው
2. በየጊዜው. The danger of fire is increasing momentarily. የእሳት ፡ አደጋ ፡ በየጊዜው ፡ እየባሰ ፡ ይሄዳል
3. ለጊዜው. I am momentarily out of cash. ለጊዜው ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብ ፡ የለኝም
*We are expecting the doctor momentarily. ሐኪሙ ፡ መምጫው ፡ ነው

## momentary,
1. (= adv.) ለጥቂት ፡ ጊዜ. There was a momentary silence in the room. ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ጸጥታ ፡ ነበር
2. (= adv.) በድንገት. They live in fear of momentary annihilation. በድንገት ፡ እናልቃለን ፡ በሚል ፡ ፍርሃት ፡ ይኖራሉ

## momentous ከፍ ፡ ያለ
The opening of the Koka dam was a momentous occasion. የቆቃ ፡ ግድብ ፡ መከፈት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ በዓል ፡ ነበር

## momentum, gain ~
1. እያየለ ፡ ሄደ. The campaign to make him President gained momentum. እሱን ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ለማድረግ ፡ የሚደረገው ፡ ትግል ፡ እያየለ ፡ ሄደ
2. ፍጥነት ፡ እየጨመረ ፡ ሄደ. A falling object gains momentum as it falls. አንድ ፡ ነገር ፡ ሲወድቅ ፡ እስኪያርፍ ፡ ድረስ ፡ ፍጥነት ፡ እየጨመረ ፡ ይሄዳል

## monarch ንጉሥ ፡ ነገሥት
Haile Sellassie First is an Ethiopian monarch. ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ናቸው

## monarchy (monarchies) ንጉሣዊ ፡ አገዛዝ
Monarchy was established in Ethiopia centuries ago. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ንጉሣዊ ፡ አገዛዝ ፡ የተቋቋመው ፡ ከብዙ ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ በፊት ፡ ነው

## monastery (monasteries) ገዳም (pl. ገዳማት)
There are many monasteries in Ethiopia. ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ገዳማት ፡ አሉ

## monastic የገዳም ፣ የመነኵሳት
He lives a monastic life. የገዳም ፡ (የመነኵሳት) ፡ ኑሮ ፡ ይኖራል

## Monday ሰኞ

## monetary የገንዘብ
The dollar is the monetary unit of the U.S.A. ብር ፡ የአሜሪካ ፡ የገንዘብ ፡ መቍጠሪያ ፡ ነው
*The old car has little monetary value. አሮጌው ፡ መኪና ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አያወጣም

## money ገንዘብ
I'm losing money on that deal. በዚያ ፡ ንግድ ፡ ገንዘብ ፡ እከስራለሁ

**make money** ገንዘብ ፡ አገኘ ፣ ገንዘብ ፡ አተረፈ
I have to make money on this job. በዚህ ፡ ሥራ ፡ ገንዘብ ፡ ማግኘት ፡ አለብኝ

He made a lot of money on the sale of the house. ቤቱን ፡ ሲሸጥ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አተረፈ

**put some money down** ቀብድ ፡ ከፈለ
You have to put some money down on this car. ለዚህ ፡ መኪና ፡ ቀብድ ፡ መክፈል ፡ አለብህ
[See also 'close, expenditures, free, lose, magnanimous, ready, roll, sum, tight, worth']

**moneylender** ገንዘብ ፡ አበዳሪ
I need money, so I'm going to the moneylender. ገንዘብ ፡ ስለሚያስፈልገኝ ፡ ወደ ፡ ገንዘብ ፡ አበዳሪው ፡ እሄዳለሁ

**money order** ሐዋላ
Can I buy a money order at the post office? ከፖስታ ፡ ቤቱ ፡ ሐዋላ ፡ ልገዛ ፡ እችላለሁ ?

**monitor** (v.) ጠለፈ ፡ አዳመጠ
The police are monitoring the telephone calls of all suspects. ፖሊሶች ፡ የተጠርጣሪዎችን ፡ ስልኮች ፡ ሁሉ ፡ ጠልፈው ፡ በማዳመጥ ፡ ላይ ፡ ናቸው

**monitor** (n.) አለቃ ፤ የክፍል ፡ አለቃ
The best student was appointed monitor of his class. ከሁሉ ፡ የተሻለው ፡ ተማሪ ፡ የክፍል ፡ አለቃ ፡ ሆኖ ፡ ተመረጠ
The monitor set the children against the newcomer. የክፍል ፡ አለቃው ፡ ልጆቹን ፡ አዲስ ፡ በመጣው ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ አሳደመ

**monk** መነኩሴ
The monks always pray during a fast. መነኩሴ ፡ በጾም ፡ ጊዜ ፡ ጸሎት ፡ ያዘወትራል

**monkey** (v.), ~ **around with** ነካካ
Stop monkeying around with those tools! እነዚህን ፡ መሣሪያዎች ፡ አትነካካ

**monkey** (n.) ዝንጀሮ
The monkeys destroyed the wheat. ዝንጀሮዎቹ ፡ እህሉን ፡ አጠፉ

**monogamy**
*Most religions preach monogamy. አብዛኞቹ ፡ ሃይማኖቶች ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ ካንድ ፡ ሴት ፡ የሚለውን ፡ ያስተምራሉ

**monolithic** ከቋጥኝ ፡ የተፈለፈለ
There are monolithic churches in Lalibela. በላሊበላ ፡ ውስጥ ፡ ከቋጥኝ ፡ የተፈለፈሉ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ አሉ

**monologue, deliver a** ~ ብቻውን ፡ ተናገረ
The actor delivered a monologue. ተዋናዩ ፡ ብቻውን ፡ ተናገረ

**monophysitism** የተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት
Monophysitism was accepted by Ethiopians in the fourth century. የተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባራተኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ገባ

**monopolize**
1. አጠቃሎ ፡ ለብቻው ፡ ያዘ. The company seeks to monopolize the coffee market. ኩባንያው ፡ የቡናውን ፡ ገበያ ፡ አጠቃሎ ፡ ለብቻው ፡ ለመያዝ ፡ ይፈልጋል
2. ብቻውን ፡ ያዘ. He is always monopolizing the conversation. ሁልጊዜ ፡ ወሬውን ፡ ብቻውን ፡ ይይዘዋል

**monopoly** ሞኖፖል
In some countries, tobacco is a government monopoly. ባንዳንድ ፡ አገሮች ፡ ትምባሆ ፡ የመንግሥት ፡ ሞኖፖል ፡ ነው

**monotheism** ባንድ ፡ አምላክ ፡ ማመን
Christians and Moslems prefer monotheism to polytheism. ክርስቲያኖችና ፡ እስላሞች ፡ ከብዙ ፡ አማልክት ፡ ይልቅ ፡ ባንድ ፡ አምላክ ፡ ማመንን ፡ ይመርጣሉ

**monotonous**
1. የሚያሰለች. Life in a small village is monotonous. ትንሽ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ መኖር ፡ የሚያሰለች ፡ ነው
2. የቸከ. His speech is monotonous. ንግግሩ ፡ የቸከ ፡ ነው

**be monotonous** ዓይን ፡ ሰለቸ
The landscape in the lowlands is monotonous. በቆላው ፡ አገር ፡ ያለው ፡ የመሬት ፡ ገጽ ፡ ዓይን ፡ ይሰለቻል

**monster**
1. ጉድ. A five-legged calf is a monster. አምስት ፡ እግር ፡ ያለው ፡ ጥጃ ፡ ጉድ ፡ ነው
2. ጭራቅ. He painted a picture of Satan in the form of a horrible monster. ሰይጣንን ፡ አስፈሪ ፡ ጭራቅ ፡ አስመስሎ ፡ ሣለው
3. ተወዳዳሪ ፡ የሌለው ፡ አረመኔ. He is a monster of cruelty. በጭካኔው ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሌለው ፡ አረመኔ ፡ ነው

**monstrous**
1. በጣም ፡ አሰቃቂ. He committed a monstrous crime. በጣም ፡ አሰቃቂ ፡ የሆነ ፡ ወንጀል ፡ ፈጸመ
2. መዓት. The public debt is monstrous. የመንግሥቱ ፡ ዕዳ ፡ መዓት ፡ ነው

**month** (n.) ወር
I earn a hundred dollars a month. በወር ፡ መቶ ፡ ብር ፡ አገኛለሁ

**monthly** (n.) በየወሩ ፡ የሚወጣ ፡ ጋዜጣ
He writes for a monthly. በየወሩ ፡ ለሚወጣ ፡ ጋዜጣ ፡ ጽሑፍ ፡ ያዘጋጃል

**monthly** (adj.)
1. የወር. If you miss one monthly payment, they won't complain. ያንድ ፡ ወር ፡ ክፍያ ፡ ብትዘል ፡ አይጨቃጨቁህም
2. (= adv.) በየወሩ. You can pay the amount in monthly installments. ሒሳቡን ፡ በየወሩ ፡ እየከፈልክ ፡ ልትጨርስ ፡ ትችላለህ
3. (= adv.) በወር. His monthly salary is $500. ደሞዙ ፡ በወር ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ነው
[See also 'popular']

**monument**
1. ሐውልት. A monument to Menilek was erected in the city. የአፄ ፡ ምኒልክ ፡ ሐውልት ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ቆሟል
2. ታላቅ ፡ ቅርስ. Homer's works are monuments of Greek culture. የሆመር ፡ ጽሑፎች ፡ ለግሪክ ች ፡ ባህል ፡ ታላቅ ፡ ቅርሶች ፡ ናቸው
3. ቅርስ. The Egyptian pyramids are prodigious monuments. የግብጽ ፡ ፒራሚዶች ፡ የሚያስደንቁ ፡ ቅርሶች ፡ ናቸው

**monumental** ታላቅ
Building a bridge is a monumental task. ድልድይ ፡ መሥራት ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ ነው

**mood** ሁኔታ
In his present mood, you better not speak to him. አሁን ፡ ባለበት ፡ ሁኔታው ፡ ባታነጋግረው ፡ ይሻላል

**moods** ሁኔታ
His moods change from time to time. ሁኔታው ፡ በየጊዜው ፡ ይለዋወጣል

**be in a bad mood** ደስ ፡ አላለ(ውም)
Don't talk to him now; he is in a bad mood. አሁን ፡ አታነጋግረው ፤ ደስ ፡ አላለውም

**be in a good mood**
He is in a good mood. ደስ ፡ ደስ ፡ ብሎታል

**be in the mood for** አሰኘ(ው)
+I'm not in the mood for that. ያንን ፡ ማድረግ ፡ አላሰኘኝም
+I'm not in the mood for laughing. ሣቅ ፡ አላሰኘኝም
[See also 'ebullient, wayward']

**(be) moody**
1. ቀፈፈ. He is a very moody person. ሁልጊዜ ፡ እንደቀፈፈው ፡ ነው
2. ብስጩ ፡ ሆነ. She has been moody ever since she lost her job. ከሥራዋ ፡ ከተሰናበተች ፡ ወዲህ ፡ ብስጩ ፡ ሆናለች

**moon** (v.), ~ **about** በሐሳብ ፡ ዋለለ
She was mooning about all day. በሐሳብ ፡ ስትዋልል ፡ ዋለች

**moon** (n.) ጨረቃ
The moon appeared today. ዛሬ ፡ ጨረቃ ፡ ወጥታለች

**full moon** ሙሉ ፡ ጨረቃ
Is there a full moon tonight? ዛሬ ፡ ሙሉ ፡ ጨረቃ ፡ ትወጣለች ?

**new moon**
*We can see the stars better during the new moon. ጨረቃ ፡ በምትወለድበት ፡ ወቅት ፡ ከዋክብት ፡ በደንብ ፡ ይታዩናል

**once in a blue moon** ከስንት ፡ አንዴ
He visits me once in a blue moon. ከስንት ፡ አንዴ ፡ ሊጠይቀኝ ፡ ይመጣል

**moonless**
*It is a moonless night tonight. ጨረቃ ፡ ዛሬ ፡ አልወጣችም

**moonlight** የጨረቃ ፡ ብርሃን
The garden is beautiful in the moonlight. በጨረቃ ፡ ብርሃን ፡ ያትክልቱ ፡ ቦታ ፡ ደስ ፡ ይላል

**moonstruck**
He acts moonstruck. ወፈፍ ፡ ያደረገው ፡ ይመስላል

**moor** (v.) አሰሮ ፡ አቆመ
The sailor moored the ship to the shore with a thick rope. መርከበኛው ፡ መርከቧን ፡ በወፍራም ፡ ገመድ ፡ ባሕሩ ፡ ዳርቻ ፡ ላይ ፡ አስሮ ፡ አቆማት

**moot** አከራካሪ ፤ መልስ ፡ የማይገኝለት
Which one of the two started the war is a moot point. ከሁለቱ ፡ ጦርነቱን ፡ የጀመረው ፡ ማን ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ ጥያቄ ፡ አከራካሪ ፡ ነው
Whether the Germans would have surrendered had Hitler died in 1944 is a moot question. ሂትለር ፡ በ፲፱፻፵፬ ዓ.ም. ቢሞት ፡ ኖሮ ፡ ጀርመኖች ፡ እጃቸውን ፡ ይሰጡ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ መልስ ፡ የማይገኝለት ፡ ጥያቄ ፡ ነው

**mop** (mopped), v.
1. ወለወለ. I have to mop the floor. ወለሉን ፡ መወልወል ፡ አለብኝ
2. ጠረገ. He mopped his forehead with a handkerchief. ግንባሩን ፡ በመሐረብ ፡ ጠረገ

**mop up** ለቃቀመ
The soldiers are mopping up the scattered enemy units. የተበታተኑትን ፡ የጠላት ፡ ኀይሎች ፡ ወታደሮቹ ፡ በመለቃቀም ፡ ላይ ፡ ናቸው

**mop** (n.) መወልወያ
She swept the floor with the mop. ወለሉን ፡ በመወልወያ ፡ ወለወለችው

**mope** ቅር ፡ አለ(ው)
He moped indoors all day. ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ቅር ፡ ብሎት ፡ እቤት ፡ ዋለ

**moral** (n.) ፍሬ ፡ ነገር
And the moral of the story is this.... የታሪኩ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ይኼው ፡ ነው
**morals** ግብረ ፡ ገብ ፤ ግብረ ፡ ገብነት
He has no morals at all. ግብረ ፡ ገብ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ነው
The church condemns corrupt morals. ቤተ ፡ ክርስቲያኗ ፡ ውድቅ ፡ ግብረ ፡ ገብነትን ፡ ታወግዛለች
**moral** (adj.)
1. የመንፈስ. I need your moral support. ያንተን ፡ የመንፈስ ፡ ድጋፍ ፡ እፈልጋለሁ
Our country won a moral victory in the UN. ሀገራችን ፡ በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ የመንፈስ ፡ ድል ፡ ተጐናጸፈች
2. የግብረ ፡ ገብ. Freely admitting one's guilt and accepting punishment is a moral act. ጥፋትን ፡ አምኖ ፡ ቅጣትን ፡ መቀበል ፡ የግብረ ፡ ገብ ፡ ተግባር ፡ ነው
3. ዐዋቂ. Man is a moral being. ሰው ፡ ዐዋቂ ፡ ፍጡር ፡ ነው
[See also 'value']

**morale** ሞራል
The morale of the troops was excellent. የወታደሮቹ ፡ ሞራል ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ ነበር

**morality** ግብረ ፡ ገብነት ፤ ግብረ ፡ ገብ ፡ መሆን
Critics complain that morality is declining in this country. ተቺዎች ፡ በዚህ ፡ ሀገር ፡ ውስጥ ፡ ግብረ ፡ ገብነት ፡ በመውደቅ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ያማርራሉ
They argued about the morality of dancing on Sunday. እሑድ ፡ እሑድ ፡ መደነስ ፡ ግብረ ፡ ገብ ፡ ስለመሆኑ ፡ ተከራከሩ

**morally** በግብረ ፡ ገብነት ፡ በኩል
What he did was morally wrong. እሱ ፡ ያደረገው ፡ በግብረ ፡ ገብነት ፡ በኩል ፡ ስሕተት ፡ ነበር
**live morally** ግብረ ፡ ገብነት ፡ ነበረው
Because he lived morally, he gained the respect of his neighbors. ግብረ ፡ ገብነት ፡ ስለነበረው ፡ የጐረቤቶችን ፡ አክብሮት ፡ አተረፈ

**morass, turn into a ~** አጨቀየ
Heavy rain turned the highway into a morass. ከባድ ፡ ዝናም ፡ አውራ ፡ ጐዳናውን ፡ አጨቀየው

**morbid** አስከፊ
He thinks morbid thoughts. ሐሳቡ ፡ ሁሉ ፡ አስከፊ ፡ ነው

**more** (adj.) ተጨማሪ
He is asking for more money. ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ ይፈልጋል
I need more men to help me. የሚረዱኝ ፡ ተጨማሪ ፡ ሰዎች ፡ እፈልጋለሁ
**more** (adv.) በይበልጥ
Be more careful in the future! ለወደፊቱ ፡ በይበልጥ ፡ ተጠንቀቅ
**more or less**
1. ከሞላ ፡ ጐደል. I believe that report is more or less true. ያ ፡ ሪፖርት ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ትክክለኛ ፡ ይመስለኛል
2. ይብዛ ፡ ይነስ. All the offices on the first floor are more or less like this. በምድር ፡ ቤት ፡ የሚገኙት ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቶች ፡ ይብዛ ፡ ይነስ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ናቸው
**more than**
1. ከ - - - በላይ. It's more than a month ago that I saw him. ካየሁት ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ በላይ ፡ ሆኗል
There is more than enough. ከሚበቃ ፡ በላይ ፡ አለ
2. ከ - - - ይልቅ. She is more beautiful than my sister. እሷ ፡ ከእኅቴ ፡ ይልቅ ፡ ታምራለች
3. ከ --- የበለጠ. The elevator cannot carry more than ten persons. አሳንሰሩ ፡ ከዐሥር ፡ ሰው ፡ የበለጠ ፡ አይዝም
**more than once** ካንድ ፡ ጊዜ ፡ በላይ ፤ ካንዴም ፡ ሁለቴ
King Theodore defeated Ras Ali more than once. አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ራስ ፡ ዓሊን ፡ ካንድ ፡ ጊዜ ፡ በላይ ፡ (ካንዴም ፡ ሁለቴ) ፡ ድል ፡ አደረጓቸው
**as many more** በተጨማሪ ፡ ያንኑ ፡ ያህል
You gave me ten apples. I should like as many more. ዐሥር ፡ ቱፋ ፡ ሰጥተኸኛል ፤ በተጨማሪ ፡ ያንኑ ፡ ያህል ፡ እፈልጋለሁ
**get more and more** ይበልጥ ፡ (በይበልጥ) ፡ እየ + perfect + ሄደ
This disease is getting more and more complicated. ይህ ፡ በሽታ ፡ ይበልጥ ፡ እየባሰበት ፡ ይሄዳል
Everything is getting more and more expensive. ሁሉም ፡ ነገር ፡ ይበልጥ ፡ እየተወደደ ፡ ይሄዳል

He got more and more involved in the matter. በነገሩ ፡ በይበልጥ ፡ ተካፋይ ፡ እየሆነ ፡ ሄደ

**give more** ጨመረ
Give me two more bottles of wine! ሁለት ፡ ጠርሙስ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ጨምርልኝ

**have some more** ጨመረ
Won't you have some more soup? ሾርባ ፡ አትጨምርም ?

**in ... more** ከ --- በኋላ
The oranges on this tree will reach maturity in two more weeks. በዚህ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ብርቱካኖች ፡ ከሁለት ፡ ሳምንት ፡ በኋላ ፡ ይበስላሉ

**no more** ምንም + negative verb
I have no more money. ምንም ፡ ገንዘብ ፡ የለኝም

**(be) no more** ፈረሰ
The house I lived in is no more. የኖርኩበት ፡ ቤት ፡ ፈረሰ

**no more of**
No more of that, please! እንግዲህ ፡ በቃ

**no more than**
*He's no more able to read Chinese than I am. እሱም ፡ ሆነ ፡ እኔ ፡ ቻይንኛ ፡ ማንበብ ፡ አንችልም

**not any more**
Don't do that any more! እንዳይለምድህ

**the more ... the**
*The more he spoke, the madder he got. በተናገረ ፡ ቁጥር ፡ ንዴቱ ፡ እየባሰበት ፡ ሄደ

**the more ... the more**
*The more I give him, the more he wants. በሰጠሁት ፡ ቁጥር ፡ ይበልጥ ፡ እንድሰጠው ፡ ይፈልጋል

**what more** ከዚህ ፡ በላይ ፡ ምን
What more do you want? ከዚህ ፡ በላይ ፡ ምን ፡ ትፈልጋለህ ?
[See also 'any, even, hardly, nothing, often, once, what']

## moreover ከዚህም ፡ በላይ
Moreover, he talks a lot. ከዚህም ፡ በላይ ፡ ይለፈልፋል
*He is fat; moreover, he is short. ወፍራም ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ አጭር ፡ ነው

## moribund, be ~ እየቀረ ፡ ሄደ
Astrology is moribund as a science. የከዋክብት ፡ ቈጠራ ፡ ሳይንስነቱ ፡ እየቀረ ፡ ሄዷል

## morning
1. ጧት. He slept all morning. ጧቱን ፡ ሙሉ ፡ ተኝቶ ፡ አረፈደ
Yesterday morning I came to see him. ትናንትና ፡ ጧት ፡ ልጠይቀው ፡ መጥቼ ፡ ነበር
2. ቀን. A few mornings ago, birds were hopping about in my garden. ከጥቂት ፡ ቀኖች ፡ በፊት ፡ ወፎች ፡ በአትክልት ፡ ቦታዬ ፡ ውስጥ ፡ ጡብ ፡ ጡብ ፡ ሲሉ ፡ ነበር

**early morning** ማለዳ
He gets up in the early morning. በማለዳ ፡ ይነሣል

**good morning!** እንደምን ፡ አደርክ ? (2nd masc. sg.)

**in the morning hours** ጧት ፡ ጧት
I like to work in the morning hours. ጧት ፡ ጧት ፡ መሥራት ፡ እወዳለሁ

**the following morning** በማግሥቱ ፡ ጧት
They made all the necessary arrangements to leave the following morning. በማግሥቱ ፡ ጧት ፡ ለመሄድ ፡ አስፈላጊውን ፡ ዝግጅት ፡ ሁሉ ፡ አደረጉ

**the next morning** በማግሥቱ
He came in the next morning with a smile on his face. በማግሥቱ ፡ ፊቱን ፡ ፈገግ ፡ አድርጎ ፡ ገባ

**this morning** ዛሬ ፡ ጧት
There was a lot to do this morning. ዛሬ ፡ ጧት ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ነበር
[See also 'thing']

## morning star ያጥቢያ ፡ ኮከብ
Can you see the morning star? ያጥቢያ ፡ ኮከብ ፡ ይታይሃል ?

## (be) morose ከፋ(ው)
+He is morose because he lost his job. ከሥራው ፡ ስለወጣ ፡ ከፍቶታል

## morphology እርባታ
The morphology of the Amharic verb is very difficult. ባማርኛ ፡ የግስ ፡ እርባታ ፡ በጣም ፡ ያስቸግራል

## morrow, on the ~ ነገ ፤ በበነጋው
I will see him on the morrow. ነገ ፡ አገኘዋለሁ
Some say a red sunset imports a fair day on the morrow. ፀሐይ ፡ ስትጠልቅ ፡ ደም ፡ መምሰሏ ፡ በበነጋው ፡ የብራ ፡ ቀን ፡ እንደሚሆን ፡ ያመለክታል ፡ ይባላል

## morsel, ~ of food ቁራሽ
I haven't had a morsel of food since I left the house. ከቤት ፡ ከወጣሁ ፡ ቁራሽም ፡ አላገኘሁ

## mortal (n.) ተራ ፡ ሰው
Entry into the holy of holies is not for

ordinary mortals. ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ የሚፈቀደው ፡ ለማንኛውም ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ አይደለም

**mortal** (adj.)
1. ሟች. Man is mortal. ሰው ፡ ሟች ፡ ነው
2. ከሞት ፡ የሚያደርስ. His injuries proved mortal. ጉዳቱ ፡ ከሞት ፡ የሚያደርስ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ
3. ከባድ. Only God can forgive mortal sins. ከባድ ፡ ኃጢአትን ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ነው
4. ዕርቅ ፡ የማይገባው. They are mortal enemies. ዕርቅ ፡ የማይገባቸው ፡ ጠላቶች ፡ ናቸው
5. የሰው. We all have mortal weaknesses. ሁላችንም ፡ የሰው ፡ ደካማነት ፡ አለብን
6. (= adv.) የሞት ፡ ያህል. The people live in mortal fear of the nearby volcano. ሰዎቹ ፡ በአካባቢያቸው ፡ ያለውን ፡ እሳተ ፡ ገሞራ ፡ የሞት ፡ ያህል ፡ እየፈሩት ፡ ይኖራሉ

## mortality
1. ሟችነት. The mortality of man is a subject of many philosophers. የሰው ፡ ሟችነት ፡ የብዙ ፡ ፈላስፋዎች ፡ ርእስ ፡ ነገር ፡ ነው
2. የሚሞቱ ፡ ሰዎች. The high rate of mortality has been reduced by modern medicine. የሚሞቱት ፡ ሰዎች ፡ ቁጥር ፡ ዛሬ ፡ በዘመናዊ ፡ መድኃኒት ፡ ተቀንሷል
*The epidemic had a high rate of mortality. ወረርሽኙ ፡ በብዙ ፡ የሚቈጠር ፡ ሕዝብ ፡ ፈጀ

**infant mortality** የሚሞቱ ፡ ሕፃናት
The infant mortality rate has been going down. የሚሞቱ ፡ ሕፃናት ፡ ቁጥር ፡ ዝቅ ፡ እያለ ፡ ሄዷል

## mortally ከልብ
The soldiers were mortally grieved by the death of their general. ወታደሮቹ ፡ በጄኔራላቸው ፡ መሞት ፡ ከልብ ፡ አዘኑ
*He was mortally wounded. በጽኑ ፡ ስለቈሰለ ፡ አልተረፈም

**be mortally offended** እንጀቱ ፡ ተቈረጠ
He was mortally offended when she refused to speak to him. አላነጋግርህም ፡ ባለችው ፡ ጊዜ ፡ አንጀቱ ፡ ተቈረጠ

## mortar
1. ሙቀጫ. She ground the spices in a mortar. ቅመሙን ፡ በሙቀጫ ፡ ወቀጠች
2. ሲሚንቶ. The wall is made of stones held together by mortar. ግድግዳው ፡ በሲሚንቶ ፡ ከተያያዙ ፡ ድንጋዮች ፡ የተሠራ ፡ ነው

## mortar fire የአዳፍኔ ፡ ተኩስ
Mortar fire held up our advance. የአዳፍኔ ፡ ተኩስ ፡ ወደፊት ፡ እንዳንገፋ ፡ አደረገን

## mortgage (v.) አስያዘ
He mortgaged his property in order to get money for a car. ለመኪና ፡ መግዣ ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ሲል ፡ ንብረቱን ፡ አስያዘ

## mortgage (n.) መያዣ ፤ ወለድ ፡ አግድ
The estate is encumbered with mortgages. ርስቱ ፡ መያዣ ፡ ተሰጥቷል
I have a mortgage on his house. ቤቱን ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ ይዤዋለሁ

## mortify (mortified) አጕሳቈለ
He mortified his body in order to find salvation. ሊጸድቅ ፡ አስቦ ፡ ሰውነቱን ፡ አጕሳቈለ

**be mortified** በጣም ፡ አፈረ
I was mortified by my son's rude behavior. በልጄ ፡ ብልግና ፡ በጣም ፡ አፈርኩ

## mosque መስጊድ
Muslims go to the mosque every Friday. እስላሞች ፡ ዓርብ ፡ ዓርብ ፡ ወደ ፡ መስጊድ ፡ ይሄዳሉ

## mosquito የወባ ፡ ትንኝ
We were all bitten up by the mosquitos. ሁላችንም ፡ በወባ ፡ ትንኝ ፡ ተነደፍን
[See also 'net']

## moss
1. የደንጊያ ፡ ሽበት. He scraped the moss from the rock. የደንጊያ ፡ ሽበት ፡ ከድንጊያው ፡ ላይ ፡ ፋቀ
2. አረንጓዴ. The stagnant water was covered with moss. የረጋውን ፡ ውኃ ፡ አረንጓዴ ፡ ሸፍኖታል

## most በጣም
The talk was most interesting. ንግግሩ ፡ በጣም ፡ አስደሳች ፡ ነበር
The music pleased me most. ሙዚቃው ፡ በጣም ፡ አስደሰተኝ
*She received us most kindly. መልካም ፡ አቀባበል ፡ አደረገችልን

**most certainly** በርግጥ
I will most certainly go. በርግጥ ፡ እሄዳለሁ

**most everybody** አብዛኞቹ
Most everybody has gone home. አብዛኞቹ ፡ ወደየቤታቸው ፡ ሄደዋል

**most of**
1. አብዛኛውን ፡ ጊዜ. He was ill most of the summer. ክበጋው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ታሞ ፡ ነበር

He is on the road most of the time. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይሄዳል
2. አብዛኞቹ. Most of those present were against it. ከተገኙት ፡ ሰዎች ፡ አብዛኞቹ ፡ ተቃውመውት ፡ ነበር
3. አብዛኛውን. He did most of the work. አብዛኛውን ፡ ሥራ ፡ የሠራው ፡ እሱ ፡ ነው

**at most** ቢበዛ
At most, the bill will come to twenty dollars. ቢበዛ ፡ ሒሳቡ ፡ ሃያ ፡ ብር ፡ ቢሆን ፡ ነው

**at the most** ግፋ ፡ ቢል
At the most, it's worth ten dollars. ግፋ ፡ ቢል ፡ ከዐሥር ፡ ብር ፡ በላይ ፡ አያወጣም

**make the most of** የሚቻለውን ፡ ያህል ፡ ተጠቀመበት
He did not have many opportunities, but he made the most of those that he had. ብዙ ፡ ዕድል ፡ አላገኘም ፤ ግን ፡ ያጋጠመውን ፡ ዕድል ፡ የሚቻለውን ፡ ያህል ፡ ተጠቀመበት
*She is not really beautiful, but she makes the most of her looks. በተፈጥሮ ፡ ቆንጆ ፡ አይደለችም ፡ ግን ፡ ባላት ፡ ውበት ፡ ሁሉ ፡ በሚቻላት ፡ ትጠቀማለች

**the most**
1. ከሁሉም. This is the most dangerous animal. ይህ ፡ ከሁሉም ፡ አደገኛ ፡ አውሬ ፡ ነው
2. ይበልጡን. Who did the most work? ይበልጡን ፡ ሥራ ፡ የሠራው ፡ ማን ፡ ነው ?
3. ከሁሉ ፡ ይበልጥ. This is the most beautiful church I've ever seen. ካየኋቸው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ ይበልጥ ፡ ያምራል
4. ብዙ. The pocketbook with the most money is hers. ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ያለበት ፡ ቦርሳ ፡ የሷ ፡ ነው
*That's the most I can pay. ልከፍል ፡ የምችለው ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ይህ ፡ ነው
*Do the most you can. የቻልከውን ፡ ያህል ፡ ሥራ
[See also 'far, kindly, part']

**mostly**
1. ይበልጡ. The audience consisted mostly of women. በስብሰባው ፡ የነበሩት ፡ ይበልጡ ፡ ሴቶች ፡ ነበሩ
2. አብዛኛውን ፡ ጊዜ. He is mostly out on Sundays. አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ እሑድ ፡ እሑድ ፡ እቤት ፡ አይውልም
3. በብዙ ፡ ረገድ. He's mostly right. በብዙ ፡ ረገድ ፡ ትክክለኛ ፡ ነው

**moth** የእሳት ፡ እራት
There are many moths flying around the lantern. ብዙ ፡ የእሳት ፡ እራቶች ፡ በፋኖሱ ፡ ዙሪያ ፡ ይበራሉ

**mother** (v.) እንደ ፡ እናት ፡ አንከባከበ
She mothers him all the time. እንደ ፡ እናት ፡ ሁልጊዜ ፡ ታንከባክበዋለች

**mother** (n.) እናት
My mother is forty years old. እናቴ ፡ አርባ ፡ ዓመቷ ፡ ነው

**mother-in-law** አማት
My mother-in-law has much land. አማቴ ፡ ብዙ ፡ ርስት ፡ አላቸው

**motherhood** እናትነት
She took the duties of motherhood seriously. የናትነቱን ፡ ኀላፊነት ፡ አጥብቃ ፡ ያዘች

**motherland** የትውልድ ፡ አገር
They defended their motherland. ለትውልድ ፡ አገራቸው ፡ ተከላከሉ

**motherless** እናቱ ፡ የሞተችበት
He is a motherless child. እናቱ ፡ የሞተችበት ፡ ልጅ ፡ ነው

**motherly** የእናት
A young child needs motherly love. ሕፃን ፡ ልጅ ፡ የእናት ፡ ፍቅር ፡ ይፈልጋል

**motherly person** እናት
She's a motherly person. እሷ ፡ እናት ፡ ናት

**mother tongue** የእናት ፡ ቋንቋ
His mother tongue is Amharic. የእናት ፡ ቋንቋው ፡ አማርኛ ፡ ነው

**motif** ዓላማ
The motif of his book is that crime does not pay. የመጽሐፉ ፡ ዓላማ ፡ ወንጀል ፡ የማይጠቅም ፡ መሆኑን ፡ መግለጽ ፡ ነው

**motion** (v.)
1. ምልክት ፡ ሰጠ. He motioned for the taxi to stop. ታክሲው ፡ እንዲቆም ፡ ምልክት ፡ ሰጠው
2. ጠቀሰ. He motioned me to be quiet. ዝም ፡ እንድል ፡ ጠቀሰኝ

**motion** (n.)
1. መነቅነቅ. The motion of the car made him sick. የመኪናው ፡ መነቅነቅ ፡ አቅለሸለሸው
2. ንቅናቄ. Watch my motions carefully, and you will see how I do the trick. ልብ ፡ ብለህ ፡ የማደርገውን ፡ ንቅናቄ ፡ ተመልከትና ፡ እንዴት ፡ አድርጌ ፡ ትንግርቱን ፡ እንደምሠራ ፡ ታያለህ
3. እንቅስቃሴ. If a thing is in motion, it is not at rest. አንድ ፡ ነገር ፡ በእንቅስቃሴ ፡ ላይ ፡ ከሆነ ፡ አልቆመም ፡ ማለት ፡ ነው

4. የቀረበ፡ሐሳብ. I second the motion to lower the taxes. ታክስ ፡ እንዲቀነስ ፡ የቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ እደግፋለሁ

**be in motion** አልቆመም ፤ ተንቀሳቀሰ
The train was still in motion. ባቡሩ ፡ ገና ፡ አልቆመም
If a thing is in motion, it is not at rest. አንድ፡ ነገር ፡ በሚንቀሳቀስበት ፡ ጊዜ ፡ ረግቶ ፡ አልቆመም ፡ ማለት ፡ ነው

**go through the motions** ለይምሰል ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አለ
He doesn't really do anything; he just goes through the motions. ለይምሰል ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ የሚሠራው ፡ ጠቃሚ ፡ ሥራ ፡ የለም
[See also 'circular']

**motionless** ዝም ፡ ብሎ
The lions stood motionless. አንበሶቹ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ ቆሙ

**motion picture** ተንቀሳቃሽ ፡ ፊልም
Motion pictures are now being made in Ethiopia. ተንቀሳቃሽ ፡ ፊልሞች ፡ አሁን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ይሠራሉ

**motivate** ገፋፋ
What motivates him to work so hard? እንደዚህ፡ ጠንክሮ፡ ለመሥራት ፡ የሚገፋፋው ፡ ምንድነው ?

**motive** (n.)
1. ምክንያት. What was his motive for killing her? እሷን ፡ የገደለበት ፡ ምክንያት፡ ምን ፡ ነበር ?
2. የሚገፋፋው ፡ ሐሳብ. His motives are only too obvious. የሚገፋፋው ፡ ሐሳብ ፡ በግልጽ ፡ የሚታወቅ ፡ ነው

**motive** (adj.) የማንቀሳቀሻ
Engines supply motive power. ሞተር ፡ የማንቀሳቀሻ ፡ ኀይል ፡ ይሰጣል

**motley** (adj.)
1. ዥንጉርጉር. Her motley dress attracts attention. ዥንጉርጉር ፡ ልብሷ ፡ የሰው ፡ ዓይን ፡ ይስባል
2. ልዩ፡ልዩ. A motley crowd filled the streets. ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሕዝብ ፡ መንገዱን ፡ ሞላው

**motor** ሞተር
He put a motor in his boat. ለጀልባው ፡ ሞተር ፡ አስገባለት

**motorcycle** ሞተር ፡ ቢሲክሌት
Many traffic policemen ride motorcycles. ብዙ ፡ የትራፊክ ፡ ፖሊሶች ፡ በሞተር ፡ ቢሲክሌት ፡ ይሄዳሉ

**motorize** በመኪና ፡ አጓጓዘ
We have motorized the entire army since World War I. ከንደኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ወዲህ ፡ ሰራዊት ፡ የምናጓጉዘው ፡ በመኪና ፡ ነው

**mottled** ዥንጉርጉር
The hyena has a mottled pelt. ጅብ ፡ ዥንጉርጉር ፡ ቆዳ ፡ አለው

**motto** መመሪያ
'Think before you speak!' is a good motto. « ከመናገርህ ፡ በፊት ፡ አስብ » ፡ የሚለው ፡ ጥሩ ፡ መመሪያ ፡ ነው

**mouldy,** see **moldy**

**mound**
1. ጉብታ. The mound that we see is undoubtedly a grave. የምናየው ፡ ጉብታ ፡ ያለ ፡ ጥርጥር ፡ መቃብር ፡ ነው
2. ቁልል. I found the book under a mound of papers. መጽሐፉን ፡ ከወረቀት ፡ ቁልል ፡ ሥር ፡ አገኘሁት

**mount** (vt.)
1. ተቀመጠ. He mounted his horse and rode off. ፈረሱን ፡ ተቀምጦ ፡ ጋለበ
2. ወጣ. He mounted the ladder. መሰላሉ ፡ ላይ ፡ ወጣ
Theodore mounted the throne in 1848. አፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ የወጡት ፡ በ፲፰፻፵፰ ዓ. ም. ነው
3. አስገባ. He is mounting photographs in an album. በአልበም ፡ ውስጥ ፡ ፎቶግራፍ ፡ እያስገባ ፡ ነው
4. ጠመደ. They mounted a gun on the fortress wall. በትልቁ ፡ ምሽግ ፡ ግምብ ፡ ላይ ፡ መድፍ ፡ ጠመዱ

**mount** (vi.)
1. ፈረሱን ፡ ተቀመጠ. He mounted in haste and rode away. ፈረሱን፡ በችኮላ ፡ ተቀምጦ ፡ ሸመጠጠ
2. ወጣ. The children mounted to the top of the steps. ልጆቹ፡ ከደረጃው ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ወጡ
3. ጨመረ. Our costs are mounting daily. ወጪያችን ፡ በየቀኑ ፡ እየጨመረ ፡ ይሄዳል

**mount** (n.)
1. ተራራ. Have you read the Sermon on the Mount? የተራራውን ፡ ስብከት ፡ አንብበሃል ?
2. ፈረስ ፤ የኮርቻ ፡ ፈረስ. The riders brought their mounts into line. ፈረሰኞቹ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ በሰልፍ ፡ አቆሙ
The general had an excellent mount. ጄኔራሉ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ የሆነ ፡ የኮርቻ ፡ ፈረስ ፡ ነበረው

*His usual mount is a mule. ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ የሚቀመጠው ፡ በቅሎ ፡ ነው

**mountain** ተራራ
How high is that mountain? ያ ፡ ተራራ ፡ ከፍታው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ነው ?

**a mountain of** መዓት
He overcame a mountain of difficulties. መዓት ፡ ዕንቅፋቶችን ፡ ተወጣ

**mountain** (adj.)
1. የተራራ. The mountaintop was covered with snow. የተራራው ፡ እናት ፡ በበረዶ ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር
2. በተራራ ፡ ላይ ፡ የሚኖር. Mountain people are used to a cold climate. በተራራ ፡ ላይ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ቀዝቃዛ ፡ አየር ፡ ለምደዋል
[See also 'range']

**mountain chain** ሸንተረር
A mountain chain separates the two countries. ሸንተረር ፡ ሁለቱን ፡ አገሮች ፡ ያዋስናቸዋል

**mountaineer** [እንደ ፡ ስፖርት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ሥራ ፡ ቈጥሮት ፡ ተራራ ፡ የሚወጣ ፡ ሰው]

**mountain goat** የሜዳ ፡ ፍየል
The hunter brought down a mountain goat. አዳኙ ፡ የሜዳ ፡ ፍየሏን ፡ ተኵሶ ፡ ገደላት

**mountainous** ተራራማ
This region is mountainous. ይህ ፡ ቀበሌ ፡ ተራራማ ፡ ነው

**mountainside** የተራራ ፡ ጥጋት
The house stands on the mountainside almost all alone. ቤቱ ፡ ተነጥሎ ፡ በተራራው ፡ ጥጋት ፡ ላይ ፡ ይገኛል

**mounted** ፈረሰኛ
Mounted police accompanied the parade. ፈረሰኛ ፡ ፖሊሶች ፡ ሰልፉን ፡ ተከተሉት

**be mounted** በፈረስ ፡ ሄደ
Troops that are mounted are called cavalry. በፈረስ ፡ የሚሄዱ ፡ ወታደሮች ፡ ፈረሰኞች ፡ ይባላሉ

**mourn**
1. ሐዘን ፡ ላይ ፡ ነው. He mourns his father's death. ባባቱ ፡ ሞት ፡ ሐዘን ፡ ላይ ፡ ነው
2. አዘነ. The whole nation mourned his passing. በሱ ፡ ሞት ፡ አገሩ ፡ በሙሉ ፡ አዘነ
3. ተጸጸተ. He mourned his misspent youth. በባከነው ፡ የወጣትነት ፡ ዘመኑ ፡ ተጸጸተ

**mourner** ለቀስተኛ ፤ ሐዘንተኛ
There were many mourners at the funeral. በቀብሩ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ለቀስተኞች ፡ (ሐዘንተኞች) ፡ ነበሩ

**mournful**
1. የሐዘን. The priest read the prayer in a mournful voice. ቄሱ ፡ ጸሎቱን ፡ ያነበቡት ፡ በሐዘን ፡ ድምፅ ፡ ነበር
2. ሐዘን ፡ የተመላበት. He answered my letter in a mournful key. ደብዳቤዬን ፡ ሐዘን ፡ በተመላበት ፡ አገላለጽ ፡ መለሰልኝ

**mourning**
1. ልቅሶ ፤ ለቅሶ. The sound of mourning can be heard in the church. ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ግቢ ፡ ልቅሶ ፡ ይሰማል
2. ከል. She still wears mourning. አሁንም ፡ ከል ፡ ትለብሳለች

**be in mourning** ሐዘን ፡ ላይ ፡ ነው
I'm still in mourning. አሁንም ፡ ሐዘን ፡ ላይ ፡ ነኝ

**mouse** (mice) አይጥ
The cat caught a mouse. ድመቷ ፡ አይጡን ፡ ያዘች

**mousetrap** የአይጥ ፡ ወጥመድ
The mousetrap does not function. የአይጥ ፡ ወጥመዱ ፡ አይሠራም

**mouth**
1. አፍ. He opened his mouth and showed his teeth. አፉን ፡ ከፍቶ ፡ ጥርሱን ፡ አሳየ
The dog stopped at the mouth of the cave. ውሻው ፡ ከዋሻው ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ደርሶ ፡ ቆመ
2. መግቢያ. The river broadens at its mouth. ወንዙ ፡ በመግቢያው ፡ ላይ ፡ ይሰፋል
*He has four mouths to feed. አራት ፡ ተቀላቢዎች ፡ አሉት

**from mouth to mouth** ካንዱ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡
The story passed from mouth to mouth. ታሪኩ ፡ ካንዱ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ተላለፈ

**put words in one's mouth**
Don't put words in his mouth! ያላለውን ፡ አትናገር
[See also 'hand, roof, stuff, water, word']

**mouthful** ጉርሻ
The sick boy couldn't eat more than a mouthful. የታመመው ፡ ልጅ ፡ ካንድ ፡ ጉርሻ ፡ የበለጠ ፡ ሊበላ ፡ አልቻለም

**mouthful of food** ጉርሻ
He took a large mouthful of food. ትልቅ ፡ ጉርሻ ፡ ጐረሰ

**take a mouthful of**
*He took a mouthful of beer, but spat it on the ground. በጉንጩ ፡ ሙሉ ፡ ጠላ ፡ ተጉንጭቶ ፡ መሬቱ ፡ ላይ ፡ ተፋው

## mouthpiece

1. አፍ. The mouthpiece of my flute is broken. የዋሽንቴ ፡ አፍ ፡ ተሰብሯል
2. አስተያየት ፡ የሚገልጽ. Al-Ahram is the mouthpiece of the government. አልአህራም ፡ የመንግሥቱን ፡ አስተያየት ፡ የሚገልጽ ፡ ጋዜጣ ፡ ነው

## movable ተንቀሳቃሽ

I sold all my movable property. ተንቀሳቃሽ ፡ ንብረቴን ፡ በሙሉ ፡ ሸጥኩት
Our fingers are movable. ጣቶቻችን ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ናቸው

**be movable ተለዋወጠ**
Christmas is a fixed holiday, but Easter is a movable one. ገና ፡ የሚውልበት ፡ ቀን ፡ የተወሰነ ፡ ነው ፤ ፋሲካ ፡ ግን ፡ ይለዋወጣል

## move (vt.)

1. ዞር ፡ አደረገ. You'll have to move your car. መኪናህን ፡ ዞር ፡ ማድረግ ፡ አለብህ
2. አዘዋወረ. Let's move the table! ጠረጴዛውን ፡ እናዘዋውረው
3. አንቀሳቀሰ. She can't move her foot. እግሯን ፡ ልታንቀሳቅስ ፡ አትችልም
4. አጓጓዘ. Trucks were used to move troops to the front. ወታደሮቹን ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ለማጓጓዝ ፡ በከባድ ፡ መኪናዎች ፡ ተጠቀሙ
5. ወሰደ. A moving company moved our furniture. እቃ ፡ የሚያመላልሰው ፡ ኩባንያ ፡ የቤት ፡ እቃችንን ፡ ወሰደልን
6. አነሣ. Step aside while we are moving the table. ጠረጴዛውን ፡ ልናነሣው ፡ ነውና ፡ ዞር ፡ በል
7. ሐሳብ ፡ አቀረበ. I move that we adjourn. ስብሰባው ፡ እንዲያበቃ ፡ ሐሳብ ፡ አቀርባለሁ
8. ገፋፋ. Nothing I said moved him to offer his help. የተናገርኩት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እርዳታ ፡ እንዲያደርግ ፡ አልገፋፋውም
9. ስሜት ፡ ነካ. The eloquence of the President moved the audience. የፕሬዚዳንቱ ፡ አንደበተ ፡ ርቱዕነት ፡ ያድማጮቹን ፡ ስሜት ፡ ነካ

**move (vi.)**
1. ተንኰሻኰሸ. I hear something moving in the dark. በጨለማው ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ሲንኰሻኰሽ ፡ ይሰማኛል
2. ቤት ፡ ለቀቀ ፤ ቤት ፡ ለወጠ ፤ ቤት ፡ ቀየረ. We're moving on October first. ይህን ፡ ቤት ፡ ጥቅምት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንለቃለን
We moved three times in the last year. ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ቤት ፡ ለወጥን
This house is too small; we will be better off if we move. ይህ ፡ ቤት ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነው ፤ ቤት ፡ ብንቀይር ፡ ይሻላል
3. ተሽከረከረ. When you press the button, the wheels of the machine begin to move. ቁልፉን ፡ ስትጫነው ፡ የመኪናው ፡ መንኰራኲሮች ፡ ይሽከረከራሉ
4. ተጓዘ. We are moving at a good speed now. አሁን ፡ የምንጓዝበት ፡ ፍጥነት ፡ ደኅና ፡ ነው
5. ተራመደ. Mark how carefully he moves! እንዴት ፡ በጥንቃቄ ፡ እንደሚራመድ ፡ አስተውል
6. ተነቃነቀ. His fetters clanked when he moved. ሲነቃነቅ ፡ የእግር ፡ ብረቱ ፡ ተቃጨለ
7. ተካሄደ. The work on the new gymnasium moved slowly. ያዲሱ ፡ ስፖርት ፡ አዳራሽ ፡ ሥራ ፡ በቀስታ ፡ ተካሄደ
8. ደረሰ. The police move quickly whenever a crime is committed. ወንጀል ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ፖሊሶች ፡ ፈጥነው ፡ ይደርሳሉ
9. ዋለ. He moves in the best society. ውሎው ፡ ከትልልቅ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ነው

**move along ወደፊት ፡ ሄደ**
The policeman ordered the crowd to move along. ፖሊሱ ፡ የተሰበሰቡትን ፡ ሰዎች ፡ ወደፊት ፡ እንዲሄዱ ፡ አዘዘ
*Things are finally moving along now. በመጨረሻ ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ መልክ ፡ እያገኘ ፡ ሄደ

**move around ተዘዋወረ**
Although the man was very old, he still moved around with alacrity. ምንም ፡ እንኳን ፡ ሰውዬው ፡ በጣም ፡ ያረጁ ፡ ቢሆኑም ፡ አሁንም ፡ ነቃ ፡ ብለው ፡ ይዘዋወራሉ

**move aside ፈቀቅ ፡ አደረገ**
Move the table aside! ጠረጴዛውን ፡ ፈቀቅ ፡ አድርገው

**move away** (vt.) **ሌላ ፡ ጋ ፡ ወሰደ**
Move the table away, please! ጠረጴዛውን ፡ ሌላ ፡ ጋ ፡ ውሰደው

**move away** (vi.) **ቤት ፡ ለቀቀ**
They moved away a long time ago. ቤቱን ፡ ከለቀቁ ፡ ብዙ ፡ ጊዜያቸው ፡ ነው

**move closer ጠጋ ፡ አደረገ**
Move the lamp closer! መብራቱን ፡ ጠጋ ፡ አድርገው

**move in ገባ(በት)**
The office is not occupied; you may move in. ቢሮው ፡ አልተያዘም ፤ ልትገባበት ፡ ትችላለህ

**move into** ገባ
We're already moved into our new house. አዲ ሱ ፡ ቤታችን ፡ ገብተናል

**move (a) little** ሳብ ፡ አደረገ
Please move your chair forward a little so I can get by. ለማለፍ ፡ እንድችል ፡ እስቲ ፡ ወንበ ርህን ፡ ወደፊት ፡ ሳብ ፡ አድርገው

**move on** አለፈ ፤ ሄደ
Time moves on, no matter what we do. ምንም ፡ ብናደርግ ፡ ጊዜ ፡ ማለፉ ፡ አይቀርም
Move on! ሂድ!

**move out**
*The train moves out slowly. ባቡሩ ፡ ቀስ ፡ በቀ ስ ፡ ፍጥነት ፡ ይጨምራል

**move out to** ገባ
My parents have moved out to the country. ቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ ገጠር ፡ ገብተዋል

**move slowly** ተጓተተ
The work on the building moves slowly. የሕንጻው ፡ ሥራ ፡ ይጓተታል

**move to** ገባ
We're moving to a new house on October first. ጥቅምት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አዲስ ፡ ቤት ፡ እንገባለን

**move up** አደገ
He moved up fast in his new job. ባዲሱ ፡ ሥራው ፡ ቶሎ ፡ አደገ

**move up and down** አርገበገበ
The bird moved its wing up and down. ወፏ ፡ ክንፏን ፡ አርገበገበች

**be deeply moved** ስሜቱ ፡ በጣም ፡ ተነካ ፤ ከባድ ፡ ሐዘን ፡ ተሰማ(ው)
I was deeply moved to hear about his tragic death. አሳዛኙን ፡ አሟሟቱን ፡ በሰማሁ ፡ ጊዜ ፡ ስ ሜቴ ፡ በጣም ፡ ተነካ ፡ (ከባድ ፡ ሐዘን ፡ ተሰማኝ)

**make move** አስኬደ
The mule balked, and nothing could make it move. በቅሎዋ ፡ ለግማ ፡ ስለቆመች ፡ ምንም ፡ ሊያስኬዳት ፡ አልቻለም
[See also 'heaven, limb, tear']

## move (n.)

1. ተራ. Whose move is it? የማን ፡ ተራ ፡ ነው ?
2. እርምጃ. This is a move in the right direction. ይህ ፡ ወደ ፡ ትክክለኛው ፡ አቅጣጫ ፡ የሚመራ ፡ እርምጃ ፡ ነው
*What will his next move be? ቀጥሎ ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ ያደርግ ፡ ይሆን ?
*Do you know all the moves in chess? የሰንጠረዥን ፡ ጨዋታ ፡ ሕጉን ፡ ሁሉ ፡ ታውቃለህ ?

**be on the move** ተንሣ
Our planes reported that enemy forces were on the move. አውሮፕላኖቻችን ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ መነሣቱን ፡ አስታወቁ
*They're forever on the move. ምንም ፡ ጊዜ ፡ አያርፉም

**make a move**
1. አደረገ. He can't make a move without asking his wife. ሚስቱን ፡ ሳይጠይቅ ፡ ምንም ፡ ሊያደርግ ፡ አይችልም
2. ተንቀሳቀሰ. Every move I make hurts. በተንቀሳቀስኩ ፡ ቁጥር ፡ ያመኛል
[See also 'strategic']

## movement

1. እንቅስቃሴ. The enemy's movements were closely watched. የጠላትን ፡ እንቅስቃሴ ፡ በደንብ ፡ ይከታተሉ ፡ ነበር
By a series of rapid movements, our forces managed to halt the enemy's advance. በርከት ፡ ባሉ ፡ ፈጣን ፡ እንቅስቃሴዎች ፡ ወታደሮቻችን ፡ የጠላትን ፡ እርምጃ ፡ ሊገቱ ፡ ቻሉ
He never belonged to any political movement. ከምንም ፡ ዓይነት ፡ የፖለቲካ ፡ እንቅስቃሴ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ አልነበረውም
2. መግቢያ ፡ መውጫ. His movements were closely watched. መግቢያ ፡ መውጫውን ፡ በጥ ብቅ ፡ ይከታተሉ ፡ ነበር

## movie ፊልም

They are showing a good movie today at the cinema. ዛሬ ፡ ሲኒማ ፡ ቤት ፡ ጥሩ ፡ ፊልም ፡ ይታያል

## movie camera ሲኒማ ፡ ማንሻ

I bought a movie camera for my son. ለልጄ ፡ ሲ ኒማ ፡ ማንሻ ፡ ገዛሁለት

## movie theater ሲኒማ ፡ ቤት

A new movie theater was built in the Mercato. መርካቶ ፡ አዲስ ፡ ሲኒማ ፡ ቤት ፡ ተሠርቷል

## moving

1. የሚንቀሳቀስ. Any moving object attracts my attention. የሚንቀሳቀስ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሐ ሳቤን ፡ ይስበዋል
2. ስሜት ፡ የሚነካ. He told us a moving story. ስሜት ፡ የሚነካ ፡ ታሪክ ፡ ነገረን

**moving spirit**
1. ዋና ፡ አዘጋጅ. He was the moving spirit in planning for the party. የድግሱ ፡ ዋና ፡ አዘጋጅ ፡ እሱ ፡ ነበር
2. የታገለ. He was the moving spirit in getting the bill passed. የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ እንዲያልፍ ፡ የ ታገለው ፡ እሱ ፡ ነበር

**mow** ዐጨደ
I must mow the grass. ሣሩን ፡ ማጨድ ፡ አለብኝ
**mow down** ዐጨደ
He mowed the captives down with a gun. ምርኮኞቹን ፡ በጠመንጃ ፡ ዐጨዳቸው

**Mr.**
1. ሚስተር. Where is Mr. Smith? ሚስተር ፡ ስሚዝ ፡ የት ፡ ናቸው ?
2. አቶ. Where is Mr. Kebbede? አቶ ፡ ከበደ ፡ የት ፡ ናቸው ?

**Mrs.**
1. ሚስዝ. Where is Mrs. Smith? ሚስዝ ፡ ስሚዝ ፡ የት ፡ ናቸው ?
2. ወይዘሮ. Where is Mrs. Belaynesh? ወይዘሮ ፡ በላይነሽ ፡ የት ፡ ናቸው ?

**much**
1. ብዙ. There isn't much food in the house. እቤት ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ምግብ ፡ የለም
2. በጣም. I feel much better. በጣም ፡ ተሽሎኛል
You should work much less; you are hurting your health. ጤንነትህን ፡ ስለምትጐዳ ፡ ሥራህን ፡ በጣም ፡ መቀነስ ፡ አለብህ
**much as** ምንም ፡ እንኳን
Much as I should like to go, I feel I must stay here. ምንም ፡ እንኳን ፡ ለመሄድ ፡ ብፈልግ ፡ እዚህ ፡ መቆየት ፡ አለብኝ
**much harder** የበለጠ ፡ ጠንክሮ
You must work much harder. የበለጠ ፡ ጠንክረህ ፡ መሥራት ፡ አለብህ
**much less**
*I didn't see him, much less speak to him. ማናገር ፡ ቀርቶ ፡ አላየሁትም
**much of** አብዛኛው
Much of what you say is true. የምትለው ፡ ነገር ፡ አብዛኛው ፡ እውነት ፡ ነው
**(be) much the same** ምንም ፡ ያህል ፡ አልተለወጠም
The patient's condition is pretty much the same. የበሽተኛው ፡ ሁኔታ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ አልተለወጠም
**as much as**
*This would be as much as saying 'I accept your idea'. ይህ ፡ አሳብህን ፡ እቀበላለሁ ፡ የማለት ፡ ያህል ፡ ነበር
**as much ... as** - - - ም ፡ - - - ም
It's as much your fault as mine. ስሕተቱ ፡ የኔም ፡ ያንተም ፡ ነው
**how much ?**
1. (ዋጋው) ፡ ስንት. How much is this? ይህ ፡ ዋጋው ፡ ስንት ፡ ነው ?
2. ምን ፡ ያህል. How much will this car cost me? ለዚህ ፡ መኪና ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ያስከፍሉኛል ?
**how much !**
1. እንዴት. How much I love that! ያንን ፡ እንዴት ፡ እወደዋለሁ ፡ መሰለህ !
2. ምንኛ. How much I love this country! ይህችን ፡ አገር ፡ ምንኛ ፡ እወዳታለሁ !
**make too much of** አጋነነ
We mustn't make too much of this incident. ይህንን ፡ ጉዳይ ፡ ማጋነን ፡ የለብንም
**not much (of)** እምብዛም
He is not much of a scholar. የርሱ ፡ ምሁርነት ፡ እምብዛም ፡ ነው
**this much** ይህን ፡ ያህል
What's going to happen to you after you eat this much? ይህን ፡ ያህል ፡ በልተህ ፡ ምን ፡ ልትሆን ፡ ነው ?
*This much is certain: He won't play tricks on us again. ዳግመኛ ፡ እንደማይጫወትብን ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው
[See also 'ever, so, thank, that, too, twice, very']

**mucus** ንፍጥ
Wipe off the mucus! ንፍጥህን ፡ ጥረግ

**mud** ጭቃ
In the rainy season, it is difficult to go through the mud. በክረምት ፡ ጭቃው ፡ አያስኬድም
**be covered with mud** ጨቀየ
The doorstep was covered with mud where people had wiped their feet. ሰዎች ፡ እግራቸውን ፡ ስለጠረጉበት ፡ ደጃፉ ፡ ጨቅይቶ ፡ ነበር
**deposit of mud** ደለል
A deposit of mud covered the field after the flood had subsided. ጐርፉ ፡ ከጐደለ ፡ በኋላ ፡ ደለል ፡ ሜዳውን ፡ አለበሰው
**form into mud** አጨቀየ
The rain formed the dust into mud. ዝናቡ ፡ መሬቱን ፡ አጨቀየው
**layer of mud** ደለል
The flood deposited a layer of mud in the streets. ጐርፉ ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ደለል ፡ አከማቸ

**muddle** (v.) አማታ
You have muddled the scheme completely. እቅዱን ፡ በፍጹም ፡ አማተኸዋል

**muddle up** አደናገረ
A financial crisis muddled up the British. እንግሊዞችን ፡ የገንዘብ ፡ ችግር ፡ አደናገራቸው

**be muddled** ተተራመሰ
Everything was muddled by the late arrival of the train. በባቡሩ ፡ ዘግይቶ ፡ መድረስ ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ተተራመሰ

**muddle** (n.), **in a ~** ተመሰቃቅሎ
When mother came home, she found the house in a muddle. እናቴ ፡ እቤት ፡ ስትገባ ፡ ቤቱን ፡ ተመሰቃቅሎ ፡ አገኘችው

**muddy**
1. የጨቀየ. A car drove down the muddy lane. መኪናው ፡ በጨቀየ ፡ ጠባብ ፡ መንገድ ፡ ተጓዘ
2. የጭቃ. Don't walk around with your muddy feet! በጭቃ ፡ እግርህ ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ አትሂድ
3. ድፍርስ. We need a filter for this muddy water. ለዚህ ፡ ድፍርስ ፡ ውኃ ፡ ማጣሪያ ፡ ያስፈልገናል
4. የተማታ. His muddy thinking is difficult to understand. የተማታውን ፡ አስተሳሰቡን ፡ ለመረዳት ፡ ያዳግታል

**be muddy**
1. ጨቀየ. The ground here is muddy. እዚህ ፡ ጋ ፡ መሬቱ ፡ ጨቅይቷል
2. ማጥ ፡ ብቻ ፡ ነው. The shore of the lake is muddy. የሐይቁ ፡ ዳርቻ ፡ ማጥ ፡ ብቻ ፡ ነው

**muffle**
1. ሸፈነ. She muffled her throat in a warm scarf. አንገቷን ፡ በወፍራም ፡ ያንገት ፡ ልብስ ፡ ሸፈነችው
2. አፈነ. You have to muffle this loud noise, it's disturbing everyone. ይህን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ድምፅ ፡ ማፈን ፡ አለብህ ፤ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ያስቸግራል

**muffler** ጭስ ፡ ማውጫ
My car's muffler is broken. የመኪናዬ ፡ ጭስ ፡ ማውጫ ፡ ተሰብሯል

**muggy** ጭፍግግ ፡ ያለ
During the rainy season, the days are muggy. በክረምት ፡ ጊዜ ፡ ቀኑ ፡ ጭፍግግ ፡ ያለ ፡ ነው

**mulch** [ከገለባ ፡ ከቅጠሎችና ፡ ከለስላሳ ፡ አፈር ፡ የተደባለቀ ፡ ማዳበሪያ]

**mule** በቅሎ
You can find a good mule for two hundred dollars. ጥሩ ፡ በቅሎ ፡ በሁለት ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ትገኛለች

**muleteer** ለጓሚ
He hired a muleteer and four mules when he went on a trip to the mountains. ወደ ፡ ተራራው ፡ ለጉዞ ፡ ወጥቶ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ለጓሚና ፡ አራት ፡ በቅሎዎች ፡ ተከራየ

**mull (over)** ሲያወጣ ፡ ሲያወርድ ፡ ቆየ
He mulled over the decision for days. ውሳኔውን ፡ ለብዙ ፡ ቀናት ፡ ሲያወጣ ፡ ሲያወርድ ፡ ቆየ

**multicolored** ብዙ ፡ ቀለማት ፡ ያለው
She put on the multicolored dress. ብዙ ፡ ቀለማት ፡ ያለው ፡ ልብስ ፡ ለበሰች

**multifarious** የተለያየ ፡ ዓይነት
He has multifarious interests. የተለያየ ፡ ዓይነት ፡ ፍላጎት ፡ አለው

**multilateral**
1. ብዙ ፡ ጐን ፡ ያለው. The hexagon is a multilateral geometrical figure. ሄክሳጎን ፡ ብዙ ፡ ጐን ፡ ያለው ፡ የጂዮሜትር ፡ ቅርጽ ፡ ነው
2. የጋራ. The NATO nations signed a multilateral defense agreement. የኔቶ ፡ ድርጅት ፡ አባል ፡ የሆኑ ፡ አገሮች ፡ ለመከላከያ ፡ የሚሆን ፡ የጋራ ፡ ስምምነት ፡ ተፈራረሙ

**multiple**
1. በርከት ፡ ያለ. He suffered multiple injuries. በርከት ፡ ያለ ፡ ያካል ፡ ጉዳት ፡ ደረሰበት
2. ልዩ ፡ ልዩ. He's a man of multiple interests. ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ ነው

**multiplication table** የጊዜ ፡ ቤት
Learn the multiplication table! የጊዜ ፡ ቤት ፡ አጥና !

**multiply** (multiplied), vt. አበዛ
If you multiply 10 by 4, you get 40. ዓሥርን ፡ በአራት ፡ ብታበዛ ፡ አርባ ፡ ይሆናል

**multiply** (vi.)
1. ተራባ. Rabbits multiply very quickly. ጥንቸሎች ፡ ቶሎ ፡ ይራባሉ
2. በዛ. His troubles multiplied. መከራው ፡ በዛ

**multitude, ~ of** በጣም ፡ ብዙ
A multitude of thoughts passed through my mind. በጣም ፡ ብዙ ፡ ነገሮች ፡ ታሰቡኝ

**large mulitude** ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የሌለው ፡ ሕዝብ
A large multitude gathered in the street. መንገዱ ፡ ላይ ፡ ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የሌለው ፡ ሕዝብ ፡ ተሰበሰበ

**multitudinous** በጣም ፡ ብዙ
Multitudinous birds sang in the trees. በጣም ፡ ብዙ ፡ ወፎች ፡ በዛፉ ፡ ላይ ፡ ይንጫጩ ፡ ነበር

**mum, keep ~** ጸጥ ፡ አለ
Keep mum about this; tell no one! ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ጸጥ ፡ በል ፤ ለማንም ፡ አትንገር

**mumble** አጕመተመተ
We can't hear him because he always mumbles. ሁልጊዜ ፡ ስለሚያጕመተምት ፡ የሚለው ፡ አይሰማንም

**mummy** [እንዳይፈርስ ፡ በመድኃኒት ፡ አማካይነት ፡ የተጠበቀ ፡ የሰው ፡ ሬሳ]

**mumps** ጆሮ ፡ ደግፍ
I caught the mumps. ጆሮ ፡ ደግፍ ፡ ይዞኛል

**munch, ~ on**
1. አላመጠ. He is munching on a cookie. ብስኩት ፡ ያላምጣል
2. ቈረጠመ. He is munching on parched grain. ቆሎ ፡ ይቈረጥማል

**mundane** የዚህ ፡ ዓለም
Monks are uninterested in mundane affairs. መነኰሳት ፡ ለዚህ ፡ ዓለም ፡ ጉዳይ ፡ ግድ ፡ የላቸውም

**municipal** የማዘጋጃ ፡ ቤት
Municipal bonds will finance the new waterworks. የማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ቦንዶች ፡ ያዲሱን ፡ የውኃ ፡ ማሰራጫ ፡ ይከፍላሉ

**municipality** (municipalities)
1. ከተማ. There were mostly Moslems in this municipality. በዚህ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ እስላሞች ፡ ነበሩ
2. ማዘጋጃ ፡ ቤት. The municipality building of Addis Ababa is new. ያዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ሕንጻ ፡ አዲስ ፡ ነው

**munificent** ታላቅ
He made a munificent bequest to the university. ለዩኒቨርሲቲው ፡ ታላቅ ፡ ንብረት ፡ አወረሰ

**munition(s)** ትጥቅና ፡ ሥንቅ
The war was lost due to a shortage of munitions. በጦርነቱ ፡ የተሸነፍነው ፡ ትጥቅና ፡ ሥንቅ ፡ በማነሱ ፡ ነው

**mural** (n.) ግድግዳ ፡ ላይ ፡ የተሣለ ፡ ሥዕል
There is a large mural in Africa Hall. በአፍሪካ ፡ አዳራሽ ፡ ግድግዳ ፡ ላይ ፡ የተሣለ ፡ ትልቅ ፡ ሥዕል ፡ አለ

**murder** (v.)
1. ገደለ. He was accused of having murdered his wife. ሚስቱን ፡ በመግደል ፡ ተከሰሰ
2. አበላሸ. She murders the song everytime she tries to sing it. በዘፈነች ፡ ቁጥር ፡ ዘፈኑን ፡ ታበላሸዋለች

**murder** (n.)
1. ነፍስ ፡ ግዳይ. The murder was not discovered until a few days later. ነፍስ ፡ ግዳዩ ፡ እስከ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ አልታወቀም ፡ ነበር
2. ነፍስ ፡ ገዳይነት. The prisoner did not bat an eye when accused of murder. እስረኛው ፡ በነፍስ ፡ ገዳይነት ፡ ሲወነጀል ፡ ዓይኑን ፡ እንኳን ፡ አልሰበረም
3. ግድያ. The murder outraged the citizens. ግድያው ፡ ነዋሪዎቹን ፡ አስቈጣቸው
4. መጋደል. The antagonism between the two villages led to murders. በሁለቱ ፡ መንደሮች ፡ መሀከል ፡ ያለው ፡ ጥላቻ ፡ እስከ ፡ መጋደል ፡ አደረሳቸው
5. መግደል. The murder of the child was a beastly crime. የሕፃኑ ፡ መግደል ፡ የአውሬነት ፡ ተግባር ፡ ነበር
6. አሟሟት. The news of Kennedy's murder astounded everybody. የኬኔዲ ፡ አሟሟት ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ አስደነገጠ

**commit murder** ሰው ፡ ገደለ
He committed murder, so the police arrested him. ሰው ፡ ስለገደለ ፡ ፖሊሶች ፡ ያዙት

**murderer** ነፍስ ፡ ገዳይ
The murderer escaped from the jail. ነፍስ ፡ ገዳዩ ፡ ከእስር ፡ ቤት ፡ አመለጠ

**murderous**
1. ሊገድል ፡ የሚችል. The villain aimed a murderous blow at the hero's back. ተንኰለኛው ፡ ጀግናው ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ ሊገድል ፡ የሚችል ፡ ምት ፡ ሰነዘረ
2. ነፍስ ፡ ለማጥፋት ፡ የታቀደ. A murderous plot was uncovered by the police. ነፍስ ፡ ለማጥፋት ፡ የታቀደው ፡ አድማ ፡ በፖሊስ ፡ ተደረሰበት
3. ካፈር ፡ የሚደባልቅ. He gave me a murderous look. ካፈር ፡ በሚደባልቅ ፡ አስተያየት ፡ አየኝ

**murky** ጨለማ ፡ የሆነ
He could not see anything in the murky cave. ጨለማ ፡ በሆነው ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ሊያይ ፡ አይችልም

**murmur** (v.)
1. አጕረመረመ. They murmur about the work. ሥራው ፡ ስለበዛባቸው ፡ ያጕረመርማሉ
2. አፏጨ ፤ ጮኸ. The wind was murmuring. ነፋሱ ፡ ያፏጭ ፡ (ይጮኽ) ፡ ነበር

**murmur** (n.)
1. ጉርምርምታ. I hear a murmur of dissent.

ያለመስማማታቸውን ፡ የሚገልጽ ፡ ጉሩምሩምታ ፡ ይሰማኛል
The brook's ceaseless murmur is enjoyable. የማያቋርጠው ፡ የምንጩ ፡ ጉሩምሩምታ ፡ አስደሳች ፡ ነው
2. ማጉረምረም. He paid the fine without a murmur. ቅጣቱን ፡ ያላንዳች ፡ ማጉረምረም ፡ ከፈለ

**muscle** ጡንቻ
Physical exercise develops muscles. ጅምናስቲክ ፡ ጡንቻዎቻችንን ፡ ያዳብራል
[See also 'strain']

**muscular**
1. የጡንቻ. He has a muscular ache. የጡንቻ ፡ ሕመም ፡ ይዞታል
2. ጡንቻማ. He has muscular legs. እግሩ ፡ ጡንቻማ ፡ ነው

**muse** አሰላሰለ
The boy spent the whole afternoon musing. ልጁ ፡ ከሰዓት ፡ በኋላ ፡ ሲያሰላስል ፡ ጊዜውን ፡ አሳለፈ

**museum** ቤተ ፡ መዘክር
Let's visit the museum! ቤተ ፡ መዘክሩን ፡ እንጐብኘው

**mush**
1. ንፍሮ. He eats mush made of cornmeal. የበቆሎ ፡ ንፍሮ ፡ ይበላል
2. ማጥ. After the heavy rain, the old dirt road turned to mush. ከባዱ ፡ ዝናብ ፡ ከጣለ ፡ በኋላ ፡ አሮጌው ፡ የአቧራ ፡ መንገድ ፡ ማጥ ፡ ሆነ

**mushroom** (v.) ብቅ ፡ ብቅ ፡ አለ
Stores mushroomed along the highway. በዋናው ፡ መንገድ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ሱቆች ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ አሉ
*The little town mushroomed into a city. ትንሿ ፡ ከተማ ፡ ቶሎ ፡ አደገች

**mushroom** (n.) እንጉዳይ
Mushrooms grow in the rainy season. እንጉዳይ ፡ በክረምት ፡ ይበቅላል

**music** ሙዚቃ
I like to listen to soft music. ለስላሳ ፡ ሙዚቃን ፡ መስማት ፡ እወዳለሁ

**musical** የሙዚቃ
Ethiopia has several kinds of musical instruments. ኢትዮጵያ ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ የሙዚቃ ፡ መሣሪያዎች ፡ አሏት

**musician** ሙዚቀኛ
The musicians took their seats in the hall. ሙዚቀኞቹ ፡ ባዳራሹ ፡ ውስጥ ፡ ስፍራቸውን ፡ ያዙ

**musk** ዝባድ
Musk is obtained from the civet cat. ዝባድ ፡ የሚገኘው ፡ ከጥርኝ ፡ ነው

**musket** ነፍጥ
I have a musket that my grandfather used. አያቴ ፡ ይይዙት ፡ የነበረ ፡ ነፍጥ ፡ አለኝ

**musketeer** ነፍጠኛ
The three musketeers are a famous trio in French literature. ሦስቱ ፡ ነፍጠኞች ፡ በፈረንሳይ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የታወቀ ፡ የሦስት ፡ ሰዎች ፡ ጓድ ፡ ነው

**musky** የዝባድ
This has a musky odor. ይህ ፡ የዝባድ ፡ ሽታ ፡ አለው

**Muslim** እስላም
There are many Muslims in Ethiopia. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ እስላሞች ፡ አሉ

**muslin** ሻሽ
His head was wrapped in muslin to keep off the dirt. አቧራው ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ እንዳይበንበት ፡ ሻሽ ፡ አስሮ ፡ ነበር

**muss** በታተነ
The wind mussed her hair. ነፋሱ ፡ ጸጉሯን ፡ በታተነው

**must** (v.)
1. አለ(በት). This must be the book you want. የምትፈልገው ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ መሆን ፡ አለበት
We must see what can be done. ምን ፡ ማድረግ ፡ እንደሚቻል ፡ ማሰብ ፡ አለብን
You must do as you are told. ያሉህን ፡ መሥራት ፡ አለብህ
2. gerundive + ይሆናል. He must have sneaked into the house. ሹልክ ፡ ብሎ ፡ ገብቶ ፡ ይሆናል
I must have left my briefcase somewhere. ቦርሳዬን ፡ አንዱ ፡ ጋ ፡ ትቼው ፡ ይሆናል
*I must ask you not to do that again. እንዳይደግምህ ፡ አሳስብሃለሁ
*I must try to see him more often. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ላየው ፡ እሞክራለሁ
*You mustn't do that! እንዳታደርገው

**must have** ያስፈልገዋል
She said she must have a new hat for Easter. ለፋሲካ ፡ አዲስ ፡ ባርኔጣ ፡ ያስፈልገኛል ፡ አለች

**must have been** ሳይሆን ፡ አይቀርም
He must have been in Ethiopia at that time. በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም

**must** (n.), **be a ~** ግዴታ ፡ ነው ፤ የግድ ፡ ያስፈልጋል
To finish on time is a must. በጊዜ ፡ መጨረስ ፡ ግዴታ ፡ ነው
In winter warm clothes are a must. በክረምት ፡ ሞቃት ፡ ልብስ ፡ የግድ ፡ ያስፈልጋል

**mustache** ሪዝ
He is growing a mustache. ሪዙን ፡ ያሳድጋል

**mustard** ሰናፍጭ
Mustard is sold in the market. ሰናፍጭ ፡ ገበያ ፡ ውስጥ ፡ ይሸጣል

**muster** ሰበሰበ
The lieutenant is mustering the troops. የመቶ ፡ አለቃው ፡ ወታደሮቹን ፡ ይሰበስባል

**muster (one's) courage** ደረቱን ፡ ገለበጠ ፤ ደረቱን ፡ ገፋ
He mustered his courage and went to see the director. ደረቱን ፡ ገልብጦ ፡ (ገፍቶ) ፡ ሥራ ፡ መሪውን ፡ ለማነጋገር ፡ ሄደ

**muster in** ለወታደርነት ፡ ተመዘገበ
He mustered in last month. ባለፈው ፡ ወር ፡ ለወታደርነት ፡ ተመዘገበ

**be mustered out** ተሰናበተ
He was mustered out of service after the war. ከጦርነቱ ፡ በኋላ ፡ ካገልግሎት ፡ ተሰናበተ

**musty** በስብሶ ፡ የሻገተ
The room was full of musty old clothes. ክፍሉ ፡ በስብሶ ፡ በሻገተ ፡ አሮጌ ፡ ልብስ ፡ ተሞልቶ ፡ ነበር

**be musty** አና ፡ አና ፡ አለ
The room is musty from being closed so long. ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተዘግቶ ፡ በመቆየቱ ፡ ክፍሉ ፡ አና ፡ አና ፡ ይላል

**(be) mutable** በየጊዜው ፡ የሚለዋወጥ
Tax and voting laws are mutable. የታክስና ፡ የምርጫ ፡ ሕጎች ፡ በየጊዜው ፡ የሚለዋወጡ ፡ ሕጎች ፡ ናቸው

**mutate** ተለወጠ
The vegetation of the earth mutated during the Ice Age. የመሬት ፡ ዕፀዋት ፡ የተለወጡት ፡ በበረዶ ፡ ዘመን ፡ ነው

**mutation** መለወጥ
A mutation of the earth's vegetation occurred during the Ice Age. የመሬት ፡ ዕፀዋት ፡ መለወጥ ፡ የሆነው ፡ በበረዶ ፡ ዘመን ፡ ነው

**mute** (v.) አለሰለሰ
He muted his voice. ድምፁን ፡ አለሰለሰ

**be muted** አነሰ
The sound was muted by the distance. ከርቀቱ ፡ የተነሣ ፡ ድምፁ ፡ አነሰ

**mute** (adj.) ዲዳ
He was born mute. ዲዳ ፡ ሆኖ ፡ ተወለደ

**remain mute** ተጋገረ
When the lawyer asked him a question, he remained mute. ጠበቃው ፡ በጠየቀው ፡ ጊዜ ፡ ተጋገረ
[See also 'deaf']

**mutilate**
1. ቈራረጠ. The robbers mutilated the body of the victim. ቀማኞቹ ፡ የገደሉትን ፡ ሰው ፡ ገላ ፡ ቈራረጡት
2. አበላሸ. He mutilated the page by drawing black lines on it. ጥቁር ፡ መሥመር ፡ እያሠመረ ፡ ገጹን ፡ አበላሸው

**mutinous** አድመኛ
The mutinous crew threatened the captain. አድመኞቹ ፡ መርከበኞች ፡ ካፒቴኑን ፡ አስፈራሩት

**mutiny** (mutinied), v. ዐመፀ
The Russian army mutinied before the revolution. የሩሲያ ፡ ወታደሮች ፡ ከሽብሩ ፡ በፊት ፡ ዐመፁ

**mutiny** (n.) ማመፅ
The mutiny of the troops was due to low pay. የወታደሮቹ ፡ ማመፅ ፡ በደሞዝ ፡ ማነስ ፡ ምክንያት ፡ ነበር

**mutter** (v.)
1. አጕረመረመ. Thunder muttered in the distance. ነጐድጓዱ ፡ ከሩቅ ፡ አጕረመረመ
2. ልቡ ፡ አጕረመረመ. He muttered in his sleep. በእንቅልፍ ፡ ልቡ ፡ አጕረመረመ

**mutter to oneself** ብቻውን ፡ አወራ
He was muttering to himself as he walked along. ብቻውን ፡ እያወራ ፡ ይሄዳል

**mutter under one's breath**
*He muttered a curse under his breath. በሆዱ ፡ ተሳደበ

**mutter** (n.)
1. ድምፅ. We could hear the mutter of distant thunder. የመብረቅ ፡ ድምፅ ፡ ከሩቅ ፡ ይሰማናል
2. ጉርምርምታ. There was a mutter of discontent in class. በክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ የቅሬታ ፡ ጉርምርምታ ፡ ይሰማ ፡ ነበር

**mutton** የበግ ፡ ሥጋ
The Ethiopians like to eat mutton. ኢትዮጵያውያን ፡ የበግ ፡ ሥጋ ፡ ይወዳሉ

**mutual** የጋራ
The contract was extended by mutual agreement. ውሉ ፡ በጋራ ፡ ስምምነት ፡ ታደሰ
Mutual respect is essential for true friendship. ለእውነተኛ ፡ ጓደኝነት ፡ የጋራ ፡ አክብሮት ፡ ያስፈልጋል
It will be to our mutual advantage. ጥቅሙ ፡ የጋራችን ፡ ነው

**muzzle** (v.)
1. አፉን ፡ አሰረ. He muzzled the ox so that it would not eat the grain. በሬው ፡ እህል ፡ እንዳይበላ ፡ አፉን ፡ አሰረው
2. ነጻነት ፡ ከለከለ. The government muzzled the press. መንግሥቱ ፡ የጋዜጦችን ፡ ነጻነት ፡ ከለከለ

**muzzle** (n.) አፍ
There is blood on the dog's muzzle. ውሻው ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ደም ፡ አለ
*Oxen wear a muzzle so they won't eat the grain. በሬዎች ፡ እህል ፡ እንዳይበሉ ፡ አፋቸው ፡ ይታሰራል

**my**
1. የኔ. This is my book. ይህ ፡ የኔ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው
2. - e, - ዬ. He is my father. እሱ ፡ አባቴ ፡ ነው
This is my table. ይህ ፡ ጠረጴዛዬ ፡ ነው

**my! my!** አቤት ፡ አቤት!
My! my! What a pretty child she is! አቤት ፡ አቤት ፡ እንዴት ፡ ታምራለች !

**myriads of** ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የሌላቸው
There are myriads of stars on a June night. በሰኔ ፡ ምሽት ፡ ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የሌላቸው ፡ ከዋክብት ፡ ይታያሉ

**myriad** (adj.) ቁጥር ፡ የሌላቸው
They were admiring the myriad stars of the summer night. ቁጥር ፡ የሌላቸውን ፡ የበጋ ፡ ከዋክብት ፡ ያደንቁ ፡ ነበር

**myrrh** ከርቤ
Myrrh is found in the market. ከርቤ ፡ ከገበያ ፡ ይገኛል

**myself** ራሴ
I'll do it myself. ራሴ ፡ እሠራዋለሁ

**be myself**
I am not myself today. ዛሬ ፡ እንደ ፡ ወትሮው ፡ አይደለሁም

**by myself**
1. ብቻዬን. I sat by myself in the garden. አትክልቱ ፡ ውስጥ ፡ ብቻዬን ፡ ተቀመጥኩ
2. ራሴ. I cooked the meal by myself. ምግቡን ፡ ራሴ ፡ አዘጋጀሁት

**mysterious**
1. እንግዳ ፡ የሆነ. His mysterious behavior made the police suspicious. እንግዳ ፡ የሆነው ፡ ሁኔታው ፡ ፖሊሶቹን ፡ ጥርጣሬ ፡ አሳደረባቸው
2. ልዩ ፡ ዓይነት. There was a mysterious light in the sky. በሰማይ ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ብርሃን ፡ ነበር

**mystery**
1. ምስጢር. The mystery of the minister's disappearance was never solved. የሚኒስትሩ ፡ መጥፋት ፡ ምስጢሩ ፡ አልተደረሰበትም
2. የተሰወረ ፡ ጉዳይ. The detective untangled the mystery after a few days. ወንጀል ፡ መርማሪው ፡ የተሰወረውን ፡ ጉዳይ ፡ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ደረሰበት
3. ረቂቅ ፡ ነገር. One of the mysteries of life is love. ከሕይወት ፡ ረቂቅ ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ ፍቅር ፡ ነው

**be a mystery** አልታወቀም
The name of the thief is a mystery. የሌባው ፡ ስም ፡ አልታወቀም

**mystic** (adj.) ረቂቅ
I am studying the mystic teachings of the ancients. የጥንታውያንን ፡ ረቂቅ ፡ ትምህርት ፡ አጠናለሁ

**mystify** (mystified) የሚለውን ፡ አሳጣው
The magician's tricks mystified the audience. የአስማተኛው ፡ ድርጊቶች ፡ ተመልካቾቹን ፡ የሚሉትን ፡ አሳጣቸው

**myth**
1. አፈ ፡ ታሪክ. There is a myth that serpents ruled the land in ancient times. በጥንት ፡ ዘመን ፡ ዘንዶዎች ፡ አገሩን ፡ ይገዙ ፡ ነበር ፡ የሚል ፡ አፈ ፡ ታሪክ ፡ አለ
2. መሠረተ ፡ ቢስ ፡ እምነት. Racial superiority is a myth. አንዱ ፡ ነገድ ፡ ከሌላው ፡ ይበልጣል ፡ ማለት ፡ መሠረተ ፡ ቢስ ፡ እምነት ፡ ነው
3. ተረት. His large stamp collection was just a myth. ብዙ ፡ ቴምብር ፡ ሰብስቤያለሁ ፡ የሚለው ፡ ተረት ፡ ነው

**mythical** በአፈ ፡ ታሪክ ፡ የተፈጠረ
Hercules was a mythical hero. ሄርኩሊስ ፡ በአፈ ፡ ታሪክ ፡ የተፈጠረ ፡ ጀግና ፡ ነበር

**mythology** (mythologies) አፈ ፡ ታሪክ
We study Greek mythology in school. በትምህርት ፡ ቤት ፡ የግሪኮችን ፡ አፈ ፡ ታሪክ ፡ እንማራለን